
ከዚህም በተጨማሪ ጥንት የጀስዊትስ ሰባኪያን ኢትዮጵያን በሃይማኖት ሲያምሱ ኖረው መጨረሻ ላይ ከተባረሩ ከብዙ ዘመን በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን እንዲገቡ ተፈቅዶላቸዋል። እንዲያውም ራሳቸውም ንጉሠ ነገሥቱ የተማሩት በካቶሊክ ፍሬሮች ስለነበረ እንደልብ በየቦታው ሚሲዮናቸውን ለማስፋፋት ዕድሉ አልተነፈጋቸውም። እነዚህ የጀስዊትስ ሰባኪያን መንግሥቱን የካቶሊክ ሃይማኖት እንዲቀበል ለማድረግ ባደረጉት ጥረት ንጉሥ ሱስንዮስን መለወጥ ችለው ነበር። ስለሆነም ለስምንት ዓመት በዚህ ሽኩቻ የሕዝብ እልቂት ተካሂዷል። መጨረሻ ላይ ሲባረሩ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን ለሁለት ከፍለው አንዱን የፀጋ ልጆች ሌላውን ቅብአት ብለው አስተምረውና ኢትዮጵያ ውስጥ መርዝ ተክልን ብለው ፎክረው ከሄዱ በኋላ በዚህ ምክንያት የኦርቶዶክስ ተከታዮች ሲቸገሩበትና ሲጋደሉበት ኖረዋል።

ከክርስትና ሃይማኖት ውጭ በጃንሆይ ዘመን መንግሥት መሠረት የጣለ ሃይማኖት ባሃይ ነው፣ በሃይ ሃይማኖት ከእስልምና ሃይማኖት የፈለቀ፣ ከመቶ ሰማንያ ዓመት በፊት የተፈጠረ ሳይንስን ያገናዘበና ለምሁር ቶሎ የሚመስጥ ሃይማኖት ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ያስተዋወቀው በተግባረ ዕድ ትምሕርት ቤት አስተማሪ የነበረው ፓኪስታናዊ ሚስተር ሙናጅም ነው። ስለሆነም ብዙ የተማሩ አማኞች ለማግኘት ችሏል።

በሌላ በኩል ወደ 35 % አካባቢ አማኝ ያለው የእስልምና ሃይማኖት የሚገባውን ድጋፍ ከንጉሠ ነገሥቱ አላገኘም፣ የሕዝቡ በትምሕርት አለመግፋት ለጃንሆይ በሃይማኖት በኩል የተስተካከለ አስተዳደር ለመፈጸም አዳግቷቸዋል። ስለዥነም "ልጅ ኢያሱን ዓይተህ ተቀጣ" ከሚለው የተማሩ ይመስል በዚህ ጉዳይ የተቆጠቡ ነበሩ።





# ምዕራፍ ፳፱

## ያለፉትን ማስታወስ

መንግሥት ተለውጦ በሌላ ሲተካ ተተኪው ከበፊቱ መንግሥት የከፋ ከሆነበት ሕዝቡ ያለፈውን መንግሥት ግሩም እንደ ነበረ አድርጎ ያቀርበዋል። ደርግ የበለጠ ጨቋኝ ነው ለማለት ተማሪ "ኃይልዬ ማረኝ! ማረኝ!" እያለ ዘምሯል። ይኸ ማለት ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጥሩ ነው ለማለት አልነበረም። ሁለቱን ሲያወዳድር ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ይሻል ነበር ለማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣን የሚይዘው መንግሥት መልካም ነገሮችን መሥራት ሲያቅተው ያለፉትን መውቀስና በእነሱም ላይ ድክመትን ማላከክ እንደ ልማድ ሆኗል። ይኸ የጎላው በደርግ ዘመን መንግሥት ነው። ደርግ ያለፈውን መንግሥት የተሻለ ሁኔታ ሕዝቡ እንዳይገነዘብ ሥነ ልቦናውን ለመቀየር ብዙ ጥሮ ተሳክቶለትም ነበር። በጃንሆይ ዘመን መንግሥት የነበረው ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነው። ጃንሆይን ታላቅ መሪ ለማስመሰል ያለፉትን ባለታሪኮች መዘንጋት ሲሆን በዚያው መጠን የአገር ውስጥ ባለታሪኮችን ብቻ ሳይሆን የውጭ አገር መሪዎችንም ማጋነን በተዘዋዋሪ መንገድ የተከለከለ ነበር።

ፖል ራኦ የሚባል ትውልዱ ህንዳዊ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የኾነ ወዳጅ ነበረኝ። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በሄራልድ ጋዜጣ ላይ በየወቅቱ ስለ ተለያዩ ጉዳዮች ይጽፍ ነበርና በአንድ ወቅት ስለ አንድ አፍሪካዊ መሪ ዝና ጽፎ ለሄራልድ ጋዜጣ አዘጋጅ ሰጥቶት ቢጠብቅ ጋዜጣው ላይ አልወጣም። ነገሩ ይቸግረውና ሄዶ አዘጋጁን ቢጠይቀው "አየህ! የአንድ ሌላ አፍሪካዊን መሪ ታሪክ ከፍ አድርገን ስንጽፍ የእኛን መሪ ማሳነስ ስለሚሆን አውቄ ነው የዘለልኩት" ብሎ እንደመለሰለት ተገርሞ አጫውቶኛል።



ፖል ራኦና ጸሐፊው

ስለ አፄ ቴዎድሮስ ተማሪውና ወጣቱ ማውሳት ቢወድም የሚፈለገው ግን ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ክብርና በጎ ተግባር እንዲንጸባረቅ ብቻ ነበር። አንዱ እበላ ባይማ ሳንሱር አልፎ መልክዓ ኃይለ ሥላሴ የሚል የጸሎት መጽሐፍ ጽፎ ነበር። ንጉሣችንን መውደድና ማክበር ግዴታችን ቢሆንም ማምለክ ግን ጸያፍ ነው። እዚህ ላይ ተወቃሹ አምላኪውም ጭምር ነው።

አፄ ቴዎድሮስን ያህል ኢትዮጵያን አንድ ያደረጉ፣ አገራቱን የእጅ ሙያ ለማስተማር የታገሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው የመጡትን ፈረንጆች መድፍ እንዲሠሩ ያደረጉና ከካሊብ በኋላ ውሃ ላይ ባሠሩት ታንኳ የተዋጉ ጀግና ምንም ያህል አይወሳላቸውም ነበር። ከዚህም አንጻር ተማሪዎች አፄ ቴዎድሮስ የተወለዱበትን መቶኛ ዓመት ለማክበር ትልቅ



ዝግጅት አድርገው መንግሥት ጉዳዩ ስላሳሰበው በዘመኑ የቸርችል ጎዳና ተቃንቶና ተሠርቶ ወደ ተክለ ሃይማኖት አደባባይና ወደ ታራስ[19] ሠፈር (ተረት ሠፈር ወይም ወደ አሮጌ ቄራ በሚወስደው መንገድ መገንጠያ) ስም ያልወጣለት አደባባይ ስለነበረ መጨረሻ ላይ የአፄ ቴዎድሮስ አደባባይ ተብሎ ተሠየመ።



በአቶ አለፈሰገ ሰላም የተነደፈው የአጼ ቴዎድሮሰ ሐውልት ሲጎበኝ

በዚያው ዘመን ሐውልት ሊሠራ ታስበና 'የሚሠራው ሐውልት ዘውድ እንደጫነ ይሁን'፣ 'የለም በሹሩባ ይሁን' የሚሉ ወገኖች ሲከራከሩ ጊዜ ፈጁ። በሹሩባ ይሠራ የሚሉት የንጉሥ ዘር ስላልኾነ ዘውድ መጫን የለበትም የሚል አስተሳሰብ ሲያንጸባርቁ ዘውድ እንደጫነ ይሠራ የሚሉት ደግሞ ንጉሥ ስለነበረ ዘውድ መጫኑ መታየት አለበት የሚል አስተሳሰብ አመጡ። በተፈጠረው እልህና አለመግባባት ሐውልቱ ሳይሠራ ቆይቶ መጨረሻ ላይ ስምምነት የተደረሰበትን ለማሠራት በክንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወት አማካይነት ጃንሆይ ዘንድ ለማስፈቀድ ቀርቦ ሳይጸድቅ

[19] የፈረንሣይ ተወላጅ ሙሴ ታራስ በ1916 ዓ.ም ሲኒማ ቤት ከፍቶ ሕዝቡ ይኸንኑ አዳራሽ የሰይጣን ቤት ብሎ ይጠራው ነበር። አሁንም አዳራሹ በቴዎድሮስ አደባባይ ይገኛል። ሠፈሩም ታራስ ወይም በትስምዶ ተረት ሠፈር ይባላል።

ቀረ። ከንቲባ ዘውዴም ሌላ ቦታ ተሹመው ስለሄዱ የሐውልቱን ሥራ የሚያነሳ ባለሥልጣን አልተገኘም። ስለ ሐውልቱ ምንም ሳይደረግ መንግሥት ተለወጠ።

ይኸው የአፄ ቴዎድሮስ ሐውልት ጉዳይ በደርግ ዘመነ መንግሥት ሳይነሳ ታልፏል። በቅርብ ጊዜ አቶ ብዙነህ ተስፋ የሚባሉ አርቲስት ሐውልቱን "ያለመንግሥት ወጭ በግሌ ለመሥራት ፈቃድ ካወጣሁ በኋላ ለሦስት ዓመት በሥራው ተጠምጄ ልጨርስ ስል የመቅደላ ቅርስ አስመላሽ ኮሚቴ ሐውልቱን ለማሠራት ሌላ ፈቃድ አውጥቶ በቅድሚያ የሴባስቶፖልን መድፍ እቦታው ላይ አቆመ" ሲሉ በጋዜጣ መግለጫ ሰጠተዋል። እንደተባለውም የመቅደላ ቅርስ አስመላሽ ኮሚቴ ከሐውልቱ አስቀድሞ የሴባስቶፖልን መድፍ አሠርቶታል።



በአቶ ብዙነህ ተስፋ ሊሠራ የተወጠነው የአፄ ቴዎድሮስ ሐውልት

መለስ ብለን በአዲስ አበባ ውስጥ የአፄ ቴዎድሮስ መንገድ የሚባለውን ማውሳቱ ቢያሳፍርም ታሪክ ነውና የት እንደነበረ እንመልከት። ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወይም አድዋ ጎዳና ወደ ናዝሬት ትምህርት ቤት የሚወስደው አርባ ደረጃ በመባል የሚታወቀው የእግር መንገድ የአፄ ቴዎድሮስ መንገድ ይባል ነበር። ይህ ነገር ብዙ ሰዎችን ቅር ያሰኝ ነበረና በኋላ ግን በዝምታ ተረሳ። ደርግ በፊት የነበረውን የተጠረበ ጥቁር



ድንጋይ ንጣፍ ነቅሎ በምትኩ በበሃ ድንጋይ በደረጃ መልክ አሠራው። በመጨረሻ የወጪ ወራጁ እግር ስለበዛበትና ድንጋዩ ተበልቶ የማያምርና አባጣ ጎርባጣ ደረጃ ሆነ።



የአፄ ቴዎድሮስ መንገድ (አርባ ደረጃ)

በሌላ በኩል ከስድስት ኪሎ እስከ አፍንጮ በር ያለው በአፄ ዮሐንስ ስም የተሰየመው መንገድስ ለእሳቸው ሥራ ተመጣጣኝ ሆኖ ነው? ለዚያውስ ስማቸው መቼ ተጻፈበት። በጠቅላላው መንገድ ለተሰየመላቸው ታላላቅ ሰዎች ስማቸውን እየመንገዱ ዳር ላይ መጻፉ የማን ኃላፊነት ይሆን?


አብዮታዊው የደርግ መንግሥት የሰው አገር አብዮተኛ ሐውልት የማርክስን፣ የሌኒንን ሲያሠራ የራሱን አገር ባለታሪኮች እንደረሳ ይታወቃል። የማርክስ ሐውልት አረንጓዴ ቀለም ስለፈሰሰበት ማርክሲስት ነን የሚሉ ሰዎች ተጨንቀው ቀለሙን ለማስለቀቅ ቢሞክሩም አቅቷቸው እንደተዥጎረጎረ ቀርቷል። የሌኒን ሐውልት ደግሞ ደርግ ገና ከሥልጣን ሳይወርድ ተነቅሎ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ቴክኒክ ክፍል ተጋድሞ ይገኛል።

አንድ መሪ በሥልጣን ዘመኑ የራሱን ሐውልት ማሠራቱ ከመሪው ሕይወት በኋላ ተከታዩ ትውልድ ካላመነበት የመፍረስ ዕድል ብዙ ጊዜ ስለሚገጥመው ትርፉ ኪሣራ ብቻ ይሆናል። ይሄም በሂትለር ታሪክ የታየ ስለነበረ ለጃንሆይ ሐውልት ይሠራ እያሉ ብዙ ሰዎች ሃሳብ ቢያቀርቡም በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል። በመሃሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የነበሩ የህንድ ማኅበረ ሰብ አራዳ መካከል ሲኒማ ኤምፓየር ፊት ለፊት የጃንሆይን ሐውልት በራሳቸው ወጭ አቁመው ነበር። ነገር ግን በኋላ ላይ የተማሪ ንቅናቄ በተፋፋመበት ወቅት ሐውልቱን አንዴ አፍንጫውን በመሸረፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ ቀይ ቀለም ላዩ ላይ በማፍሰስ ሐውልቱን እንደማይፈልጉት አሳውቀው ነበር። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ይኽንኑ ሐውልት ተከታይ ለማብዛት ሲል ወዲያው አነሳው። ሆኖም የደርግ መሪ ራሳቸው በዘመናቸው ዋናው ፖስታ ቤት ፊት ለፊት የሚገኘውን የድላችንን ሐውልት ሲያሠሩ የራሳቸውን ምስል በነሃስ አስቀርጸው ለጥፈውበታል። ምንም እንኳን በዘመናቸው የንጉሡ ነገሥቱ ሐውልት እንዳይሠራ አንዳንድ ሰዎች ቢቃወሙም የነፃነት ሐውልት (አራት ኪሎ) ላይ ምስላቸው ተቀርጿል። በኋላ ግን ደርግ ምስላቸውን አስጠርቦ መልኩን ቀይሮታል።

የሚያሳዝነው ግን ጃንሆይም ቢሆኑ ከእሳቸው በፊት የነገሡት ታላላቅ ንጉሦች ታሪክ እንዲነሳ እጅግም አለመፈለጋቸው ነው። ያም ሆኖ ግን የሕዝቡ ፍቅር ለአፄ ምኒልክ ከፍተኛ በመሆኑ ተቸግረውና የአፄ ምኒልክን ሐውልት በቅድሚያ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ አዝዘው ያሠሩት ስለነበረ እንጂ ፈልገው ያቆሙት አልነበረም። ጠላት አፍርሶት ታች ግቢ ቀብሮት ኖሮ ሲወጣ እንደገና ሲያቆሙት ሐውልቱ ያረፈበት ድንጋይ ደረጃው ከበፊቱ ዝቅ ያለ እንዲሆን ተደርጓል። እንዲያውም ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወትን ሐውልቱ እንዲነሳና አፄ ምኒልክ ሆስፒታል ፊት ለፊት ባለው ካሊብ አደባባይ ላይ እንዲቆም ቢያዟቸው ከንቲባው ጉዳዩን ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አቀረቡና ከፍተኛ ተቃውሞ ተደረገ። በተለይ የአቧሬ ወረዳ ዕድሮች ሊቀ መንበር በነበሩት በግራዝማች ኀኑይ በላይነህ ወልደ የስና በሌሎችም ብርታት ሐውልቱ ሳይነሳ ቀረ። ሰዎች በፊት ሐውልቱ ጋሻ ነበረው እያሉ ቢናገሩም ንጉሥ በሥልጣኑ ቀጭ ስለሆነና መከላከያ ጋሻ ስለማይገዝ ሐውልቱ ላይ ከበፊቱም ጋሻ አልነበረበትም።



ኢትዮጵያ ባለታሪክ አገርና የሚሰዉላት ልጆች ያሏት እናት ናት። የመንግሥት ሥልጣን የሚጨብጡ ሁሉ ለአገራቸው ታሪክ ሠርተው በሞቱት ልጆችዋ ሰለሚቀኑ ታሪካቸውን ይደብቃሉ። ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማሪያም መንገድ ሃጠረጉላቸውን የአቶ ገርማሜ ንዋይን ታሪክ አንስተው አያውቁም። እንዲያውም አብዮቱ በፈነዳ ጊዜ የእነ መንግሥቱ ንዋይ ፎቶግራፍ በሰፊው መሸጥ ሲጀመር ተከለከለ። አዲሱ ትውልድም ያለፉትን ባለታሪኮች ውለታ ግንዛቤ ውስጥ አያስገባም፡፡ ለምሳሌ የአቡነ ጴጥሮስ ደም የፈሰሰበት ቦታ ላይ ያለው የምልክት ድንጋይ የቆሻሻ መጣያ ሆኗል። ለጠላት አትገዙ እያሉ የተገደሉት ጳጳስ የከፈሉት መስዋዕትነት ለነጻነታችን አስተዋጽኦ እንደነበረው ግን የማያውቅ ያለ አይመስልም። ሐውልት መከበር ያለበት ሆኖ እያለ ማታ ማታ አሽከርካሪ አጥሩን በመኪና እየገረሰሰ ሲሄድ ከከፍተኛ ቅጣት ጋር ማሳደሻውን እስከፍሎ ወዲያው እንደማሳደስ ችላ እየተባለ ማፈሪያ እየሆነ ይታያል።



የአፄ ምኒልክ ሐውልት ከጠላት ወረራ በኋላና (በግራ) በፊት(በቀኝ)

ከጠላት ወረራ በኋላ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት እንደገና በ1934 ዓ.ም ሲከፈት ስሙ ተቀይሮ "ለዓይነት የቆመ የአስፋው

ወሰን ትምህርት ቤት” ተብሎ ተጠራ። ሕዝቡ በጥንት ስሙ መጥራቱን ስለቀጠለ እንደገና በ1937 ዓ.ም የበፊት ስሙ ተመለሰለት።

በ1939 ዓ.ም መጋቢት ወር ላይ ጃንሆይ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት አዳሪ ተማሪዎችን ሲጎበኙ ምግብ ቤቱ ግድግዳ ላይ የአፄ ምኒልክና የእቴጌ ጣይቱን ምስል ተሰቅሎ ሲያዩ በንዴት “ይኸ እንዲነሳ!” ስላሉ ጃንሆይ እዚያው በመጎብኘት ላይ እያሉ የሁለቱ ምስል ተነስቶ የእሳቸውና የእቴጌ መነን ምስል ተሰቀለ። ይባስ ብሎ ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የተራው ሰው ልጆች በተፈሪ መኮንንና በቀኃሥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የመሳፍንትና የመኳንንት ልጆች ይገቡ ነበር። በዚህም ምክንያት በተፈሪ መኮንንና በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎችም መካከል በመጠኑ የመከፋፈል ሁኔታ ተነስቶ ነበር። ሠልፍ በሚወጡበት ወቅት የትምህርት ቤቶቹ የሙዚቃ ባንዶች የከበሮ (ታንቡር) አመታቶችን ትርጉም እየሰጡና እየተሰዳደቡበት ይተላለፉ ነበር። አልፈው ተርፈው የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪዎች የሚከተለውን ግጥም በየምክንያቱ በመድረክ ይዘምሩ ነበር።

ተፈሪ መኮንን ሐር ከሚያለብሰኝ
ዳግማዊ ምኒልክ ደበሎ ያልብሰኝ

ተማሪዎችም ላይ የነበረው አመለካከት አንድ ዓይነት ስላልነበረ በየምክንያቱ ለየትምህርት ቤቶቻቸው እየወገኑ ከሌላው ጋር ይደባደቡ ነበር። የባላባት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና የኮተቤ (ቀኃሥ) ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎቹ ስታዲዮም ላይ ተደባድበዋል። የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መጥተው በመደባደብ ተማሪ ሞቷል። የጄኔራል ውንጌትና የባላባት (መድኃኔ ዓለም) ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተደባድበው አንድ ልጅ ሞቷል።

የአፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥትን ለማሠራት በሥራ ሚኒስቴር በኩል ኢትዮጵያዊው አቶ አፈወርቅ ዮሐንስና እንግሊዛዊና፣ ስዊድናዊ መሃንዲሶች የቤተ መንግሥት ፕላን ሠርተው አቀረቡ። ውድና ቅምጥል ስለሆነና ሥራውንም ለመጨረስ ብዙ ጊዜ የሚወስድ ሆኖ ስለተገኘ በምትኩ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት በ1948 ዓ.ም በ20 ሚሊዮን ብር ተሠራ። ቤተ መንግሥቱ ላለመሠራቱ ሌላውና ትክክለኛ የሚመስለው



ምክንያት ግን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአፄ ምኒልክን ዝና ከፍ የሚያደርግ ሥራ እንዲሠራ ስለማይፈልጉ ነው እንጂ ሌላ ፕላን ተሠርቶ የምኒልክ ቤተ መንግሥት ሊታደስ ወይም በአዲስ መልክ ሊሠራ በተገባ ነበር።

አሌክሳንደር ፑሽኪን የተባለ ሩሲያዊ ባለቅኔ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ነበረው ስለተባለ የሁለቱን አገሮች ሕዝብ ያስተባብራል ተብሎ የሩሲያ የባህል ማዕከል እንደተሰየመለት ይታወቃል። አልፎ ተርፎም በቅርቡ ሐውልት እንደተሠራለት አይተናል። ፑሽኪን ከመወለድ ሌላ ለኢትዮጵያ ያደረገላት ነገር የለም። ነገር ግን ስንትና ስንት ለዚህች አገር የተሰውላትና ባለቅኔዎች እያሉ ለፑሽኪን ሐውልት መሠራቱ ትርጉሙ ምን እንደሆነ ግራ ያጋባል። የተመረጠውም አደባባይ ሌላ የራሱ ታሪክ ያለው ሲሆን ለብዙ ዓመታት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቅሎበት የቆየ ነው። በአጭሩ የፑሽኪን ሐውልት እንደ ሌኒን ሐውልት የሚያገነው ሩሲያን እንጂ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሐውልት የሚያስቆም ገድል ያለው አይመስልም።

ሌላው ለታላቁ የምኒልክ ቤተ መንግሥት የተደረገለት ነገር ቢኖር ዙሪያውን በብረት አጥር ቀኃሥ በሚል ምህጻረ ቃል መታጠሩ ብቻ ነው። ደርግ ቀኃሥ የምትለውን አርማ ለማፍረስና እንደገና በሌላ ለመተካት ብዙ ወጭ ስላስፈለገው አጋጣሚውን ሲጠብቅ ራሱ ወረደ። ቢያሠራው ኖሮ ማጭድና መዶሻ ምልክቱን ያደርግ ነበር ብሎ መገመት አያዳግትም። የሚያጠያይቀው ተከታዩ መንግሥት ማርክሲስት ካልኾነ እንደገና ያፈርሰው ነበር ወይስ ይተወዋል? የሚለው ነው።

አጼ ምኒልክ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ብልህ፣ ሥልጣኔ የሚወዱና ለሚቀጥለው ትውልድ የሚጠቅም ሥራ ለመሥራት የሚጥሩ ነበሩ። አፄ ምኒልክ ያቋቋሟቸውን አዳዲስ መሠረተ ልማቶች ማስፋፋትና ማደስ ሲገባ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ከእሳቸው በፊት ለተሠሩት ነገሮች እድሳትና መስፋፋት እንዲደረግላቸው ተገቢውን ትኩረት አይሰጧቸውም ነበር። በተለይ የአፄ ምኒልክን ሥራና ስም የያዘ ተቋም አይወደድም። በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት በአዳሪነት የሚማሩት ተማሪዎች እንኳን ከሌሎች ትምህርት ቤት አዳሪ ተማሪዎች በተለየ የሚሰፋላቸው ልብስ ኬንዳ ሲሆን የሚመገቡበት ሳህንና ሻይ የሚጠጡበት ጋቢጣ ኒኬል ነበር። ስለሆነም ብዙ ተማሪዎች ወደ ሌላ የመንግሥት ትምህርት ቤት መዛወርን ይመርጡ ነበር። እዚያ ትምህርት ቤት የተማሩ ተማሪዎቹም ብዙዎቹ ወታደርነት እየገቡ መኮንኖች በመሆን አገራቸውን ከማገልገላቸውም

ሊላ የጃንሆይንም መንግሥት ለመገልበጥ በሚደረገው ሙከራ ሁሉ ተሳትፈዋል። ከነዚህም መካከል እነ ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ፣ ኮሎኔል እምሩ ወንዴ፣ ኮሎኔል መልኬ ጌታሁን፣ ሻለቃ ያሬድ ቢተው፣ ኮሎኔል ሞላልኝ፣ ጀነራል ነጋ ተገኝ ይገኙበታል።

በተለይ በምኒልክ የተሠራውን የባቡር ሃዲድ መስመርና ሌሎችንም መሠረተ ልማቶች አስፋፍቶ እንደ መጠቀምና ለኢትዮጵያ ምጣኔ ሃብት ማጎልበቻ ማድረግ ሲቻል ያልታደሱና ያልተስፋፉበት ዋናው ምክንያት በራሳቸው በጃንሆይ ባለመጀመራቸው ብቻ ነው። ይህ የሚያመለክተው ለጃንሆይ የራሳቸው ዝና እንጂ የኢትዮጵያ ጥቅም ቀደሚያ እንዳልነበረው ነው።





# ምዕራፍ ፴

## ሙስና

ሙስና የግዕዝ ቃል ሲሆን ሁለት ትርጉም አለው። አንደኛው ጥፋት ማለት ሲሆን ሊላው ውበት ነው። ስለ ውበት የሚገልጸውን ለመገንዘብ ያህል የሚከተለውን ማጤን ነው።

የአንገቷ ንቅሳት የጥርሷ ሙስና
እሁድ ያስገድፋል እንኳን ሓሙስና

ቀደም ብሎ ሙስና በአማርኛ ንቅዘት (Corruption) እየተባለ ይጠቀስ ነበር። የሆነ ሆኖ አሁንም ሙስና ያው ጥፋት ወይም ንቅዘት የሚለውን ትርጉም የያዘ ነው።

ሙስና በማንኛውም የሥራ መደብ ላይ ያለ ሰው የሚፈጽመው ተገቢ ያልሆነና የማይጠበቅ ተግባር ነው። ሙስና ወይም ንቅዘት የመንግሥት ሠራተኞች በተለይ ባለሥልጣኖች የሚሰጣቸው አደራ ከፍ ያለ ስለ ኾነ ይህንኑ ኃላፊነት ለግል ጥቅም ብለው የሚፈጽሙት የማይጠበቅና መጥፎ ምግባር ይሆናል። ይኸውም መሥራት ያለባቸውን በለመፈጸም፣ ወይም በሚሠሩበት ወቅት ለሌላ ጥቅም ብለው በትክክል ሳይወጡ፣ ወይም ደግሞ ሥልጣናቸውን መከታ በማድረግ አጉል ተግባር አውቀውም ይሁን በቸልታ ሲፈጽሙ ነው። ለምሳሌ ጉቦ ተቀብለው አድሎአዊ ሥራ መሥራት፣ ወይም የመንግሥትን ገቢ ለራስ ማዋልና በሥልጣን መከታ አንድን ሰው ያለ አግባብ መበደል እንዲሁም ያለውዴታ ተቃራኒ ጾታን ለሩካቤ ሥጋ ማስገደድና የመሳሰሉት ናቸው።

ሙስና የተጀመረው በመንግሥት ሹመት አሰጣጥ ላይ ይመስላል። በንጉሠ ነገሥቱ ጊዜ ለሹመትም መታያ የሚከፈልና ተመንም

እንደነበረው ይወሳል። መታያ ጥቅም ለማግኘት የሚሰጥ እጅ መንሻ ማለት ነው። ለምሳሌ:

| | |
|---|---|
| ለወረዳ አስተዳዳሪነት ለመሾም | 3,000 ብር |
| ለአውራጃ አስተዳዳሪነት ለመሾም | 5,000 ብር |
| ለአገረ ገዥነት ለመሾም | 10,000 ብር |

በቤተ መንግሥት ራሱን የቻለ የመታያ ቢሮ እንደነበረ ይታወቃል። መታያ የሚሰጡ ሰዎች ሹመት ፈላጊዎች ካልሆኑ አንዳንድ ጊዜ ተጠርተው ምን እንደሚፈልጉ ይጠየቁና ጉዳያቸው ይፈጸምላቸው ነበር። አልፎ አልፎም መታያ የሚከፈለው ታማኝነትን ለማረጋገጥም ጭምር ነው።

ቀደም ብሎ አንድ አገረ ገዥ የሚያስገባው ግብር የራሱ ይሆንና እሱ ደግሞ በተራው ለዋናው ማዕከላዊ መንግሥት የሚጣልበትን ያስገባል። በተለያዩ አካባቢዎች የአገረ ገዥው የክብር መጠሪያ ንጉሥ ወይም ባላባት ወይም ማንኛውም የባህል ማዕረግ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመንግሥት የተሾመ ባለሌላ ማዕረግ ባለሥልጣን ነው።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት ሁሉ ገቢ ለመንግሥት ቀጥታ እንዲገባ ሲደረግ አገረ ገዥዎች ደሞዝ ተቆርጦላቸው እንዲያስተዳድሩ ይላኩ ነበር። በይፋ በደሞዝ ብቻ እንዲኖሩ ይደረግ እንጅ እነሱም በተራቸው ከደጀ ጠኚውም ከባለጉዳዩም ሁሉ መታያ መቀበሉን ቀጠሉበት። ስለሆነም ሕጋዊ ባልሆነ መልኩ ግን በይፋ የሚያስከፍሉት ጉቦ መሰል ንጥቂያ እንደነበረ ይታወቃል። አንዳንዶቹ ሹሞች ከመሻራቸው በፊት ቶሎ ለመክበር መታያውን እያበዙ ብዙዎችን ያጉላሉ ስለነበረ "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" የሚባል መጥፎ ባህል ሥር መስደድ ጀመረ።

ክቡር አቶ መኮንን ደስታ በጣም የተማሩና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ነበሩ። በውልደትም የጎጃሙ የደጃች ተድላ የልጅ ልጅ ናቸው። ከወረራው በኋላ የመጀመሪያው የትምህርት ሚኒስትር ነበሩ። ከእንግሊዞች ጋር በተደረገው ድርድር የፈርማው ዕለት ራስ ሆቴል ግብዣ ተደርጎ የእንግሊዙን መልዕክተኛ መጠጥ አወሳሰድ ተመልክተው ያዘጋጁትን ሌላ ውል በማስፈረም አገሪቱ ሳትወድ በተጽዕኖ ልትዋዋል የነበረውን በተቃራኒው እንዲሆን አድርገዋል እየተባለ ይወራላቸዋል። የወሊጋ አገረ ገዥ በነበሩበት ጊዜ የአዶላ



ወርቅ ሙሉ በሙሉ ወደ ቤተ መንግሥት ይገባ ነበርና በከፊል ወደ መንግሥት እንዲገባ ሲደረግ 75% በመቶው ለቤተ መንግሥት 25% በመቶ ለመንግሥት ሲባል አይቻልም ብለው ከለከሉ። በኋላ ቤተ መንግሥት ተጠርተው አስተምረን አስተምረን እኛ 75% ከመቶ እንዳንወስድ ታውካለህ እንዴ ብለው ጃንሆይ ሲቆጡ የለም "ወርቃዊው ስምዎ በወርቅ እንዳይጎድፍ በመቆርቆሬ ነው" ብለው ነገሩን አብርደው 50% ለመንግሥት 50% ለቤተ መንግሥት እንዲሆን ስምምነት ላይ ተደረሰ። ከዚህ ወቅት ጀምሮ ወርቁ ግማሹ ወደ ቤተ መንግሥት ግማሹ ወደ መንግሥት ግምጃ ቤት እዚያው የተመረተበት ቦታ ተከፋፍሎ ይላካል። ታዲያ አንዳንድ ጸሐፊዎች ስለወርቁ ጉዳይ ሲያትቱ ወደ መንግሥት ግምጃ ቤት ብቻ ስለገባው ያወሱና ነገሩን ይሸፋፍኑታል።

ሹሞች ምናልባት መታያ የሚቀበሉት ለመኖሪያ የሚከፈላቸው ደሞዝና ያሰባቸው የሥራ ጫና ከሚላኩበት ቦታ ርቀት አንጻር ተመጣጣኝ ስላልነበረና ልምድም እየሆነ ስለመጣ ነው። ከግዛት ግዛት የሚገኘው ጥቅም ይበላለጥ ነበር። ለምሳሌ ተወዳጅ የሆነ ሰው ከፋ ላይ ሲሾም ተወዳጅ ያልሆነ ሰው ግን ጋሞ ጎፋ ላይ ይሾም ነበር። ከፋ የቡና አገር ከመሆኑም በላይ ለም ስለሆነ ብዙ ጥቅም ሲገኝበት በተቃራኒው ጋሞ ጎፋ ሩቅና መንገድም ስላልነበረው ጥቅም የሚገኝበት አልነበረም። በተጨማሪም ባለሥልጣኖች የሚጋዙበት ቦታ ስለነበረ አንድ ሰው እዚያ ሲሾም እንደተወረወረ ያህል ይቆጥረው ነበር።

በሌላ መልኩ መታያ ወይም ጉቦ መቀበልና መስጠት በአንዳንድ አውራጃዎች የተለመደ ወግ ነበር። ለምሳሌ በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት አንድ አቶ ኃብተ አብ ባይሩ የሚባል የተማረ ወጣት ከፋ ውስጥ ቦንጋ አውራጃ ተሹሞ ጉቦ ባለመቀበሉ የአገሩ ሕዝብ ገንዘባችንን ካልወደደ እኛንም አይወደንም ማለት ነውና አንፈልገውም ስላሉ ተሸሯል።

ጃንሆይ በቀድሞው አሠራር መሠረት ሁሉም ገቢ ለንጉሠ ነገሥቱ፣ በየግዛቱ ያለውም ለአገረ ገዥው መሆኑ ቀርቶ ለመንግሥት እንዲሆን በማድረግ የአገሪቱን አስተዳደር ቅርጽ ለውጠዋል። ይህን ካደረጉ በኋላ መልሰው የግል ንብረትንና የመንግሥት ንብረትን በማደባለቅ በፍጹማዊ ሥልጣናቸው በሚሰጡት ትዕዛዝ የተመሰቃቀለ ሁኔታ ተፈጠሮ ነበር። ሲፈልጋቸው የመንግሥት ንብረት የሆነውን ለግለሰብ ይሰጣሉ፤ መልሰውም በመንግሥት ወጭ እንዲገዛ ያደርጋሉ። ስለግል

ንብረታቸው አስተዳደር ቤተርስት የሚባል ቢሮ ከፍተው እንዲሁም እያንዳንዱ ንጉሣዊ ቤተሰብ የቤተርስት ሹም እየሾመ የግል ንብረታቸውን ያስተዳድሩ ነበር። በመሆኑም ንጉሡ ነገሥቱ በሚሰጡት ትዕዛዝ የግልንም የመንግሥትንም ኃብት በአሠራር ያዙበት ስለነበረ የተዘበራረቀ ሁኔታ ተፈጠረ። የቤተርስት ሹሞችም በእነሱ የስም ከለላ ብዙ ጭቆና በግለሰቦች ላይ ያደርጉ ነበር። ይህም ሲደረግ የንጉሣውያን ቤተሰብም በስማቸው የሚነገድ መሆኑን የማያውቁበትም ወቅት ነበረ።

የግለሰብ ንብረቶችም በጫና ወደ ቤተርስትነት የገቡ ብዙ ናቸው። ለምሳሌ 44 ኮኖክ የሚያመርተው ድርጅት ጣምራ ባለቤቶች እነ በቀለ ሻቢ ተነጥቀዋል። አምቦ ውኃና ዞማልክ የተባሉት የለስላሳ መጠጥ ፋብሪካዎች የተፈሪ ሻረው ንብረት ነበሩ። ንብረቱን ለመውሰድ ሲባል ተፈሪ ሻረውን ያለፍላጎቱ የበጎ አድራጎት ዋና ሥራ አስኪያጅ ተደርጎ ተሾመ። ጉድለት ሊገኝበት ባለመቻሉ ወደ ስዊድን አምባሳደርነት ተሹሞ የንግድ ሥራውን ትቶ እንዲሄድ የተደረገው ይሄንኑ ሀብት ለመውረስ ነበር። ተፈሪ ሻረው ስዊድን አምባሳደር ሆኖ እያለ በ1953 ዓ.ም የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ሲደረግ ዕውቅና ሰጥቶ ስለተገኘ እሱም ስደተኛ ንብረቱም በበጎ አድራጎት እንዲጠቃለል ሆነ።

"አሳ ሲገማ ከጭንቅላቱ" እንደሚባለው የበላዮቻውን የሚመለከቱ የበታች ሹማምንቶች የመንግሥትን ንብረት በተቻላቸው ዘዴ ሁሉ ወደ ግል ይወስዱ ነበር። የመንግሥት ባለሥልጣኖቹ ያለባቸው ኃላፊነት አገሪቱን ከድህነት፣ ከድንቁርናና ኋላ ቀር ከሆነ አስተዳደር ማዳንና ማሻሻል ሲሆን እነሱ ግን ሥራቸው ሁሉ የግል ጥቅም ላይ ያተኮረ በመሆኑ በሁለት ዙር ሊያስጨፈጭፋቸው ችሏል። አንደኛው ዙር በእነ መንግሥቱ ንዋይ ያልተሳካ የመንግሥት ግልበጣ ወቅት ሲሆን ሁለተኛው ዙር ደግሞ በእነ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የመንግሥት ለውጥ ጊዜ መሆኑ ነው። በንጽጽር በ1911 ዓ.ም ከብረው የተገኙትና የተሻሩት ሚኒስትሮች ዕድለኞች ነበሩ ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም ተሻሩ እንጂ ሃብታቸው አልተወረሰም፣ እነሱም እንደ ቅርብ ጊዜ ሚኒስትሮች ሕይወታቸው አደጋ ላይ አልወደቀም።

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት በሥራ ላይ የነበሩ ከተራ ሠራተኛ ጀምሮ ለጉርሻና ለጉቦ ሲሉ ተገልጋዩን ማጉላላት ጀምረው ነበር። በተለይ እንደ ጉምሩክ ባሉ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ ሰዎች ከሌላው



የመንግሥት ሠራተኞች ይበልጥ ይወራባቸው ነበር። ሌላው እንደ ፈቃድ መስጠት ዓይነት አገልግሎቶች የሚሰጡ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ያሉ ባለሥልጣኖች ሕግ እየጣሱ በጉቦ ፈቃዱን ይሸጡ ነበር። ችግሩ መጀመሪያ ላይ ይሾሙ የነበሩት ባለሥልጣኖች ባለውለታዎች ስለነበሩ ከአንዱ መሥሪያ ቤት ሲሻሩ ሌላ መሥሪያ ቤት ስለሚሾሙ እነሱን ያጋለጠ የመንግሥት ሠራተኛ እንደ በጥባጭ ይቆጠርና ይጉላላ ነበር። በዚህ የታወቁትና ብዙ ባለሥልጣኖችን ንጉሡ ዘንድ እየከሰሱና እየረቱ እንዲሻሩ ያደርጉ የነበሩት አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ ነበሩ።

ከዚህም ሌላ ባለሥልጣኖቹ ትምህርት ያንሳቸው ስለነበረ አሠራራቸው ግልጽነት አልነበረውም። ከሥልጣናቸው በላይ እርምጃ ይወስዳሉ፣ ዘመዶቻቸውን ቁልፍ ቦታ ላይ አስቀምጠው የመሥሪያ ቤቶችን ገቢ ለራሳቸው ያደርጋሉ። በዚህ ላይ በየመሥሪያ ቤቱ ያሉት እንደ እነሱ ዓይነት ስለሆኑ የአንዱ ጠላት የሁሉም ጠላት ስለሚሆን የመንግሥት ሠራተኛውን በብዛት በክለውታል። በኋላ ላይ የተማሩ ሚኒስትሮች ቦታውን እየያዙ አንዳንድ መሻሻል ቢያደርጉም የሙስናው ደረጃ ግን እምብዛም ባለመቀነሱ የመንግሥት አሠራር ሊስተካከል አልቻለም።

ከነበረው ሙስና አንዱ ዘረኝነትም ሲሆን በሥልጣናቸው መከታ ያለይሉኝታ ዘረኛነትን ያራመዱ ከነበሩት መካከል የሚከተሉት ያደረጉትን እንመልከት። አቶ ይልማ ዴሬሳ ለአየር ኃይል የሚመለምሉት በብዛት ከወለጋ ብቻ ነው ተብሎ በሰፊው ይወራባቸው ነበር። በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ አቶ ዮሐንስ እስጢፋኖስ ኤርትራውያኖችን ብቻ በመቅጠር የጎሣ አለመግባባት ለመፍጠር ችለዋል። ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁም ለፀጥታ ሠራተኛነት ጎንደሬዎች" ብቻ በመቅጠሩ ተወንጅሎ ምክንያት በማቅረቡ በግሳጼ ታልፏል። የትምህርት ምክትል ሚኒስትር የነበሩት ዶክተር መንገሻ ገብረ ሕይወት ወደ ውጭ አገር የሚሄዱትን ተማሪዎች ሲመርጡ የትግርኛ ተናጋሪዎችን ብቻ በመምረጣቸው ተወቅሰው ከሥልጣናቸው ወርደዋል። የሚቀርቧቸው ሰዎች "ለምን እንዲህ ይኾናል?" ብለው ሲያነጋግሯቸው "እኔ እዚህ ቦታ ላይ እስካለሁ ድረስ ለስኮላርሽፕ የሚላኩት ትግርኛ ተናጋሪዎች ብቻ ናቸው!" ብለው ያለ ይሉኝታ ተናገሩ ይባላል። ከተማረ ሰው እንዲህ ዓይነት አመለካከት ባልተሰነዘረ ደግ ነበር። እኚሁ ዶክተር መንገሻ ካስቀሯቸውና በኋላ ተጨቃጭቀው ሆላንድ አገር ሄደውና ተምረው ከተመለሱት አንዱ ዶክተር አዳሙ ዋቅጅራ አሁንም በሕይወት

ይገኛሉ። የጎማን ስሜት በመፍጠርና በማጋነን የተማሩ ሰዎች ያደርጉት የነበረው መሠሪ ተግባር ለቀጣዩ ትውልድ ጠንቅ ይሆናል እንጂ መጨረሻ ላይ ማንንም እንደማይጠቅም የታወቀ ነው።

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ላይ የነበሩት ጄኔራሎችም ውትድርናውን ረስተው የእርሻ መኪና ሲገዙና ሲያስጠግኑ እርሻቸውን ሲጎበኙና ስለእርሻ ጉዳይ ሲራወጡ ለሚመለከታቸው ያስገርሙ ነበር። በመንግሥት ሄሊኮፕተርና መኪና እንዲሁም በመንግሥት ነዳጅ ለግላቸው ጉዳይ እየተጠቀሙ እንደሠሩ ሁሉ ደሞዝ ቢከፈላቸውም ውሏቸው ግን እርሻቸው ላይ ነበር። አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ያልሠራበትን ክፈሉኝ ካለ ወይም በሥራ ሰዓት ቁጭ ብሎ ውሎ በትርፍ ሰዓት ብቻ ልሥራ ሲል ሙስና ነው። በመንግሥት ቴሌፎን እንኳን የግል ጥሪ ካደረገ ሙስና ነው። የመንግሥት ገንዘብ የሕዝብ ገንዘብ ስለሆነ ሁሉም ሰው በተለይ የመንግሥት አደራ የተጣለባቸው እንዳይባክን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።

ዳኛ መሆን ካለበት አበሳ አንዱ፣ የተረታው ሁሉ ጉቦ በልቶ ይሆናል! ብሎ በዳኛ ላይ ማጉረምረሙ ሲሆን በተለይ ይህ ሃሜት ደግሞ ከደካማ ሰዎች እየተደጋገመ የሚሰማ ነው። ዕውነት ጉቦ በልቶ ዳኛ አለአግባብ ከፈረደ ከዚህ የባሰ ሐጢያት ያለ አይመስልም። ሆኖም አልፎ አልፎ ሐጢያተኛ ይጠፋል ማለት ደግሞ አይቻልም።

ሙስና በተለይም በመንግሥት ሠራተኞችና ባለሥልጣኖች ዘንድ ሲስፋፋ የሚያሳዩዋቸው ብዙ ምልክቶች አሉ። እነዚህም

| | |
|---|---|
| 1 | ከበላይ ያሉት ራሳቸው በሙስና ሲዘፈቁ ከበታች ያሉት ተስፋ በመቁረጥ እኛም ፋንታችንን እንውሰድ በማለት፣ |
| | |
| 2 | ያለው መንግሥት ዘላቂነት አጠራጣሪ ሲሆን ከሥልጣናችን ከመነሳታችን በፊት እንዝረፍ የሚል አስተሳሰብ በባለሥልጣኖች ሲሰርፅ፣ |
| | |
| 3 | መንግሥት ቀረጥና ቁጥጥር ሲያበዛ ፍትሕ ሲያጓድል ሕዝቡ ከጫናው ለመዳን ባለሥልጣኖችን ለመሸንገል እንደ አማራጭ መጠቀም ሲጀምር፣ |
| | |
| 4 | የመንግሥት ሠራተኞች ዝቢያቸው አንሶ የዕለት ኑሯቸውን ለማሸነፍ በሚያደርጉት ትግል የሚያስከፍሉት ተጨማሪ ክፍያ ስለሚሆን፣ |
| | |
| 5 | የመንግሥት ሠራተኞች ለመሾምና ወደ ከፍተኛ ዕድገት ለመድረስ |



| | |
|---|---|
| | በሥራ፣ በአገልግሎትና ችሎታ ሳይሆን በወገን፣ በጎሣ፣ በተወላጅነት፣ በዝምድናና በጋብቻ መሆኑን ሲያምኑበት፣ |
| | |
| 6 | ጡረታ በሚወጡበት ወቅት የጡረታ ክፍያቸው የመግዛት ኃይሉ ስለሚሸረሸርና ዝቢያቸው ስለማይበቃቸው ጉልበት ባላቸው ጊዜ የተቻላቸውን ሃብት ለማጋበስ፣ |
| | |
| 7 | መንግሥት የሥልጣን ጊዜውን ለማራዘምና ደጋፊዎቹን ከሥልጣናቸው በላይ ሲሠሩና ጉቦ ሲቀበሉ ሌላው ሠራተኛ ሲመለከት |

በጥቅሉ ሙስና የሠላም ዘመን ዘረፋ ከመሆኑም በላይ በተለያዩ ሁኔታዎች ሊስፋፋ፣ ሥር ሊሰድ የሚችል አገርን የሚያቀጭጭና ብሔራዊ ክብርንም የሚነካ በሽታ ነው።



# ምዕራፍ ፴፩

## መሠረተ ልማት

ጥንት ያልነበረ ዘመናዊ ህክምናና ክትባት በአገሪቱ እየተስፋፋ ሲሄድና ሰውም እየተማረ ራሱን መጠበቅ ሲጀምር የሕዝብ ቁጥር እንደሚጨምር ግልጽ ነው። የቁሳቁስ ፍላጎትም ሰው እየሠለጠነ ሲሄድ በዛው ልክ ይጨምራል። ቢያንስ ያለጫማ አይሄድም፣ ለምሳሌ የአዲስ አበባ ነዋሪ ውስጥ በባዶ እግር የሚሄድ መገኘት ያቆመው ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ ነው። ስለሆነም ከአዲስ አበባ ነዋሪ መካከል አብዛኛውን የመንጠቆ ትል (HOOK WORM) አይዘውም። የሽንት ቤትና የአካባቢ ጽዳት ተሟልቶ ቢሆን ኖሮ በሽታው የሚይዘው ሰው ጨርሶም አይገኝም ነበር። የጥርስ መፋቂያ መጠቀም ትቶ ብሩሽና ሳሙና ይፈልጋል፣ ጥሩ ለመልበስና ለመመገብ ይጥራል፣ እስከተቻለ ድረስ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ የተመቻቸ ሁኔታዎችን ለማግኘት ይሯሯጣል።

በ1950ዎቹ ዓመታት አንድ ሰው ሚስት ሲያገባ ዛሬ መኪና እንደሚዋሰው ያኔ ሰዓት ይዋስ ነበር። በ1990ዎቹ ዓመታት ሰዓት የሌለው ሰው በከተማ ውስጥ ቢኖርም ቁጥሩ ጥቂት ነው። ታዲያ አገሪቱ የተማሩ ልጆች እያፈራች ስትሄድ ሌሎችም የተመጣጠኑ የግንባታና የምርት ብዛት ስለሚያስፈልጋት መንግሥት የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር የራሱን ኃላፊነት መወጣት ይገባዋል።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ውስጥ በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን በመጠኑም ይሁን እንጂ ብዙ ነገር ተሞክሯል። ግን ዘለቄታ ያለውና ለመሠረተ ልማት የሚረዱ ነገሮች ላይ የገንዘብ ወጪ ተደርጎ የሕዝቡን ኑሮ የሚያሻሽል ሥራ አልተሠራም። ስታሊን ከአምስት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ፈጅቶ ለአገሩ ግን ጠቃሚ የሆኑ የመሠረተ ልማት ተቋሞች ትቶ ስለሄደ ያን ያህል አልተጠላም። በማለቱ ፍኩ ሀገር ያሳቋረጠ ክንፉ ል መሬ ሪማ —



ነበረበት። ከሁሉም የሚያሳዝነው ደግሞ በውዳሴ ከንቱ የዚህች የድሃ አገር ገንዘብ እየባከነ ከድህነት አውጥቶ በኤኮኖሚ ሊያቆናጥጣት የሚችል ሥራ አለመሠራቱ ነው።

በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከ**19000** ሰው በላይ አልቆበት ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ የተዘረጋው የባቡር አገልግሎት በጃንሆይ **58** ዓመት ሥልጣን ጊዜ እንኳን ተስፋፍቶ አገሩን ሊያዳርስ ቀርቶ የሚሰጠውም አገልግሎት ከዓመት ዓመት እያዘቀዘቀ በመሄዱ ሊጠቅም የሚገባውን ያህል አገልግሎት ለአገሪቱ አልሰጠም። የባቡር ሃዲዱ አቃቂ ደርሶ ስለነበረ ጃንሆይ ያደረጉለት ነገር ቢኖር ከአቃቂ እስከ ለገሃር 12 ኪሎ ሜትር ማስረዘማቸው ብቻ ነበር። አፄ ምኒልክ ባቡሩን ከአዲስ አበባ እስከ ነገሌ፣ ወሊጋና ጅማ ለማገናኘት ያቀዱት ሃሳብ ቀርቶ አንዴ ወደ አሰብ ሌላ ጊዜ ወደ አዋሳ ይዘረጋል እየተባለ በወሬ ቀረ። አዲስ አበባም ውስጥ ቢስፋፋ ኖሮ ለከተማው ሰው መጓጓዣ ያገለግል ነበር። አሜሪካና ህንድ በባቡር ምን ያህል ሥልጣኔያቸው ወደፊት እንደገፋ መመልከቱ ጥሩ ነው። የዓለም ሰዓት በሥርዓት ውሳኔ አግኝቶ ሥራ ላይ የዋለው በባቡር ምክንያት ነው።

ስልጣኔን ያመጣሁት እኔ ነኝ ለማለት ካልተፈለገ በስተቀር የቀደመው መሪ የጀመረውን ቀጣዩ ካልጨረሰውና መሪ በተለዋወጠ ቁጥር የነበረውን አፈራርሶ የራሱን ሌላ አዲስ መገንባት ከኾነ ተጎጂው ሕዝብና አገሪቷ መሆኗ ነው።

ሕግና ደንብ በማውጣት እንኳን ከብዙ ችግር መላቀቅ ይቻል ነበር። መሬትን በስፋት መያዙን የአገር መሪዎች ሁሉ ለሥልጣናቸው መቆያ ስላደርጉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍዳውን ያየበት ነገር ነው። ደርግ እንኳን መሬት ወርሶ ሕዝቡን ጭሰኛ አደረገ እንጅ ለሕዝብ አላከፋፈለም። የሕዝቡ ጥያቄ መሬት ለአራሹ እንጂ መሬት ለመንግሥት አልነበረም።

እርግጥ የመሬት ይዞታ ተስተካክሎ ቢሆን ኖሮ አብዛኛው ሕዝብ የምርት ውጤቱ አድጎ የኢኮኖሚ መሻሻልና እመርታ በታየ ነበር። ሆኖም ከሕዝቡ 85% ገበሬ ሆኖ ከሁለት ሺ ዓመት በፊት በሚታረስበት ዘዴ በበሬ ከማረስ ባለመላቀቁ የትም አይደረስም። ስለሆነም ብዙ ሥራ የሚከፈትበት ሁኔታ መመቻቸት ነበረበት። በአደጉት አገሮች ከሕዝቡ ከ2% እስከ 5% ብቻ እያረሠ አገሩን ሁሉ አጥግቦ ወደ ውጭ መሸጥ ችሏል።

የከብት ርባታም ቢሆን በየቤቱ የሚረባው አመርቂ ካለመሆኑም በላይ የአፈር መሸረሸርን ያበረታታል። ስለ እርሻ ከተነሳም ዝናብ ጠብቆ በሰፊው ለማረስ ስለማይቻል በመንግሥት ጥረት ግድቦችና የመስኖ ልማት መስፋፋት ነበረበት። በርካታ ኢንጂኔሮች ያስተማረው የኢትዮጵያ ገበሬ አሁንም የሚያርሰው በፊት በለመደው በጥንቱ ሞፈርና ቀንበር ነው።

በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት 40% ያህሉ በደን የተሸፈነ ኾኖ እያለ ከአውስትራልያ ባሕር ዛፍ አስመጥተው ተክለዋል። ሆኖም አሁን ወደ 3% ያህሉ ስለቀረና የሰሃራ በረሐም እየሰፋ ስለመጣ በርትቶ ዛፍ እንደመትከል ፈንታ ሥራሽ ለማውደም ርብርቦሽ ይደረጋል። በየአሥር ዓመት ይደጋገም የነበረው ድርቅ በየሦስትና አራት ዓመት እየተመላለሰ ስለመጣ አገሪቱ ለሰው መኖሪያ ተስማሚነቷ እየቀነሰ ነው። በቀኃሥ የመጨረሻ ዘመን ሚኒስትሮችና መኳንንቶች የዛፍ ደን እየተሰጣቸውና እየቆረጡ ሸጠው ባለገንዘብ መሆን ጀምረው ነበር። በተለይ በአርሲ የተደረገው የደን ሥፍጨፋ የሚያስተዛዝብ ነበር። ደርግ ደግሞ ሥልጣን ሲይዝ ካድሬዎቹ ዛፉን ጨፍጭፈው በገንዘቡ ፈነጠዙበትና አገሪቱ አረንጓዴ መሆንዋ ቀርቶ ቢጫ መሆን ጀመረች። በኋላ ለይምሰል በአዲስ አበባ እንጦጦና የካ ጋራዎች ላይ ተማሪን ሰብስበው ዛፍ እንዲተክሉ ሲያስገድዱ ተማሪዎቹ ደግሞ ችግኙን በመዘቅዘቅ እየተከሉ ሲቀልዱ ከርመዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፊደላችንን ለብዙ ዘመን ጠብቃ እንደኖረችው ሁሉ አሁንም በየአድባራቱና በየገዳሙ ዛፎቻችንን በመጠበቅ አስተዋጽኦ እያደረገች ትገኛለች። ይሁን እንጂ ከዚያው ጎን ለጎን ሌሎችም ጥፋቶች እየተስተዋሉ ነው። ለምሳሌ በ1994 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቅርሳ ቅርስ ባለ አደራ ጽሕፈት ቤት እንጦጦ ማርያም አጠገብ የሚገኙትን ዛፎች በመሸጥ ዛፉን ሁሉ አስቆርጦ በምትኩ እንዲተከል አላደረገም። በመሃሉ አፄ ምኒልክ በመጀመሪያ እንጦጦ ላይ የተከሉትን አምስት ዛፎች የቆረጠው ማን እንደሆነ አልታወቀም። እንዲሁም ቀራንዮ የነበረው በንጉሥ ኃይለ ሥላሴ የተተከለው ዛፍም ተቆርጦ ጉቶው ብቻ ቀርቷል።

የአዲስ አበባ ነዋሪ ከዋናው ቤቱ ይበልጥ ለአጥር ያለው ስሜት (Fence Mentality) ትልቅ ነው። አጥሩ ሦስት ሜትር ርዝመት ላይ ከመድረሱም በላይ፣ ጥድ፣ አጋምና ኮሽም እየተከለ መንገድ



ከማጣበቡም ባሻገር በግቢው የሚበላ ፍሬ የሚሰጥ ወይም የደን መመናመንን ለመግታት የሚያግዝ ዛፍ ሲተክል አይታይም። በአሁን ጊዜ የሚሠሩት የአጥር በሮች ከከባድነታቸው ሌላ ቁመታቸው ከሦስት ሜትር ይበልጣል። ፋሽን እየሆነም ስለመጣ አሥሩን አሮጌ በር እየለወጡ በአዲሱና በረጅሙ በር በመተካታቸው ከተማው ስፊ እስር ቤት ከመምሰሉም በላይ እንደ መካከለኛ ምስራቅ አገሮች ኋላ ቀርነታችንን ያሳያል። አጥር ለክፉ ቀን ከምንም እንደማያስጥል በቀይ ሽብር ዘመን ታይቷል። ቀደም ብሎ የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የአጥር ቁመት ከ25 እስከ 50 ሳንቲ ሜትር እንዲሆን የውስጥ ደንብ ነበረው። የራሱን የግቢ አጥር ግን ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ በብረት አሳድጎታል።

ከአገልግሎት አውታር መንገድን በተመለከተ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጣሊያን በአምስት ዓመት የወረራ ዘመን የሠራቸው መንገዶች ደረጃውን ባልጠበቀ እድሳት ብቻ አገልግሎታቸውን ሲቀጥሉ ዘላቂነት ያለው የመንገድ ሥራ አልተሠራም። የአውራ ጎዳና ባለሥልጣን ድርጅት ለነዚህ መንገዶች የጥገና ሥራ ያፈሰሰው ገንዘብና የሥራው ውጤት አይመጣጠንም። ያስመጣቸውንም መሣሪያዎች በዘዴ የተገለገለባቸው አይመስልም። ለዚህም ዋናው ምክንያቱም መጋዘን አጣብበው ሊቀመጡ ባልተገባም ነበር የሚለው ግምት ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ ከጣሊያን ወረራ በኋላ ኤኮኖሚውን የሚያሻሽል ምንም አመርቂ ሥራ ባለመሠራቱ ተምሮ ለሥራ የተዘጋጀው ኃይል ሥራ ፈት እየሆነ አገሪቱ ከቅኝ ግዛት በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ዓመታት ነጻ የወጡት የአፍሪካ አገሮች እየበለጧት ሲሄዱ ያለፈን ታሪክ ብቻ እያወሩ በመኮፈስ ጊዜ ተቃጠለ። ታሪክ ያለው ሕዝብ ሥነ ልቦናው ከፍ ያለ መሆኑ አያጠራጥርም። ልንኩራበትም ይገባል። ግን እየተራብንና በአሁኑ ዘመን ያለነው እንደበፊተኞቹ አባቶቻችን ጠንክረን ሳንሠራ በመናችንን ማሳለፍ አይገባም። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ሄደው ለጃንሆይ "ከአፍሪካ አገሮች በሥልጣኔ ወደ ኋላ ቀረን" ብለው አቤት ሲሉ ጃንሆይ "ኢትዮጵያን ማወዳደር ያለባችሁ ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ጋር ነው" ብለው ሲናገሩ ተማሪዎቹ በነገሩ ስቀው ተመለሱ። ይኸ የሚያሳየው በገዥውና በተገዥው መካከል ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነት ነበር።

ቀደም ብለን ቀዋሚ ሥራ ባለመሥራታችን ዛሬ ልጆቻችን በየዓረቡ አገር ለግርድናና ለአሽከርነት ለመሄድ በሚያደርጉት ጥረት የተሳካላቸው

እንኳን እንደ ትልቅ ዕድል ይቆጥሩታል። አንድ ግፌኛ ወላጅ 'አንድ ልጅ ውጭ አገር መላክ ማለት አንድ ከባድ የጭነት መኪና ከነተሳቢው እንደመግዛት ይቆጠራል!' አለ ይባላል። አገራችንን እናገለግላለን እያሉ የተማሩት ኢትዮጵያውያን በምዕራብ አገሮች የረባ ሥራ የሚሰጣቸው እያጡ ዶክተር ሆነው በዘበኝነትና በታክሲ ነጅነት እየኖሩ ያስተማረቻቸውን አገር ለማገልገል ዕድል ሳያገኙ ዕድሜያቸው እያለፈ ነው።

በጠቅላላው የሕዝቡን ድህነትና የከተማዎቹን አሠራር፣ የባላገሩን ሕዝብ አኗኗር ለሚመለከተው ሰው እንዲያውም ራሳችንን ማስተዳደር ያዳገተን መስሎ ይታያል። የባለሥልጣኖች ችላ ባይነት፣ የነገሮች መዘበራረቅና መቆላለፍ፣ አተኩሮ ለተመለከተው ያሳፍራል። የቢሮክራሲው ቀይ ጥብጣብ (Bureaucratic red tape) መጠላለፍ ሥራ ለመሥራት ትልቅ እንቅፋት መሆኑ እየታየ ልክ እንደ ትክክል ነገር መታለፉ የሚገርም ነው። ብዙ ሰዎች በንግግራቸው መካከል "ጣሊያን ሌላ አሥር ዓመት በቆየ ደግ ነበር" እያሉ ይቆጫሉ። ለዚህ ትውልድ ባይሳካለትም በግድም ሆነ በውድ ስልጣኔው ላይ መድረሱ አይቀርም። የቅኝ ተገዥ መሆን ሥነ ልቡና ላይ የሚተወው ጠባሳ የማይሽር ስለሚሆን እንኳን በአምስት ዓመት መወረር ብቻ ተወጣነው።

ሌላው ትልቁ ነገር ባለፉት መንግሥታት አስተዳደር ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞች አስተሳሰብ አዎንታዊ መሆን ሲገባው አሉታዊ መሆኑ ነው። ይህንን ሥር የሰደደ አመለካከት ለመቋቋም "አይቻልም" ከማለት "ይቻላል" ብሎ ነገርን በቀና ለመመልከት እንዲበረታቱ አቶ ከቡር ገና የንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዴንት በነበሩበት ወቅት "ይቻላል" የሚል አርማ አንስተው ነበር።

ይህ ከሆነ ዘንዳ የመንግሥት ሠራተኞች ለምን ይቻላል ብለው ነገርን ለመመልከት ይሳናቸዋል ብሎ ለጠየቀ ሰው ሁለት መልስ አፌቱ ድቅን ይላል። አንደኛው ሙስና ሲሆን ሁለተኛው የችሎታ ማነስና የመወሰን ሥልጣን እጦት ነው። ሙስና የሚሆነው ሕዝቡን በማስቸገር ጉቦ ለመጠየቅ ያለ ፍላጎት ሲመስል ሁለተኛው ደግሞ በራሳቸው ላይ ዕምነት ማጣት ነው። ሌላው ምናልባት መንግሥትን ገዝግዞ ለመጣል የሚደረግ ሙከራም ሊሆን ይችላል። ሁል ጊዜ በዚህ ዓይነት የሚሠራ ከሆነ ጊዜ ስለሚፈጅ አገሪቷ ትቀጭጫለች። አላወቁ እንደሆን ነው እንጂ አገሪቷ ብትዳብር ራሱ በፖለቲካውም መሻሻልን በውዴታ ሳይሆን በግዴታ ያመጣል። ቀና ላልሆነ መንግሥትማ ሕዝብ ሳይሻሻል እጆቹን አጣጥፎ



ቁጭ ቢል ለመግዛት ይመቸዋል። አገርንም እየተወ ቢሄድ ምንግዱ! የቀረው ይበቃዋል። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት አማራና ትግሬ በኋላ ቀርነት እንዳሉ እንዲቆዩ የተደረገው የቤተ መንግሥቱ ተቆርቋሪና ጠባቂ ሆነው እንዲያገለግሉ ጭምር ነበር።



የትራፊክ መብራት በኤሌክትሪክ ምሰሶ ተክለው ሲታይ

ስለ መንግሥት ሥራ አመራር ግድ የለሽነትና የብክነት ሥራን በግልጽ ከሚያሳዩ በርካታ ምሳሌዎች አንዱ በሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ያለው የትራፊክ መብራት ነው። የትራፊኩን መብራት ከፊቱ የስልክ እንጨት ተተክሎበት እንደሚጋርደው ለተመለከተ ሰው 'መብራቱ ነው ወይስ የስልክ እንጨቱ መጀመሪያ የተተከለው?' ብሎ ይጠይቃል። በኋላ የተተከለውን ስንመለከት ምን ዓይነት ሰው እንደተከለው ለመገመት ያስቸግራል።

በአጠቃላይ የመንግሥትን ሁኔታ ለመረዳት አዲስ አበባን በመመልከት ብዙ መረዳተ የቻላል። በተለይ አዲስ አበባ ለኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የባህል፣ የንግድ፣ የመገናኛ ማዕከል ስለሆነች አዲስ አበባ ቁጥር ብሎ ስለጠቅላላው አገር ብዙ መረዳት ይቻላል። አዲስ አበባን ብቻ በመመልከት አገሪቷ ራዕይ እንደሌላት እንረዳለን።

## የአዲስ አበባ ከተማ አመራር

የመጀመሪያው የአዲስ አበባና የጎንደር ከተሞች ከንቲባ ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ጎሹ በ1901 ዓ.ም የአዲስ አበባ ማኅበር የሚባለው እንደተቋቋመ ማስተዳደር ጀመሩ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ በ1912 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ሆነው ሲሾሙ ስሙን የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አሉት። ማዘጋጃቤት ለሚለው ቃል በእንግሊዝኛ የሰጠነው ትርጉም ሚዩኒሲፓሊቲ (Municipality) የሚለውን ነው። በመሠረቱ ሚዩኒሲፓሊቲ ማለት ራስ ገዝ የሆነ ከተማ ወይም ማኅበረ ሰብ ማለት ነው። ሚዩኒሴፕ ደግሞ የሚዩኒሲፓሊቲ ነዋሪ ማለት ነው። ዋናው አስተዳዳሪም ከንቲባ (Mayor) የሚባል ማዕረግ ይኖረዋል። የከንቲባነት ማዕረግ የከተማውን ክብር ከፍ የሚያደርግ ስለነበረ የከንቲባዎች ልዩ ልብስም ነበር። በተለይ ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ልብሳቸውን ለብሰው የከተማውን ቁልፍ ለክብር እንግዶች ሲያበረክቱ ያኮሩ ነበር።

ከ1942 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ አበባ የዓለም ከተሞች ማኅበር አባል ነበረች። በዚህም ምክንያት ከተማዋ በቻርተር የምትተዳደር በመሆኗ ከንቲባዎቹ በየዓመቱ በሚደረገው የዓለም አቀፍ ከተሞች ስብሰባ ላይ ይገኙ ነበር። ከተማው የሚተዳደርበት ቻርተር ስለነበረው የከተማው ምክር ቤት በሕዝብ ተመርጦ ምክር ቤቱ በተራው ሦስት ዕጩ ከንቲባዎች ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀርብና ጃንሆይ አንዱን መርጠው ይሾማሉ ይላል። ይሁንና ይህ አሠራር ተፈጻሚነት ነበረው ይባል እንጂ በዘመኑ ጃንሆይ ከመጠን በላይ ይፈሩ ስለነበረ እሳቸው የፈለጉትን ይሾሙና ይሽሩ ነበር እንጂ ዴሞክራሲው በጋዜጣ ለሕዝብ ከመደሰየት አልፎ ተፈጻሚነት አልነበረውም። አንዱ ባለሥልጣን ከሌላ የመንግሥት ሥልጣን ላይ ተነስቶ ሲሾም በፈለጉት ሰዓት ደግሞ በቦታው የነበረውን ከንቲባ ሌላ ሹመት ሰጥተው ያነሱታል። •





ከንቲባ ዘውዴ ገብረሕይወት

ከጠላት ወረራ በኋላ ደጃች ውቤ መኖሪያ ቤት ውስጥ እንደገና የተቋቋመው የማዘጋጃ ቤት ባለመታደል በነቀዘ አስተዳደር የተደቆሰ ቤት ነበር። ከመነሻው በብዛት የቤተ ክህነት ሰዎች፣ በደርግ ጊዜ ካድሬ የሞላበት ሲሆን በሹመት ከተመደቡት ከንቲባዎች መካከል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት የነበሩት ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሥላሴ ዕቅዶችን በማዘጋጀት፣ ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ቋሚ ሥራዎችን በመሥራት፣ ከንቲባ ዶክተር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ ለከተማው የእግር መንገዶች አቅድ በመስጠት፣ ከንቲባ ዘውዴ ተክሉ ከተማው ውስጥ መሠረተ ልማትን በማቋቋምና በማሠራጨት ይታወቃሉ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዘውዴዎች በተደጋጋሚ የከንቲባነት ሹመት አግኝተዋል። ከሌሎችም ከንቲባዎች የሚታይ ሥራ የሠሩት ዘውዴዎቹ ነበሩ። እዚህ ላይ ሊታወስ የሚገባ ነገር ቢኖር አሁን

በመሠራት ላይ ያለውን የቀለበት መንገድ ያቀዱት ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሥላሴ እንደ ነበሩ ይታወቃል።



ከንቲባ ዶ/ር ኃ/ጊዮርጊስ ወርቅነህና ባለቤታቸው ዶ/ር ጀምበር

ለመወደድ ሲል ደርግ በጊዜያዊነት በነጭ ሊስት እየፈረሙ ይሠሩ የነበሩትን ጊዜያዊ ሠራተኞችን በጅምላ ቋሚ ሠራተኞች አደረገ። ዕድሜያቸው ከ55 እስከ 85 ዓመት የነበሩ ሁሉ አነስተኛ ዕድሜ በማስመዝገብ ስለተቀጠሩ በሥራው ላይ ከፍተኛ በደል አድርሰዋል። ለምሳሌ በወረዳ 5 የጽዳት ዘበኛ የነበሩት በ1975 ዓ.ም ወደ ቤታቸው ሲሄዱ ወድቀው በመሞታቸው ዕድሜያቸው 83 ዓመት መሆኑ ታወቀ። ዳሩ ግን በመሥሪያ ቤቱ ፋይል ውስጥ የተመዘገበው ዕድሜያቸው 48 ዓመት ነበር። እንዲሁም በወረዳ 2 የአራዳ አትክልተኛ የነበሩት ዕደሜያቸው 78 ዓመት የሆነው አጭሩና ጎበጥ ያሉ የነበሩት ያስመዘገቡት ዕድሜያቸው 52 ዓመት ሆኖ በሥራ ላይ



ሞተዋል። የማዘጋጃ ቤት አትክልተኞችና ተላላኪዎች በዚህ መልኩ በመሠማራት አዛኝ ቅቤ አንጓች የነበረው ደርግ የሥራ ዲሲፒሊን በአገሪቱ እንዳይኖርና አስመሳይ ካድሬዎቹን እየሰገሰገ የአገሪቱን ዕድገት አወላገደው። አስተዳደሩ ለአዲሱ ተቀጣሪዎች የደንብ ልብስ ሲያሰፋና ስለፖለቲካ ውይይት ሲያደርግ ኖረ እንጂ ምንአልባትም ለከተማው ከአብዮት አደባባይ በስተቀር ጠቃሚ ሥራ አልሠራም።



ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሥላሴ በከንቲባ ልብስ ከሚኒስትሮች ጋር ሆነው ጃንሆይን ሲጠብቁ

በ1967 ዓ.ም የደርግ መንግሥት ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ በዴሞክራሲ መንገድ ተመርጠዋል ብሎ የቀበሊ ካድሬዎችን አስቀመጠ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የከንቲባ የክብር ልብስ መለበሱ አቋረጠ። እንዲያውም የመንግሥት ፖሊሲ የነበረው ከተማውን በመተው ወደ ባላገር ያተኮረ ስለነበረ አዲስ አበባ የሕዝቡ ቁጥር ቢጨምርም ውጥንቅጧ የወጣ ከተማ ሆነች። ይህ ፖሊሲያቸው የተዋቀረው በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች "ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ብቻ አይደለችም" ብለው ያነሱትን መፈክር መሠረት በማድረግ ይመስላል። ተማሪዎቹ ያሉት ሊላውንም አትርሱት ነበር እንጂ አዲስ አበባ አትሻሻል ወይም አተገንባ አልነበረም። ባገኙት ክፍተት ከንቲባ ዘውዴ ተክሉ

ከጥቂት ሥራ ወዳዶች ጋር ብቻ በመሆን መሠረተ ልማትን እንደምንም ለመሥራት ጥረዋል። እነዚህም በየቦኑ የከነማ ፋርማሲና ዳቦ ቤቶች እንዲቋቋሙ ምድረ ጋቸውና በተጨማሪም በየቦኑ የፍራፍሬና አትክልት መሸጫዎች ለማቋቋም ሞክረው ውጥናቸውን ሳይጨርሱ መሥሪያ ቤቱ ወደ አዲስ አበባ አስተዳደር ደረጃ ዝቅ አለና ሥራው ቀርቶ ፖለቲካ ማናፈስ ተጀመረ።

በ1928 ዓ.ም የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፒየር ላቫል ስለወልወል ግጭት ጉዳይ በሚወያይበት ጊዜ አዲስ አበባ የሚለውን ስም ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰማ "አበባ እንዴት ያለ ደስ የሚል ስም ነው" 'A-be-ba. Que c'est chic, ça. A-be-ba.' ብሎ አደነቀ። አሁንም ብዙ የውጭ አገር ሰዎች ስሙን በጣም ያደንቁታል። ፈገግ የሚያሰኘው አዲስ አበባ የሚለው ስያሜ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በይፋ የምትታወቅበት ስም ሆኖ እያለ በመንግሥት ሚዲያ ጭምር በሌላ ስም መጥራት ትክክል አይመስልም። አዲስ አበባ ባንትይቀጡ የሚባሉ የታወቁ የሥጋ ደዌ በሽተኛ የሚታጠቡበትን ፍል ውኃ ፊን እያለ ከመሬት የሚወጣበትን አካባቢ ባንትይቀጡ፣ ፊንፊኔ ወይም ፍልውኃ ብለው ሰዎች የሚጠሩት ከደካ አራራ ጉብታ ወረድ ያለ ሥፍራ ነበር። አዲስ አበባ የሚባለው አገር በውስጡ ጉለሌ፣ ኮልፌ፣ ኮተቤ፣ እንጦጦ፣ ቀጨኔ፣ ገፈርሳ፣ አዲስ ከተማ፣ አራዳ፣ ረጲ፣ የካ፣ ፍልውኃ ወይም ፊንፊኔና ከዚያም በላይ በርካታ ቦታዎችን ያጠቃልላል። እየሰፋ ሲሄድም ቃሊቲ፣ ገርጂ፣ ላፍቶ፣ ኢንዶዴ(ቦሌ)፣ ቀራንዮ፣ ታክለውበታል። ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ የሱስ የአፄ ምኒልክ ታሪክ በሚለው መጽሐፋቸው የአዲስ አበባ የበፊት ስሙ ፊንፊኔ ነበር ብለው ስለጻፉ በርካታ ሰዎች ይኸንኑ በመከተል ሲያስተጋቡ አቶ በሪሁን ከበደ ደግሞ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ታሪክ በሚለው መጽሐፋቸው እንዶጥና ይባል ነበር በማለት ጽፈዋል። የኦሮሞ ተወላጆች ግን ሸገር እያሉ ይጠሩት ነበር። አዲስ አበባ በመሠረቱ ግን አጠቃላይ ስም የነበራት አይመስልም። መጀመሪያ የተሠፈረበትን ስፍራ የከተማው ስም ለማድረግ ከተፈለገ እንጦጦ ቅድሚያ ይኖረዋል።

በተረፈ የውጭ አገር ሰዎች ስለ አዲስ አበባ ከተማ ሲገልጹ መላቢስ ከተማ መሆንዋ እንደሚገርማቸው ነው። ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወት የአዲስ አበባን ከተማ ሥርዓት ለመስጠት ያልሞከሩት ነገር አልነበረም። ዶሮ እንኳን ወደ ገበያ ስትመጣ እንዳትንጠለጠል የከለከሉ ሰው ነበሩ። ጋሪን፣ ከብትን ከከተማ ያወጡና አሁን ያለውን የማዘጋጃ ቤት



ሕንጻ ያሠሩ ሰው ናቸው። በተረፈ እሳቸው ለአዲስ አበባ የሠሩትን ለመዘርዘር ቢሞከር ራሱ አንድ መጽሐፍ ይፈጃል። ከተማው ግን ከእሳቸው በኋላ ስንት ሕጻናት፣ ሽማግሌዎችና እርጉዞች በሚበዋወሩበት መንገድ በሬ አስደንብሮ የሚነዳባት ከተማ ሆናለች። ደንብ ቢወጣም አስፈጻሚ አካል ስለሌለ ደንቡ ራሱ የሚሰጠው ጥቅም አይኖርም። በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት ሥነ ሥርዓት አስከባሪ ፖሊስ ለጥቂት ጊዜ እንደነበረ ይታወሳል። መንገድ ዳር ሰዎች ሲጸዳዱ ይዘው የሚያስቀጡ የታወቁና የሚፈሩ የማዘጋጃቤት ሥርዓት አስከባሪዎች ተመድበውም ይሠሩ ነበር።

በመሠረቱ ብዙ አገሮች እንደሚያደርጉት ዋና ከተማው ከነአካባቢው ተከልሎ በራሱ የሚተዳደርና የሁሉም ዜጋ ንብረት የሆነና የተለየ አካባቢ መኖር ይገባው ነበር። ስለሆነም መደረግ ያለበት አዲስ አበባን ከ75 ኪሎ ሜትር ባላነሰ ራዲየስ ከልሎ በሰሜን እስከ ደብረ ሊባኖስ፣ በምስራቅ ሞጆን፣ በደቡብ ቡኢና ቱሉቦሎን፣ በምዕራብ ግንጪን ጨምሮ የአዲስ አበባ ክልል ማድረግ የመጨረሻ ችግር ፈቺ ይሆናል። ምክንያቱም ለከተማው ነዋሪ ቆሻሻ መጣያ፣ ለመጠጥ የዝናብ ውኃ ማጠራቀሚያ፣ የደን ቦታ፣ የአትክልት ቦታ፣ መዝናኛ፣ የዱር አራዊት ክልል፣ የከብት ማደለቢያ፣ የተፈጥሮ ገጽታ፣ የፋብሪካ መንደር፣ የምርምር ስፍራ፣ የመቃብር ክልልና ከተማው ወደፊት የሚስፋፋበት መጠባበቂያ አብሮ መታሰብ አለበት። ሰው የሚኖርበትን አካባቢ ብቻ አዲስ አበባ ብሎ ከልሎ መጥራት አንድ ስፈ እስር ቤት እንደመፍጠር ይቆጠራል። እያንዳንዱ ክልላዊ መንግሥት የኢትዮጵያን ዋና ከተማ ልውሰድ ብሎ ከታገለ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ አንድነትን በአእምሮው እያሰርጽም። ስለሆነም ለአንድነት ሲባል ጉዳዩን በወቅቱ እልባት መስጠቱ ተገቢ ይሆናል። የፌዴራሉ ዋና ከተማ በክልሉ መኖር ለክልሉ ክብረና ምገስ ከመሆኑ ሌላ የኤኮኖሚ አስተዋጽኦ አለው።

ናይጄሪያ ፌዴራል ካፒታል ቴሪቶሪ የሚባል ክልል አዘጋጅታ በውስጡ የአቡጃን ከተማ ዋና ከተማዬ ብላ ሠርታለች። ይህ ክልል ማንም ወገን የኔነው የሚለው ሳይሆን ማንም ናይጄሪያዊ በአንድነት የሚኖርበት አገርና ከተማ ነው። ሌሎችም አገሮች እንደ ብራዚልና አውስትራሊያ ያደረጉት ይኸንኑ ነው።

# ከተማ ማፈራረስ

የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አስተዳደር ግንባታ ላለመሥራት ምክንያቱ ገንዘብ የለም አገሪቷ ደሃ ነች የሚል ነው። ግን ለአንድ ሥራ ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ገንዘብ ይባክናል። ነዋሪውም ጉልበት ባለው ጊዜ የሠራውን ቤት አቅም ባነሰው ጊዜ ያፈርስበታል። ከመፍረስ በከፊል የተረፉትን ቤቶች ነዋሪው ጠጋግኖ ስለሚጠቀምባቸው ልዩ ቅርጽ ያላቸው ቤቶች አዲስ አበባ ውስጥ በብዛት ይገኛሉ።

ጉዳናዎች ዳር የሚሠሩ የእግር መንገዶች አንድ ጊዜ ውሃ ክፍል፣ ሌላ ጊዜ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ ሌላ ጊዜ መብራት ኃይል፣ ሲቆፍረው በፊት የተሠራው አስፋልት ይቆፈርና እንደገና ይሠራል። ነገሩ አያበቃም እንደገና ሌላ ዙር ይጀመራል። ዕውነት ራዕይ ቢኖር ኖሮ ለውኃ፣ ለመብራትና ለቴሌ የገመዶችና ቧንቧዎች ማለፊያ ቱቦዎች መጀመሪያውኑ ተቀብረው መንገዱ ቢሠራ፣ ለብዙ ጊዜ ያገለግል ነበር። ውኃ ክፍል በየመንገዶቹ ዳር በሁለት በኩል ቧንቧ አስቀድሞ እንደመዘርጋት አንድ ሰው ውኃ ለማስገባት በጠየቀ ቁጥር መንገዶቹን ሲከትፍ ይታያል። ለምን መንገዶቹን በሥርዓት አታድሱም ሲባሉ እኛ ለማዘጋጃ ቤት የዕድሳቱን ግምት ከፍለናል ይላሉ። መንገዱን ማዘጋጃቤቱ እንደማያድሰው ሲያውቁ በግብር ይውጣ የከተማውን መንገድ በማፍረሳቸው ለዚች አገር ወደ ኋላ መቅረት ተጠያቂ ከመሆን አያድናቸውም። ኃላፊ የሆነ ባለሥልጣን ለበላይ ችግሩን ማስረዳት ይኖርበታል። የሚሰማውም ከአጣ ሥራውን መልቀቅ አለበት። አለበለዚያ የግብር ይውጣ ነው የሚሠራው ማለት ነው። የውኃ ክፍል የመቶኛ ዓመቱን ሲያከብር "ለውኃ ጡር አለው" ብሎ መፈክር አድርጎ ነበር። በዚያኑ ወቅት ቸርችል ጎዳና ላይ ከሁለት ወር በላይ ወራጅ ቧንቧ ተሰብሮና የሚጠግነው አጥቶ ውኃው እየፈሰሰ አካባቢው አረግሮ አብቅሎ ነበር። ሕዝቡንም የሚያስከፍለው በከፊል ለአየር አንጂ ሙሉ ለሙሉ ለውኃ አይደለም። ምክንያቱም ውኃ በሌለ ጊዜ ቧንቧው ውስጥ የተከማቸውን አየር ውኃ በመጣ ጊዜ ሲገፋው ሜተሩን ስለሚያሽከረክረው ነው። ሌላው ትልቁ ችግር ደግሞ ቧንቧው ባዶ ሲሆን ውስጡ በዝገት ከመጎዳቱም በላይ ባገኘው ቀዳዳ የተበከለ ውኃ ተመልሶ ይገባበትና በተለምዶ ሕዝቡ የቧንቧ ውኃ ሳያፈላ ስለሚጠጣ በውኃ ወለድ በሽታ የሚሰቃየው እየበረከተ የመሄዱ ጉዳይ ነው።



በመሠረቱ አዲስ አበባ ውስጥ የመንገድ ጥገናውም ኾነ አሠራሩ የግብር ይውጣና ኋላ ቀር ከመሆኑም በላይ አሠራራቸውን ለማሻሻል ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም። የመንገድ ነጭ መስመር እንኳዋን በትክክልና ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ኾኖ መሠመር አልቻለም። መንገድ ሲያድሱም የፈሳሽ መተላለፊያ ገንዘብ አውጥቶ ላለመሥራት ውኃ መንገዱን እንደሚያቋርጠው እያወቁ አስፋልት አልብሰው ይሄዳሉ። የራስ መኮንን ድልድይና ፍልውኃ አጠገብ በየዓመቱ መንገዶች የውኃው መተላለፊያቸው እየፈነዱና ለመተላለፍ ማስቸገራቸው የተለመደ ክስተት ሆኗል። በተጨማሪም ወራጅ ውኃ በመንገዶች ላይ ሲወርድ ተግቶ የሚቆጣጠረው ባለመኖሩ መንገዶችን ያፈራርሳል። ከተሠራ አንድ ዓመት ያልሞላው የቀለበት (አሁን የግማሽ ጨረቃ) መንገድ ገና ከአሁኑ ውኃ እየቦረቦረው ነው። ማስረጃ መጥቀስ ቢያስፈልግ ቦሌ ሞሐ ኩባንያ አጠገብና ከዮሴፍ መቃብር ወረድ ብሎ ያለውን አስፋልት አሁኑኑ እየቦረቦረው መሆኑን መመልከቱ በቂ ነው።

መጋቢ መንገዶች ትኩረት ስለማይሰጣቸው ችግሩ በዚህ ረገድ በጣም የጎላ ነው። የተዘጉ መንገዶች ለመጥቀስ ያህል የገዳም ሠፈር መንገድ ወይም በውኃ ክፍል ጀርባ ያለውና የአባ ኮራን ሠፈረ መንገድ ለዕድሳት ያልታደሉ ናቸው። የጣሊያን ሠፈር መንገዶችም ታድሰው አያውቁም። አስፋልታቸው እያበጠ መኪና የሚሰብሩ መንገዶች ደግሞ ከመርካቶ የሚነሳው የጅማ መንገድ፣ ከአርበኞች መንገድ ወደ አሮጌው ፖስታ ቤት የሚወስደው መንገድና ከሰሜን ሆቴል ወደ ዮሐንስ የሚወስደው መንገድ ናቸው። በስፋት ተሠርተው ጥቅም ያልሰጡ መንገዶች ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ የሚወስደው መንገድ ፔፕሲ ኮላ ሲደርስ በመቆሙና በፖሊስ ሆስፒታል በኩል የሚሄደው መንገድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲደርስ ባለመቀጠሉ ሲሆን ከሱም በላይ ያለው ወደጌጃ ሠፈር የሚታጠፈው መንገድ ባለመዝለቁ ጥቅም አልሰጡም። ዕቅድ ቢኖር ኖሮ አንድ ጊዜ በደንብ የተጠገነው መንገድ ለብዙ ዓመት ስለሚያገለግል በሚቀጥለው ሌላ አዲስ መንገድ በማደሻው ገንዘብ ይሠራ ነበር። እንዲያውም ብዙውን ጊዜ በደረቁ በበጋ ወራት ሲጨቃጨቁ ክርመው ሥራ የሚጀምሩት በክረምት ነው ይባላል።

ዕውነት ድሃ ከሆንን ገንዘባችንን ከማባከን በበለጠ ለሚጠቅመን እናውለው ነበር። ያለብን ችግር የአመለካከት እንጅ የገንዘብ ችግር አይደለም። አገሪቱ ድሃ ናት፣ ገንዘብ የለም የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ። እርግጥ ኃብታም

አይደለንም ግን ገንዘባችንን ስናጠፋ ወደፊት ለሚጠቅመንና ኃብታም ለሚያደርገን ካላጠፋነው ነዳጅ እንኳን ቢወጣ ከድህነት አንወጣም። ነዳጅ እያላቸው ድሃ የሆኑ አገሮች በርካታ ናቸው። ለመጥቀስ ያህል ናየጀሪያ፣ ካሜሩን፣ ትሪኒዳደና ቶቤጎ፣ ቬኔዙዌላ፣ ወዘተ.. ናቸው። አስተዳደሩ ሳይሻሻል ነዳጅ ባይወጣ ይሻላል ብለው የሚከራከሩም አሉ። ምክንያቱም የመጭው ትውልድ የምድር ውስጥ ኃብት እንዳይባክን ለማለት ነው።

የአ.አ. ማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ነባር መንገድ ላይ አፈር ወይም ድንጋይ ቆልለው ወይም መንገዱን ቆፍረው ሲሄዱ ተገቢ ምልክት እንኳን ሳያደርጉ በመሄዳቸው አደጋ ሲደርስ በማግስቱ ተሰበስበው አደጋውን እያዩ 'ሾፌሩ ሰክሮ ይሆናል!' እያሉ ይሳለቃሉ። ለምልክት የፕላስቲክ ኮን እንኩዋን ማስቀመጥ አልተቻለም። በአዲስ አበባ የአደጋ መከላከያ ምልክት ድንጋይ ሆኗል። እንደ ደቡብ አፍሪካ ባሉ አገሮቸ የባላገር መንገድ እንኳን ሲታደስ መብራት የተቀመጠበት በርሜል ለብዙ ኪሎ ሜትር ያህል ይደረደራል። አስፋልት መንገድ ላይ ሰዎች በክረምት ለቤት መሥሪያ ጭቃ ሲያቦኩበት በበጋ በርበሬ ወይም ጌሾ ሲያሰጡበት የሚከለክል ኃላፊ የለም። የውስጥ መንገዶችን የፈለገ በድንኳን ሲዘጋው ወይም የእግቢ ማፍሰሻ አየሆነ ሲሄድ የሚናገር የለም። ወለሉን ያልጠበቀ ክፍት ቦይ በየመንገዱ ዳር ስለሚሠራ የከተማን ኑሮ አደገኛ እያደረገው ነው። ተላላፊ በሽታ ገብቶ ሕዝቡን ቢጨርሰው የራሱ ጠላት ራሱ መሆኑን እንኳን ሳይገነዘብ እንዳያልቅ ያሰጋል።

*መቼም የአገሪቱ መንግሥትም ኾነ ማዘጋጃ ቤት ለመሥራት የሚፈራው ነገር ቢኖር ድልድይ ነው። አዲስ አበባ ደግሞ ተራራማ በመሆንዋ ያለድልድይ ሥራ በምንም መልኩ ልትሻሻልና ልታምር አትችልም።*

## የመንገድ ሥራ

*የመንገድ አዘረጋግ ሥርዓትን ለማሻሻል ብዙ አብነቶች ሊነሱ ይችላሉ። አራተኛ ክፍለ ጦር ፊትለፊት የጥንቱ መሿለኪያ* (Overpass or Flyover Bridge) *አጠገብ ከቅዱስ ዮሴፍ ት/ቤት አንስቶ እስከ አራተኛ ክፍለ ጦር አጥር ማለቂያ ድረስ አፈር ተቆልሎ የመኪናው መንገድ ከባቡሩ ሃዲድ ጋር እንዲገናኝ ተደረጎ ተሠራ።*



*መንገዱ ከተሠራ ጀምሮ እስከ አሁን በርካታ የሰው ሕይወትና ንብረት ተጎድቷል። ስድስት ወይም ስምንት ምሰሶ ተተክሎ ባቡሩ ላዩን፣ መኪኖች ሥሩን፣ እንዲሄዱ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ የትራፊክ መጨናነቅና አደጋም አይኖርም ነበር። የመንገዱም ትክክለኛ ወለል ይታወቅ ነበር።*

የአንድ መንገድ ወለል ካልታወቀ በመንገዱ ዳር የሚሠሩት ቤቶች በዕቅድ ሊሠሩ አይችሉም። የፍሳሽም መሄጃ በዕቅድ ሊሠር አይችልም። የወለል ነገር ከተነሳ የአዲስ አበባ መንገዶች ወለላቸው በጭራሽ አይታወቅም። እያንዳንዱ የአዲስ አበባ መንገድ ሲታደስ አስፋልት በጠጠር ተቦክቶ ይደረብበታል። አቀበት መንገድ ላይ የሚደረበው ጠጠርና አስፋልት ፀሐይ ሲመታው እየተሸበሸበ መኪና ይሰብራል። ከሁለት ዕድሳት በኋላ የመንገዱ ጠርዞች ሲዋጡ ተቆፍረው ይወጡና ከፍ ይደረጋሉ። ውኃ ማስተላለፊያ ጉድጓዶች እየሰመጡ አደገኛ ይሆናሉ። በዚህ ዓይነት ከሃምሳ ዓመት በኋላ በየመንገዱ ዳር ያሉት የምድር ቤቶች ውስጥ ሰው የሚገባው በመሰላል ይሆናል ማለት ነው።

ሌላው አገር ለአካል ጉዳተኞች ብዙ እንክብካቤ በሚደረግበት ዘመን እኛ አገር ግን ዓይነ ስውሮች በየመንገዱ ዳር ባለው በሰው ሠራሽ ጉድጓድ እየገቡ ተጨማሪ የአካል ጉድለት ሲደርስባቸው እንመለከታለን። ደንቡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት ክንቲባው በሕዝብ የተመረጠ ቢሆን ኖሮ ሥራ መልቀቅ ይኖርበት ነበር። ችግሩ ከንቲባዎቹ የመንግሥት ሹሞች ስለሚሆኑ ሕዝቡን አይፈሩትም። ነዋሪው "ለማን አቤት ይባላል" ሲል የሚያሰማው ምሬት ብዙ መልዕክት እንዳዘለ ሥልጣን ላይ ያሉት የሚገባቸው አይመስልም።


ሙሴ ሚናስ

## የከተማ ዕቅድ

የአዲስ አበባ መሪ (ማስተር) ፕላን እየተባለ የሚወራው ለሕዝብ የተደበቀ ግን ሰውን ውዥንብር ውስጥ የሚከት ነው። የልምዱ

መሃንዲስ ሙሴ ሚናስ በየመኳንንቱ ቤት ሲደርሱ መንገዱን አጠፍ እያደረጉ የተቻላቸውን ጊዜው በሚፈቅደው መሠረት ሠርተዋል። ሰውየው በጣም የታወቁ ስለነበሩ ሕዝቡ ከዚህ በታች ያለውን ገጥሞላቸዋል።

ባሊያንም መጣ ሄደ ተመለሰ
እንግሊዝም መጣ ሄደተመለሰ
ሚናስ ብቻ ቀረ ቤት እያፈረሰ።

አስቀድሞውኑ ሁሉ ነገር በዕቅድ ቢሠራ ኖሮ ቤት ማፍረስን ምን ያመጣው ነበር። ከሙሴ ሚናስ በኋላ የነበሩትም መሃንዲሶች መንገድ ብቻ ሳይሆን ድልድይም አጣምመዋል። ከጉለሌ ወደ ቀጨኔ የሚወስደው መንገድ ሲሠራ የወይዘሮ ጅፋሬ ቤት ላይ የሚያልፈውን መንገድ ለማሸሽ ድልድይ ማጣመም ነበረባቸው። የወሎ ሰፈር መንገድም ተጣሞ የተሠራው በዘመኑ በነበረ ባለሥልጣን ተጽዕኖ ነው ተብሎ ተወርቷል። በደርግ ዘመን የነበሩት መሃንዲሶች ከተማው ሳይሆን ራሳቸው ያለ ይሉኝታ ብዙ ተጠቅመዋል ይባላል። የሚያሳዝኑት ንጹህና ችሎታ ያላቸው መሃንዲሶች አብረው መወቀሳቸው ነው። መሪ ፕላን የሚባለው ለሕዝብ ይፋ ሆኖ ስሜት ያለው አጥንቶት ቢተችበትና ውሳኔ መጨረሻ ላይ ቢደረስ ይሻል ነበር። ይህ ሆኖ ቢሆን ኖሮ በየጊዜው መሪ ፕላኑ እየተሻሻለ ነው እየተባለም ምክንያት አይሰጥም ነበር።

አዲስ አበባ ራዕይ የሌለው ከተማ ስለሆነ ከስንት ዓመት በኋላ ኦሊምፒክ እንደሚካሄድበት፣ ከስንት ዓመት በኋላ የሕዝቡ ብዛት ስንት ሚሊዮን እንደሚሆን፣ ሕዝብ በምን ማመላለሻ ወደፊት እንደሚጓጓዝ፣ አይታወቅም። ለሕዝብ መናፈሻና ለፓርክ የተከለሉ ቦታዎች ለግለሰብ መኖሪያ እየተሰጡና እየተሸጡ አልቀዋል። ልክ አፄ ምኒልክ ጃንሜዳን እንደከለሉት ባሲያንም ወደ ኮልፌ በሚወስደው መንገድ በስተቀኝ ያለውን ከአሁኑ አውቶቡስ መናኸሪያ በላይ ያለውን ቦታና የኳስ ሜዳ እየተባለ የሚታወቀውን ለጥ ያለ ሜዳ ከልሎ ለሕዝብ መናፈሻ ያስቀመጠውን ሕዝብ ተመርቶት አሁን ችም ችም ያለ መንደር ኾኗል።

ቀደም ብሎ ከለገሃር እስከ ቦሌ የተዘረጋው የሃዲድ መስመር ሲያገለግል ሲችል መዘጋቱ የማን ጥፋት ወይም ችላ ባይነት ነው? መንግሥት ራሱ የሕዝብ ማመላለሻ ስላልሠራ ኃላፊነቱን ለባለታክሲዎችና ለአንበሳ አውቶቡስ በመተው መሃል ከተማዎች መናኸሪያ እየሆኑ ነው። አደባባዮችም የአውቶብስ ማቢያና ጋራዥ



እየመሰሉና የከተማው ውስጥ የመኪና አነዳድም በግራ ይሁን በቀኝ ግራ እያጋባ ነው። የምኒልክ አደባባይና ለገሃር የሞዓ አንበሳ አደባባይ የአውቶብስ ጋራዥ ሆነዋል። ኢትዮ ፍሩት የእግር መንገድ ላይ ድንኳን ተክሎ አትክልት ሲሸጥ መንገድ ዘግቶሃልና ተነስ የሚለው የለም። ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ያስወገዱትን የእግር መንገድ ላይ ሱቆች የኮካ ኮላና ፔፕሲ ኮላ ሱቆች እንደገና ተደርድረውበት መንገድ እያጣበቡ ነው። አዲስ አበባ ውስጥ ስለ እግረኛ መንገድ ከማንሳቱ መተው ይሻላል። የትራፊክ መብራቶችን ሲገጥሙ እንኳን ስለ እግረኛ የሚታሰብበት አይመስልም። በዓለማችን ካሉ ትልልቅ ከተሞች መካከል ሕጻን ልጅ በጋሪ (Perambulator or Pram or Push Chair) እየገፉ የማይወጡበት ከተማ አዲስ አበባ ነው።

ለእሳት አደጋ የሚያገለግል ግፊት ያለው ውሃ አዲስ አበባ ውስጥ በየዋና መንገዶች ዳር ለመግጠም ታልሞ አያውቅም። በአሁን ሰዓት የሚሠራው ቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ያለው ብቻ ነው። የእሳት አደጋውም ድርጅት ከከተማው ዕድገት ጋር አብሮ የሚሄድ አይመስልም። አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ የውሃ ጉድጓድ በነበረ ጊዜ ልጆች ሲገቡበት የእሳት አደጋ ይጠራና ሲመጣ ይዞ የሚመጣው ነገር ቢኖር ሬሳውን ዘንጥሎ የሚያወጣ መንጠቆ እንጂ ኦክሲጅን ተሸክሞ ጉድጓዱ ውስጥ ገብቶ ልጁን በሕይወት ለማውጣት ሲሞክር ታይቶ አይታውቅም። የአዲስ አበባ ነዋሪ ከክፉ ነገር ሰውረኝ እያለ መኖር ልምዱ ሲሆን አሁን ደግሞ አትመመኝ ማለት ጀምሯል። ምክንያቱም ለድንገተኛ ህክምና የተዘጋጀ ሃኪም ቤት እየጠፋ ስለሄደ ነው።

የፎቆች ከፍታ እያደገ ሲሄድ የእሳት አደጋ ድርጅትም እስከ ሄሊኮፕተር ድረስ የመጠቀም ልምድ ማዳበር ይጠበቅበታል። ትልቅ እሳት በተነሳ ቁጥር የአሲዬሽንን የእሳት አደጋ እርዳታ እየጠበቀ የከተማው የእሳት አደጋ ክፍል ሊቆይ አይገባውም። እስከ አሁን የሚታየው ቤት ሲቃጠል አመዱ ላይ ውሃ አፍስሶ መመለስ እንጂ ቤቱን ከእሳት ቃጠሎ የማዳን ችሎታ ድርጅቱ ያለው አይመስልም።

አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና ልትሆን ዕድሉ ነበራት። እኛ ግን ጠንክረን ወንዞቻችንን የሚያሻግር ድልድይ እንኳን ለመሥራት ስላልተባበርን ዕድሉን አፈር እየቆለሉ ድልድይ ለሚሠሩት የናይጀሪያ ዋና ከተማ ለእነአቡጃ ሳናስረክብ አንቀርም። ስለሆነም የኢትዮጵያ ብልፅግና ከጅምሩ ስለተበላሸ እስካለንበት ዘመን ድረስ እያሽቆለቆለ እንጂ እየተሻሻለ ሲሄድ አልቻለም። የኒው ዮርክ ከተማ የምትታወቀው

በሮቆችዋ ሳይሆን ከዛሬ አንድ መቶ ሃምሳ ዓመት በፊት በወጣላት ፕላን መሆኑን ከተማዋን የጎበኙ ሁሉ ያውቃሉ። እንደዚሁ ሁሉ አሥመራ ከተማ እንኳን ባሊያን በመሃል የሚያልፈውን ወንዝ ደፍኖ መንገድ ስለሠራባት ለኤርትራውያኖች መኩሪያ እንደሆነች እናውቃለን።

ጉንቢ ሃሳቦችን ከብዙ ሰዎች ለማሰባሰብ የሚቻለው የፕላኑ አሠራር ግልጽ ሲሆን ነው። ሃሳብ ከባለሙያው ውጭ ሊገኝ አይችልም ብሎ መደምደም ያስቸግራል። ለምሳሌ ጎሞራው በሚል የብዕር ስም የሚታወቁት ጸሐፊ ለአዲስ አበባ ያላቸውን ምኞትና የአዲስ አበባን የምድር ውስጥ መንገድ በአበባ ቅርጽ የሳሉትን በኢትዮጵ መጽሔት በጥር ወር 1995 ዓ.ም እንዳወጡት ብዙ ሰው ተመልክቷል። የሚደንቀው ደግሞ ለምድር ውስጥ መንገድ እንዴት አድርጎ ከዝቋላ የሚነፍሰውን ነፋስ ለንጹህ ዓየር አቅርቦት ለመጠቀም እንደሚቻል ለማሳሰብ መሞከራቸው ጭምር ነው። የምድር ውስጥ መንገድ ለዘመናችን በጦርነት ጊዜ ለነዋሪው መደበቂያም ጭምር ሆኖ ስለሚያገለግል ዕቅድ ውስጥ መግባቱ ቅንጦት አይሆንም። እንዲያውም ለኒዩክሊር መከላከያም ጭምር እንዲሆን ታስቦ መሠራትም ይኖርበታል።

የአዲስ አበባ መሪ ፕላን አለ ብሎ ለማለት አያስደፍርም። ለዚህ ድምዳሜ ዋናው ምክንያት የመሪ ፕላኑ ምስጢር መሆኑ፣ በየጊዜው መለወጡና መሪ ፕላኑን ተከተሎ ከተማው አለማደጉ ነው። ለዋና መንገድ የታቀደው ቦታ ላይ ቤት እንዲሠራ ፈቃድ ይገኛል። ዛሬ መኖሪያ ሠፈር የተባለው ነገ ተሸሮ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ይሠራበታል። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንኳን አንዱ የሠራውን ሌላው ይነጥቀዋል። ለምሳሌ ቡና ቦርድ ያሠራውን ሕንፃ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ገብቶበታል፤ የግብርና ሚኒስቴር ያሠራውን የኦሮሚያ ጽሕፈት ቤት ወስዶታል፤ የመከላከያ ሚኒስቴር ያሠራው ሕንፃ የፌዴራል የጸረ ሙስና ኮሚሽን ገብቶበታል፤ ለሆስፒታል የተሠራውን ቤት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ይዞታል፤ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አዲስ የሠራውን ቤት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በከፊል ይዞት ራሱ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ውጭ ቤት መከራየት ጀምሮ ነበር። እንዲያውም በቤቱ ጥበት ምክንያት ቢሮዎቹ በየአውራጃው በተወረሱ መኖሪያ ቤቶች መዛወርም ጀምረው ነበር። መንግሥት ሲለወጥ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተንሰራፍቶበት ቤቱ ውስጥ ከባድ ማሽን ከጃፓን አገር አስመጥቶ በማስገባቱ ግድግዳው መሰነጣጠቅ ጀምሮ ቤቱ እስከ አሁኑ በመታደስ ላይ ይገኛል። ስለኾነም አንዱ



በጥናት ያሠራውን ሕንፃ ሌላው ሲገባበት ቤቱ ውስጡ ይፈራርስና እንደገና ሲለዋወጥ ወጪ የሚያስከትልና የተመሰቃቀለ ቤት ይኾናል። ስለሆነም ብዙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የኤሌክትሪክ ገመድ አንደሸረሪት ድር ያደራባቸው ይመስላሉ። በጠቅላላው አሠራሩ ሁሉ በጥናት መካሄድ ሲገባው በተዝረከረከ መንገድ መፈጸሙ አሠራሩ ራዕይ የሌለው መኾኑን ያመለክታል። ለተከታታይ ጥገናም በጀት ተይዞለት በሥርዓት የሚከናወን አይመስልም። ምክንያቱም ልክ እንደመኖሪያ ቤት ግንባታው ሲያበቃ አለቀ ተብሎ ውስጡ መግባት እንጂ ቤቱን በቀጣይነት ማደስ ከመሥሪያ ቤቱ የዕለት ተዕለት ሥራ ጋር የሚካተት አይመስልም።

የአራዳ ሕንጻ የከተማውን ዕምብርት በደረጃ ዝቅ ያደረገ መስሎ ይታያል። የተሠራውም ቤንዚን በራሽን በሚታደልበት ዘመን አጠገቡ ያለው ጎዳና ለአሥር ዓመት ያህል ተዘግቶ ስለነበረ እያንዳንዱ የአዲስ አበባ አሽከርካሪ በቤንዚን ወጭ ብዙ ከስሮበታል። የምድር ቤቱም ለመኪና ማቆሚያ እንዲጠቅም ሆኖ ተሠርቶ በሆነ ኖሮ አገልግሎት ይሰጥ ነበር። ለመሆኑ ለምንድን ነው መንግሥት የሚያሠራው ሕንጻ ከአሥር ዓመት በፊት የማያልቀው? ሃያ ዓመትም ገደማ የፈጀ እንደ ብሔራዊ ባንክ ሕንፃ የመሳሰሉም እንዳሉ ይታወቃል።

## የተረሱ ሠፈሮች

በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን መንግሥት መሬቱ ለአይሮፕላን ማረፊያ አይሆንም ቢባልም ለከተማ ይቀርባል በማለት ቦሌ ወይም ኢንዶዴ ላይ እንዲሠራ ተደርጓል። ስሙ የቀዳማዊ ኃይላ ሥላሴ ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ ሲባል በደርግ ዘመን መንግሥት የቦሌ ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ ተባለ። ቦሌ ወይም አምቦ ማለት በኦሮምኛ ቋንቋ የጨው አፈር ማለት ነው። የቦታው ስም ግን ኢንዶዴ እንጂ ቦሌ አልነበረም። ይህ የአይሮፕላን ማረፊያ በአሁኑ ወቅት ከተማ እየከበበውና የከተማ ማዕከል እየሆነ ሄዷል። እንደሚባለውማ በደርግ ዘመን መንግሥት አይሮፕላን ማረፊያው ዱከምን አልፎ ዝቋላ አጠገብ ድሬ የሚባል ቦታ ላይ ለማዛወር 12 ሜትር ያህል ኮንክሪት ተሞልቶ ሥራው ተጀምሮ ነበር።
የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የአይሮፕላን ማረፊያን እየተከታተሉ መሬት መያዝና መኖሪያ ቤት መሥራት እንደልምድ እያደረጉት መጥተዋል።

መንግሥትም እንዲርቁ እንደማድረግ ጭራሽ ያበረታታል። ለምሳሌ የልዑል ማህለ ሥላሴ መንደር አሁን ቀበሌ 25 የሚባለው መጀመሪያውኑ መንግሥት አሠርቶ ለሕዝብ የሸጣቸው ቤቶች ናቸው። አይሮፕላን ማረፊያ እየተከተለ ሕዝቡ ለምን ቤት ይሠራል ቢባል አንድ የሚያስገድደው ነገር መኖሩን ይጠቁማል። መንግሥት ሌላውን የመኖሪያ ሠፈር ዞር ብሎ ስለማያየውና ሁልጊዜ አዲስ ነገር የሚታየውና የሚገነባውም አይሮፕላን ማረፊያ አጠገብ ስለ ሆነ ነው። የቀለበት መንገድም ቢሠራ የአይሮፕላን ማረፊያውን ማዕከል በማድረግ ነው። ለምሳሌ የጥንት የአዲስ አበባ ሠፈሮችን ብንወስድ እንደ ዶሮ ማነቂያ፣ ሠራተኛ ሠፈር፣ እሪ በከንቱ፣ ባሻ ወልዴ ችሎት፣ ዘበኛ ሠፈር፣ ገዳም ሠፈር፣ አባ ኮራን ሠፈር፣ አቧሬ፣ ኳስ ሜዳ፣ ጉለሌ፣ ቀጨኔ፣ ስድስት ኪሎ፣ አራት ኪሎ፣ እያረጁና እየፈረሱ እንጂ እንደ አዲሱ የቦሌ ሠፈር ዘመን አመጣሽ የፍሳሽ አገልግሎት፣ ወይም አዲስ ዲጂታል የስልክ መስመር አይሠራላቸውም። ቦሌ ውስጥ እንዲያውም ቤቨርሊሂል በመባል የሚታወቀው ሠፈር የባለ ሥልጣኖችና የከበርቴዎች መኖሪያ ሆኗል። በአንጻሩ አንዳንድ ሠፈር የውስጥ መንገዶቹ በአጣናና በዶሮ ነጋዴዎች ተዘግተው መኪና ማስተላለፉቸው እየቀረ ሲሄድ ዞር ብሎ የሚያያቸው ባለሥልጣን አልተገኘም። ስለሆነም አንድ ሰው ቤት ቢሠራ እንደ አዲሱ ሠፈር ዋጋ አያወጣለትም። አሮጌ ድልድይ ቢሰበር እስኪታደስ ሦስታና አራት ዓመት ይፈጃል። የቀለበት መንገዱ እንኳን በነዚህ ሠፈሮች አካባቢ እንዳያልፍ የሚታገሉ እንዳሉ ይታወቃል። ስለዚህ በነዋሪው ለመፍረድ አስቸጋሪ ይሆናል።

እንደ ዕውነቱ ከሆነ አይሮፕላን ማረፊያ አጠገብ መኖር ከሚያስከትለው አደጋ በተጨማሪ ከሚነሳውና ከሚያርፈው አይሮፕላን የሚተነውና የማይተየው የሞተር ጭስ ለጤና ጥሩ አይሆንም። ጩኸቱና የአየር እርግብግቦሹ ቤቶችን ይጎዳል። የሞተር መፈተሻው የሚያወጣው ድምጽ የደርግ ባለሥልጣኖችን ማታ ማታ ስለረበሸ ብዙ የአሜሪካን ብር ወጭ ተደርጎ እምድር ውስጥ እንዲሆን ተደረገ።

በተለይ ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ እምብርት የሚባለው የቱ እንደሆነም የሚቸግርበት ሁኔታ አለ። በፊት በቅዱስ ጊዮርጊስ አራዳ ወይም ፒያሳ አካባቢ የዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት ነበር። መሆን የነበረበት በፊት የተመሠረተው ከተማ እየተሻሻለና እየሰፋ ሄዶ ዳብሮ ዘይትም ቢደረስ ምንም አልነበረም። አሠራሩ ግን የበፊቱ እየተረሳ አዲስ ሠፈር ዳመሥረት ብቻ ከሆነ ዛሬ ጊዜ ቦሌ አካባቢ ብዙ ገንዘብ እየወጣ የሚሠራው ከተማ ነገ ደግሞ ይረሳና አዲስ



ሠፈር በወረት መገንባት ይጀመራል። ስለዚህ ነው አዲሱ የተሳካለት ትውልድ ከጥንት ሠፈሮች እየኮበለለ ወደ አዲሱ ሠፈር ኑሮውን የሚጀምረው።

## የቦታ ይዞታ

አዲስ አበባ ውስጥ ጥንት በአፄ ምኒልክ ጊዜ ለአንድ የጦር አበጋዝ መሬት ሲሰጠው ከነሠራዊቱ ስለሆነ ለራሱ የሚበቃውን ያህል ካጠረ በኋላ በተረው ለባለሟሎቹ እንደየማዕረጋቸው ዙሪያውን መሬት አከፋፍሎ ይመራል። በኋላ ላይ ግን የመሬት ጥቅም እየታወቀ ሲመጣ ስማቸው በሠነድ ለመንግሥት ያልገባ ሰዎች እንደጭሰኛ ሆነው ከመኖራቸው ሌላ ቢከራከሩም ዳኛ እያጡ ደርግ በውርስ እስካስተካከለው ድረስ ችግር ነበረ። ከነዚህም መካከል በላይ ግቢ ዙሪያ የሠፈሩት የራስ መኮንን ባለሟሎች ለብዙ ዓመት የማይከራከሩት ባለጋራ ስለነበረባቸው ባለቤትነታቸው ሳይለይ እስከ 1967 ዓ.ም ኖረዋል። የእቴጌ ጣይቱ መስኮችን ጣሊያን ባዶ ቦታ ሆነው ስላገኛቸው ለሕዝብ መርቷቸው ብዙ ቤቶች ተሠርተውባቸው አሁን ድረስ ችምችም ያሉ መንደሮች ሆነዋል። ሕዝቡ ለማዘጋጃ ቤት ግብር እንዳይከፍልና ባለቤትነቱን እንዳያጸድቅ የቦታው ባለቤት እቴጌ ስለሚል ብቻ ማዘጋጃ ቤትም ደፍሮ መወሰን አቅቶት ከ1933 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም ለመንግሥት ግብር ሳይከፈልባቸው ቀርተዋል።

## የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አሠራር

የአዲስ አበባን ማዘጋጃ ቤት ለምሳሌ ያህል ጠቀስን እንጂ ብዙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚጠበቅባቸውን ያህል አልሠሩም። የሚሾሙት ባለሥልጣኖች የሚደክሙት ለመንግሥት ተጨማሪ ገቢ ያስገኙ መሆናቸው እንዲታወቅና ከፍተኛ ሹመት እንዲያገኙ ነው። ለምሳሌ ያህል በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን እንዲያስተዳድር የተሾመ ሰው ስርጭቱ ላይ ምንም መሻሻል ሳያደርግ በተጠቃሚዎች ላይ የሃምሳ ብር የቴሌቪዥን ግብር ብቻ ተክሎ ወረደ።

የቴሌኮሙኒኬሽን መሥሪያ ቤት ሲጨነቅበት የሚታየው ስለ መስመር ማስፋፋትና ከሚሰጠው አገልግሎት ጥቅም አኳያ ሳይሆን ስለ ቴሌፎን መሣሪያዎች (Apparatus) ሽያጭ ነው። በሌላው አገር

ይህ ሥራ የነጋዴዎች አቅርቦት ወይም የፋብሪካዎች ምርት ነው። እንዲያውም የቴሌፎን መሣሪያ ፋብሪካ አንድ ከበርቴ ለመክፈት ፈልጎ በቴሌኮሙኒኬሽን አለመተባበር እንደቀረ በሰፊው ይወራል። ውጤቱም ኢትዮጵያ በመረጃ ዘመን በአፍሪካ ጭምር ኋላ ቀር ሆናለች። መንግሥት የሌላት ሶማሊ እንኳን በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኢትዮጵያን ትበልጣለች።

የትንባሆ ሞኖፖል መሥሪያ ቤት የተበላሹ ሲጋራዎችን እንደማቃጠል ለሕዝብ ይሸጥ ነበር። ዓላማው ብዙ ገቢ ማሳየት እንጂ የሞኖፖል መብት የተሰጠው ንጹህ ሲጋራ ማቅረብና የሕዝቡን ጤንነት መጠበቅ መሆኑን የዘነጋ ይመስላል። ስለ ሕዝቡ በተበላሸ ሲጋራ መታመም ለባለሥልጣኑ ጉዳዩ አይደለም። ስለሆነም መሥሪያ ቤቱ ሥልጣኑን ያለአግባብ ስለተጠቀመ (Abuse of Au(hority) ሙሰና ይሆናል።

እንደ ብሔራዊ ሎቶሪ ያሉ መሥሪያ ቤቶች እንደሌላው የሠለጠኑ አገሮች የውድድር ንግድ ላይ ለሚሰማሩት ነጋዴዎች መመሪያ መስጠትና መቆጣጠር ሲገባቸው ራሳቸው ሎተሪ ሻጭ ሆነው መንግሥትን በንግድ ሥራ ላይ የሞኖፖል ሥራ እንዲሠራ አድርገውታል። ለዚህም ይመስላል ኢትዮጵያ ውስጥ የፈረስ እሽቅድምድምና የመሳሰሉ የውርርድ (Betting) ንግድና ካዚኖ የማይካሄደው። ከሽጡት የሎቶሪ ብዛት ስንት በመቶ መልሰው ለሕዝብ መስጠት እንዳለባቸው አይታወቅም። ሎተሪም የደረሰው ሰው በታክስና በዕርዳታ ስም በፊትለፊትና በተዘዋዋሪ መንገድ ከፊሉን መልሶ መስጠት ይገደዳል።

በተባበሩት መንግሥታት እንደ አደገኛ ዕፅ የተቆጠረውንና የሶማሊ መንግሥት እንኳን በአዋጅ የገደበችውን ጫት የኢትዮጵያ ተተኪ ትውልድ እየተላመደው የእሱ ተገገር ሲሆን ገና ለገና መንግሥት ብዙ ገቢ ያገኛል ተብሎ ጠበቅ ያለ እርምጃ የሚወሰድ መሥሪያ ቤትም ሆነ ባለሥልጣን አልተገኘም። የሚደንቀው ደግሞ ገበሬው ሌላውን እርሻ ሁሉንም ጭምር እያጠፋ በጫት እየተካው መሆኑ ነው። ይህን የመሰለው አድራጎት ሙሉ ቢያድርም ለወደፊቱ ጎጂነቱ ይታያል።

የቀይ መስቀል ድርጅትም ለአደጋ መከላከል ዝግጅቱ ምን ያህል እንደሆነ ሕዝቡን ስለየሚያሳትፍ አይታወቅም። ሥልጣኑም በመንግሥት ተሿሚዎች•የተያዘ ነው። በሠላሙ ጊዜ ያላሳተፋት ሕዝብ በጦርነት ጊዜ ለግልጋሎት ሊጠራ አይችልም። በመጠኑ



የአምቡላንስ አገልግሎት መስጠቱ አልቀረም። በተረፈ ሕዝብ የሚመለከተው ለጥምቀት ጊዜ በርትቶ አጾክብሬ ያለባቸውን ሰዎች በአንቡላንስ እያባረረ መርፌ ሲወጋ ነው።

ብዙ ገንዘብ ወጥቶ፣ መሣሪያ ተገዝቶ፣ ወታደር ሠልጥኖ፣ ሁሉም ስንቅ እንዲያዘጋጅ ተደርጎ አገርን ከሚወርር ጠላት ጋር እንደምንዋጋው ሁሉ በሽታ የሚረጩ ትንኞች ሲፈጁን ዝም ብለን የምናየው ለምንድ ነው? ለምንስ ጦርነት አንገጥማቸውም?። በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን የነበረው የወባ ማጥፊያ ድርጅት በደርግ ዘመን ማሠልጠኛውም ተዘግቶ የወባ መከላከያ ተብሎ ወደ ጤና ጣቢያ ደረጃ ዝቅ እንዲል ተደረገ። ስለሆነም ወባ እንደገና አንሰራፍቶ ሕዝቡን እየፈጀው ነው። የተማሩም ልጆች አገራቸውን ለመርዳት ወደየባላገሩ ሲሄዱ በወባ ተነድፈው ይመለሱና ሲታመሙ ቀላል ጉንፋን አየመሰላቸው በሥርዓቱ ሳይታከሙ እየቀሩ ያለቁት በርካታ ናቸው።


የተፈሪ መኮንን ሆፒታል ይባል የነበረው አሁን የኢትዮጵያ የጤና፣ የምግብና የመድሃኒት መመርመሪያ ኢንስቲትዩት በተለምዶ ፓስተር ኢንስቲቲዩት የሚባለው አስመኪና ዘመናዊ የመመርመሪያ መሣሪያ ሊኖረው ይገባል። ምክንያቱም ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ተዋሕሲያን በአሁኑ ዘመን እየተበራከቱ ስለመጡ ለምርምርና ለመከላከል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል። ምንም እንኳን የተዋሕሲያንና የመድኃኒቶች ምርምር በመጠኑ ቢደረግም አሠራሩ የቀለጠፈና ዘመናዊ መሆን ወቅቱ የሚያስገድደው ሁኔታ ነው። በ1963 ዓ.ም አባዬ ወይም ኤፌሶን በሚገኘው ወንዝ ላይ ሰው ላይ በሽታ የሚያሰፋፋ ባክቴሪያ ሲገኝ ተቋሙ ቪብሪዮ ኮሌራ ነው ለማለት አዳግቶት ናሙናው ፓሪስ ተልኮ ከተረጋገጠ በኋላ ነበር በይፋ በሽታው ኢትዮጵያ ውስጥ መግባቱ የተነገረው። ምክንያቱም ሠራተኞቹ ሥራ ከጀመሩ በኋላ በዓለም ውስጥ ያለውን ግኝት ለመከታተል የሚያነቡት ጽሑፍ ስለማያገኙና ተጨማሪ ሥልጠናም ስለማያገኙ ነው። መሣሪያዎቻቸውም ዘመናዊነት የተላበሱ አይደሉም።

የኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ አፍሪካ ውስጥ የገባው በክትባት መልክ ነው ተብሎ ተጽፏል። ስለሆነም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገቡትን መድኃኒቶችና ክትባቶች መመርመሩ የሚያስመሰግነው ነው። ኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ የተሟላ ድጋፍ ሊደረግለትና የኤች. አይ. ቪን መድኃኒት ለማግኘት ምርምር መጀመር ኃላፊነቱ ሊሆን ይገባል።

በተለይ አገሪቷ ገና ያልተነኩ ብዙ ዕጽዋቶቿ ባለቤት ስለሆነች የባህል መድሃኒቶችን ለመመርመር ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። እንዲያውም የበቁ ሰዎች "መድሃኒቱ እደጃችሁ ነው" እያሉ በመሮህ ላይ ናቸው።

ይህች ዓለም የቻለ የሚኖርባት (survival of the fittest) መሆንዋን ማወቅ ይኖርብናል። አለበለዚያ እንደ ቀይ ህንዶች ወይም እንደ አቦርጂኒስ እኛ አልቀን ሊሎች ሕዝቦች ይህችን ድንግል መሬት ይኖሩባታል።





# ምዕራፍ ፴፪

## ጃንሆይና ዲሞክራሲ

ዲሞክራሲን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበሩት አብርሃም ሊንከን ያብራሩት እንዲህ ብለዋል።

"Democracy is the government of the people, by the people for the people."

ትርጉሙም "ዲሞክራሲ የሕዝብ ፣ በሕዝብ፣ ለሕዝብ የሆነ መንግሥት ነው"

ይሁንና ዲሞክራሲ ብዙ የሚያጠቃልላቸው ጉዳዮች ስላሉት በዚህ ትርጉም ብቻ ለመወሰን ያስቸግራል። መንግሥት የሕዝብን መብት እየገፈፈ ግዴታውን ብቻ እንዳይቆልል ይወስናል። በጠቅላላው ውስጠ ሚስጥሩ ሥልጣንን የሕዝብ ማድረግ ነው።

የመንግሥት መዋቅር ሕዝብ በሚመርጣቸው ሳይፈልጋቸውም በሚሸራቸው ባለሥልጣኖች የሚገነባ መሆን ሲኖርበት ውሳኔም የሚሰጠው በአብዛኛው ድምጽ የሚደገፍ ሲሆን ነው። ያምሆኖ ግን የድምጽ ብዛታቸው ትንሽ ነው ተብሎ የጥቂቶችም መብት አይደፈርም። የሥልጣን መፍለቂያ ሕዝብ ሲሆን አስፈጻሚዎችን እንደሚመርጥ ሁሉ ሕግ አውጭዎችንም ይመርጣል።

ምንም እንኳን ጥንታዊው የንጉሥ ነገሥት መንግሥት በጥንቱ ሥርዓት መሠረት በውልደት ወይም በውርስ ሥልጣን ላይ የሚወጣበት ሥርዓት ስለነበረ በልምድ ትክክል ነው ተብሎ በወቅቱ በሕዝብ በመታመኑ እንደ ሥርዓት ሲሠራበት ኖሯል።

የዴሞክራሲን ሥርዓት በተግባር ለመተርጎም አስቸጋሪ ቢሆንም በቅን ልቡና ወደእሱ የሚወስድ መንገድ የከፈተ መሪ ሊመሰገን ይገባል። አዲሱ ሥርዓትም ሙሉ በሙሉ ያለ እንከን በትክክል ይሠራል ብሎ መጠበቅም ችኩልነት ይሆናል። ለመጀመሪያ ጊዜ ሚኒስትሮችን በ1898 ዓ.ም የሾሙትና የመንግሥትን ሥራ አከፋፍሎ ለመሥራት የሞከሩት አፄ ምኒልክ ነበሩ። ምንም እንኳን በ1911 ዓ.ም በመሃል ሰፋሪዎች አድማ ሚኒስትሮቹ ቢሻሩም ተመልሶ ሕግና ደንብ ወጥቶ አዳዲስ ሚኒስትሮች በጃንሆይ ተሹመዋል። አሠራር ላይ ሚኒስትሮቹን እንዲረዷቸውና እንዲያማክሯቸው የውጭ አገር ሰዎች ተቀጥረውላቸው ነበር። ከጠላት ወረራ በኋላ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንደገና ሲቋቋሙ ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ ሚኒስትሮች እየተሾሙ ሥራቸውን ማካሄድ ጀምረዋል።

ይህ አጀማመሩ ጥሩ ሆኖ የነበረው እርምጃ እየዳበረና እየተሻሻለ መሄድ ሲገባው ከጠላት ወረራ በኋላ ሕዝቡ ብዙ ሲጠብቅ መልሶ የንጉሡ ነገሥቱ ፍጹማዊነት እየጎላ በመሄዱ ምንም የተመቻቸ ሁኔታ ቢኖርም ሥልጣኔውን መልሶ መግታት ተጀመረ። በአጠቃላይ ሲታይ ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ የዴሞክራሲ ጭላንጭሉ ታይቶ ከሳቸው ዘመን በኋላ እንደገና ደብዛው ጠፍቷል። ምንም እንኳን ፍጹማዊ የንጉሡ ነገሥት መንግሥት ቢሆንም በየመሥሪያ ቤቶች የተመደቡት ሚኒስትሮች ባጀታቸውን ካስፈቀዱ በኋላ ሥራቸውን በነጻነት ይሠሩ ነበር። ስለሆነም እያንዳንዱ ሚኒስትር የነበረው ማዕረግና ክብር ነጻነት እንደነበረው ያስረዳ ነበር።

ከንጉሠ ነገሥቱ ዘመን በኋላ የነበረው የወታደር መንግሥት በየመሥሪያ ቤቱ አንዳንድ ቋሚ ተጠሪ መድቦ በተጨማሪም በሌላ የሚታዘዙ ካድሬዎች በመሰግሰግ ሚኒስትሮቹ ጥላ ቀሏቸው ለሥራው ሁሉ ወሳኝ ጠፍቶ አገሪቱ ወደፊት እንደመሄድ ባለህበት ሂድ ተጀመረ። የብዙ ሚሊዮን ብድር በአገሪቷ ስም የሚፈርሙት ሚኒስትሮቹ ሳይታመኑ ቀርተው የሚኒስትሩ መኪና በሾፌሮች ቁጥጥር ሥር እንዲውልም ተደርጎ ነበር።

በሙያ ማኅበራት በኩል የሂድን እንደ ኾነ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት እያንዳንዱ የሙያ ማኅበር ራሱ በመረጠው ወኪሉ ይንቀሳቀስ ነበር። በደርግ ዘመን መንግሥት ግን የገኘው ወገኖች



ተመርጠው የመንግሥት አፈቀላጤ ይሆኑና አሽከርነቱ ሲመራቸው መጨረሻ ላይ አገር ጥለው ይጠፋሉ፣ ሲዘላብዱ ተይዘው ይታሰራሉ፣ ወይም ይገደላሉ።

ተማሪዎች የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት እንደሚቃወሙ እየታወቀ ከሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶች አንስቶ እስከ ዩኒቨርስቲ የየራሳቸውን ማኅበራት ሥራ አስኪያጆች እየመረጡ ዲሚክራሲያዊ እንቅስቃሴን ይለማመዱ ነበር። በደርግ ዘመን ግን በከፍተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶች ቀርቶ በዩኒቨርሲቲዎች የዴሞክራሲያዊ ማኅበሮች ሊቋቋሙ አልቻሉም።

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት ለፓርላማ ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ ተመራጮች እየዞሩ ለመራጩ ዓላማቸውን እያስረዱ ይወዳደሩ ነበር። ከሳቸው ዘመነ መንግሥት በኋላ የተመራጮች ፎቶግራፍ በየቦታው ይለጠፍና ዓላማቸውንም ለመራጩ ሳያስረዱ ይመረጣሉ። አመራረጡ ላይም መራጩ ሕዝብ ቅሬታ ነበረው። ሕዝቡም አንዳንዴ ያልመረጠው ሰው እንደሚመረጥ ያውቃል።

በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ሊቋቋም ያልቻለው የፖለቲካ ፓርቲ ነበር። በደርግ ዘመን ፓርቲዎች ተመሥርተው መጨረሻ ላይ በኮሙኒስት ሥርዓት አገሪቱ ስለምትመራ አንድ ፓርቲ አገሩን ሲያስተዳድር ቆየ። እሱውም የገዥዎች ስብስብ ስለሆነ ወዛደሩን እወክላለሁ ቢልም የሚያጅበው ሰላነሰ በመንግሥት ሥልጣን ከአንድ እርከን በላይ ያሉ ባለሙያዎች ሁሉ በግድ አባል ካልሆኑ ከሥራቸው ይነሱ ነበር። መጀመሪያ ላይ ተቋቁመው የነበሩት ማወናበጃ ፓርቲዎችም ከሰሙና አባሎቹ በአሐዳዊ ፓርቲው በኢሠፓ ተዋጡ።

ብዙውን ጊዜ ስለዴሞክራሲ የሚወተውቱ መንግሥታት ዴሞክራት አለመሆናቸውን ነው የሚያመለክቱት። ለምሳሌ ምሥራቅ ጀርመን ዴሞክራት ነን ለማለት የጀርመን ዴሞክራቲክ ሬፑብሊክ ተብለው ሲጠሩ የምዕራብ ጀርመን ግን የጀርመን ሬፑብሊክ ተብለው ይታወቁ ነበር። እንዲሁም የሰሜን ኮሪያ አሁን ድረስ የኮሪያ ዴሞክራቲክ ሬፑብሊክ ሲባሉ የደቡብ ኮሪያ ግን የኮሪያ ሬፑብሊክ ተብሎ ይጠቀሳል። ኮሙኒዝም በዴሞክራሲ የሚያምን ፍልስፍና ሆኖ አመራሩን የጨበጡት በተግባር ላይ በዴሞክራሲ ላይ በማሾፋቸው ከብዙ ደም መፍሰስ በኋላ የተገኘው ውጤት ተቀለበሰ። ይህም የሚሆንባቸው ምክንያቶች

ሦስት ናቸው። አንደኛው አመራር ላይ ያሉት ሥልጣን በሚጨብጡበት ወቅት ብዙ ደም ስለሚያፈሱ ለመውረድ አየፈሩ ነው። ሁለተኛው ሥልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ሃብት ውስጥ ስለሚነከሩና ድሎት ስለሚለምዱ ድህነትን ስለሚፈሩ ነው። ሦስተኛው የሰው ልጅ ራስ አፍቃሪነት (egoism) ሥልጣን ላይ በደረሱ ሰዎች የተደበቀ ፍላጎት ስለሚኖር እነሱን የሚያሰወግድ ሁኔታ በምንም መልኩ ሥራ ላይ እንዳይውል ስለሚከላከሉ ነው።

እንደ ጥንቱ ነገሥታት የቡድኑ ቀንደኛ መሪ ሲሞት ለልጁ ሥልጣኑን በተዘዋዋሪ መንገድ ያወርሳል። የሰሜን ኮርያው ኘሬዚዳንት ሲሞት የተካው ልጁ ነው። ማኦ ትሴቱንግም ሊያወርስ የፈለገው ከቲያትር ቤት መድረክ መርጦ ያገባትን ሚስቱን ነበር እንጂ ደንበኛ ዴሞክራሲያዊ ውድድር ተደርጎ ተተኪዎችን አላስመረጠም። ሳዳም ሁሴን ቀን ከዳው እንጂ ልጆቹ እንዲተኩት አዘጋጅቶ ነበር። የሶሪያው መሪ ልጁን ተክቶ ነው ያለፈው። የግብጹስ ሙባረክ ብቻውን ለምርጫ እየቀረበ መመረጡ ዲሞክራት ያሰኘው ይሆን? እሱስ የሚተካውን ልጁን እያዘጋጀ አይደለምን?

በአንጻሩ በዴሞክራሲ በሚያምኑ አገሮችም የዴሞክራሲ ሥርዓት ፍጹምነት የለውም። አሜሪኮኖችም ዴሞክራትና ሬፖብሊካን የሚባሉ ሁለት ኃይለኛ ፓርቲዎች አሏቸው። ሁለቱ ፓርቲዎች አንድ ከመሆናቸው የተነሳ ስም እንኳን ተቀያይረዋል። ሌላ ፓርቲ እንዳይገባባቸው የአሜሪካንን ሕዝብ አፍነው ዞዱን ብቻ እየሞሉ ስለሌላው ዓለም እንዳያውቅ ተጽዕኖ አድርገውበት ከሌላው የዓለም ሕዝብ ጋር ግንኙነቱን እያሻከሩት አመራሩን እንደዱላ እየተቀባበሉት ይገኛሉ። በተለይ የሪፖብሊካን ፓርቲ የነጭ አክራሪነት ጠባይ የሚታይባቸውና የጦረኝነት ባህርይ የሚታይባቸው ናቸው ተብለው ይተቹበታል። በሌላው ዓለም ሕዝብ ዘንድ አሜሪካን አገር ፍጹም የሆነ ዴሞክራሲ ያለ ይመስላል እንጂ በዘዴ ሕዝቡ እየተጨቆነ ነው። እስከ 60ዎቹ አሥርተ ዓመታት ድረስ የአሜሪካ ሕዝብ አጭር ሞገድ (ሾርት ዌቭ) ሬዲዮ እንዲኖረው አይፈቀድለትም ነበር። አንዳንድ የነበራቸውም ሰዎች እንዲያስመዘግቡ ይታዘዙ ነበር። በኋላ ግን ውጭ የኖረውና ተመላሹ ወታደር በብዛት እየያዘ ስለገባና ለቁጥጥር ስላላመቻቸው ትተውታል። አሜሪካ ውስጥ ሬዲዮ የሚገዛ ሰው ወይም መኪና ውስጥ የሚገጥሟቸው ሬዲዮኖች የመካከለኛ ሞገድና የኤፍ ኤም መቀበያ ብቻ ነው ያላቸው። ምክንያቱም የሩቅ ጣቢያዎችን ሕዝቡ



እንዳይሰማ ስለሚፈልጉ ነው። የቴሌቪዥን ጣቢያዎችም የአካባቢ ወሬ ብቻ ነው የሚያወሩት። በንጽጽር እንደ አሜሪካ ሕዝብ ስለሌላው ዓለም ጉዳይ የማያውቅ ሕዝብ የለም ለማለት ያስደፍራል። አሜሪካኖች በውጭው ዓለም ችግር በተፈጠረ ቁጥር በፖለቲከኞችና ኤክስፐርት ነን ባዮች ሲያካልቡትና ግራ ሲያጋቡት ይታያል።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ጭላንጭል ታይቷል ማለት ይቻላል። ምንም እንኳን ንጉሡን በተመለከተ መናገር የሚቻለው ጥሩ ጥሩውን ብቻ እንጂ መንቀፍ፣ መተቸት፣ መቀለድ ወይም ያልኾነ ምስል ማዘጋጀት ግን ያስገርፋል፣ ያሳስራል፣ ወይም ሊያስገድል ይችላል። ለምሳሌ አቶ ነፀረ ወልደ ሥላሴ የተባሉ ታዋቂ የብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድን ተጫዋች "ከጃንሆይ አስተዳደር የይድነቃቸው አስተዳደር ይሻላል" ብለው ስለተናገሩ አራዳ መካከል በሕዝብ ፊት ተገርፏል። በተረፈ እሳቸውን ሳይነካ ሚኒስትሮችን ብቻ የሚቃወም ከኾነ መናገር ይቻል ነበር። በተለይ የከተማው ወፈፌዎች የልባቸውን ሲናገሩ ቆይተው ራሳቸውን ከአደጋ ለመከላከል "ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ!" ካሉ ማንም አይነካቸውም ነበር። እስከተለውም በደርግ ሥርዓት ጭቆናው ከፋ እንጂ የተሻሻለ ነገር አልታየም። በተቃራኒው በኢሕዴግ ዘመነ መንግሥት ሥርአቱንና መሪዎቹን መተቸት ተችሎ እየተሠራበት ነው።

በጠቅላላው ሲታይና ያለፈውን ሁኔታ በማገናዘብ ጃንሆይን የምንወቅሳቸው የነበረውን የንግሥና ሥርዓት በመከተል ልጃቸውን ለምን አላነገሡም ወይም ደህና የጀመሩትን ዴሞክራሲ ዳር ባለማድረሳቸው ነው። ራሳቸው በ1921 ዓ.ም ንጉሥ የተባሉት ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ በሕይወትና በሥልጣን ላይ እያሉ ስለ ኾነ ለልጃቸው ንጉሥነት ለመስጠት ከሰማንያ ዓመት በላይ ሆነው ለምን አልፈለጉም የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አይቻልም። ስለዚህ ነው የጥንቱን ሥርዓት ገርስሰው አዲሱን ሥርዓት ሳያመቻቹ ብዙ ችግር ያለባትን አገር እያወቁ ከፍት ቤት ትተው ለገዳይና ለዘራፊ ጣሉን የሚል ቅያሜ በሕዝቡ ላይ ያሳደሩት። ከእሳቸው ዘመን በፊት የተሻለ ንጉሥ እንዳልነበረና ምንም እንዳልተሠራ የሚፈልጉትን ያህል ከእሳቸውም በኋላ ጎልቶ የሚታይ መሪ ተነስቶ የእሳቸውን ዘመን ታሪክ የሚያስንቅ እንዳይኖር ይጥሩ እንደነበረ ድርጊታቸው ይመስክራል።



# ምዕራፍ ፴፫

## የጃንሆይ ተቃዋሚዎች

እንደሚታማው ሁሉ አቤቶ ኢያሱ ሃረማያ (ዓለምማያ) ሃይቅ ላይ ተፈሪና ዘጠኝ ሰዎች ይሄዱባት የነበረውን ጀልባ አስሸንቁሮና ተሳፋሪዎችን አደጋ ላይ ጥሎ ከሆነ እውነትም ለተፈሪ ጠላት ነው። አለበለዚያ ግን የመንግሥት ሥልጣን በጨበጠ ጊዜ ብዙ ማድረግ ሲችል ተፈሪን ከሐረር ከመሻር በስተቀር አልነካም። ስለሆነም ልጅ ኢያሱ የተፈሪ ጠላት ነበር ከማለት ተፈሪ የልጅ ኢያሱ ጠላት ነበሩ ማለት ይቀላል።

ንጉሥ ሚካኤል ልጃቸው ያለ ኃጢያቱ ሲወነጀልና አያቱ ካወረሱት መንግሥት ሲሻር 60,000 የወሎ ጦር ይዘው ለዘመቻ መምጣታቸው በጠላትነት ሳይሆን በልጃቸው በኩል ራሳቸውም እንደተበደሉ ስለቆጠሩት እሳቸውን እንደጠላት ማየት ተገቢ አይሆንም።

ተፈሪ ራስ ተብለው የልጅ ኢያሱን ሥልጣን ሲወስዱ ሊቃወሙ ፈልገው ያልተቻላቸው ብዙ ናቸው። ብዙዎቹ ሁኔታውን ፈርተው ዝምታን ስለመረጡ ቁጥራቸው አይታወቅም። እዚህ ላይ ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ እንኳን ልጅ ኢያሱን ለማውገዝ አልቻኮሉም ነበር። ነገር ግን አንዳንዶቹ በየምክንያቱ እየገነፈለባቸው ተቋውሚቸውን የገለጡና ለእስር ለግርፋት፣ ለግዞት የተዳረጉና ለድርጊታቸውም ልዩ ልዩ ምክንያቶች እየተሰጡ የሰዎቹ ዓላማ ተዛብቶ የተነገረባቸው ቢኖሩም በተለይ በየምክንያቱ በይፋ በጠላትነት የተፈረጁት የሚቀጥሉት ናቸው።



## ፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ

የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት ብልሁ ፊታውራሪ ኃበተ ጊዮርጊስ አባ መላ በመባል ይታወቁ ነበር። ፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ ብልህ በመሆናቸው ችግር ሲፈጠር አፄ ምኒልክ ጉዳዮችን እሳቸው ዘንድ ይልኩ ነበር። በኬኒያ ወሰን በኩል የኢትዮጵያን ድንበር አልፈው ስላገኟቸው "ሁለት የእንግሊዝ መኮንኖች በኢትዮጵያውያን ወሰን ጠባቂዎች ስለተገደሉ የተገደሉበትን ስፍራ ለእንግሊዝ አስረክቡ" የሚል የጉልበተኛ ጥያቄ ሲቀርብ መልስ ቢታጣ መልዕክተኞቹ ወደ ፊታውራሪ ኃብተ ጊሮርጊስ ተላኩ። እሳቸውም በጥያቄው መሠረት የተባለውን ስፍራ ለእንግሊዝ ለመልቀቅ ተስማምተው በተራቸው ሌላ ጥያቄ አቀረቡ። ጥያቄያቸውም "ልጃችን ዓለማየሁ ቴዎድሮስ በናንተ ወታደሮች ተወስዶ የሞተበትን የሎንዶንን ከተማ ልቀቁልን" ስላሉ መልዕክተኞቹ አፍረው ተመለሱ።



ፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ

በመጀመሪያው ላይ ተፈሪን ለመሾም አስተባብረዋል። ፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ወግ አጥባቂ ስለነበሩ ተፈሪ የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማስገባት ሽር ጉድ ማለታቸውንና አንዳንድ ሰዎች ላይ የሚወሰደውን እርምጃ ስለጠሉት ወደ ተቃዋሚነት ጎራ ዞሩ። በ1919 ዓ.ም ሞተው አራዳ ጊዮርጊስ ተቀበሩ።

## ደጃች ባልቻ ሳፎ (አባ ነፍሶ)

የአድዋው ጀግና ደጃች ባልቻ ሳፎ ከጀግንነታቸው የተነሳ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ግጥም ተገጥሞላቸዋል።

ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ
መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ



ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ (አባ ነፍሶ)

ደጃች ባልቻ ራስ ተፈሪን መጥላታቸውን አልደበቁም። ቢሆንም ከጥላቻ በስተቀር ያደረጉት ምንም ነገር አልነበረም። ተፈሪ ግን አቂመው ስለነበረ ሥልጣን በያዙ ጊዜ ደጃች ባልቻን በግዞት ወደ አምቦ መንገድ አስወስደው ሚሊዮን እስከገባ ድረስ አቆይተዋቸዋል። በወረራውም ወቅት ምንም ተፈሪን ቢጠሉም ለአገራቸው ነፃነትና የሚወዱቸው የምኒልክ ቤተ መንግሥትን ጠላት ሲይዘው ለማየት ስላልፈለጉ በ80 ዓመት ዕድሜያቸው ወደ አርበኝነቱ ገብተው አዲስ አበባን ለመያዝ በሰበታ በኩል እስከ ንፋስ ስልክ ድረስ ጠላትን አጥቅተው ነበር። ነገር ግን በሲላ አቅጣጫ የዘመቱት ስላልተሳካላቸው የያዙትን ቦታ ትተው መመለስ ግድ ሆነባቸው። ሆኖም ወጨጫ አካባቢ ውጊያቸውን ቀጥለው በጠላት እጅ ተገደሉ። የነበራቸው ትልቅ የአገር ፍቅር ታሪክና ጀግንነት እንዲታወስ ስለታመነበት አንድ ሆስፒታል አዲስ አበባ ውስጥ ተሰይሞላቸዋል።

## ሊጋባ በየነ ወንድማገኘሁ

ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ እያሉ ከአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ትዕዛዝ አልቀበልም ብለው የተነሱ ሊጋባ በየነ ነበሩ። የሊጋባ በየነ አቋም "ማን ተፈሪን እንደራሴ አድርጎ ሾመውና የንግሥተ ነገሥትን ሥልጣን ይሻማል?" ብለው ነበር የተነሱት። ሁሉም የሥልጣኑን ሚዛን እየየ ከራስ ተፈሪ ጋር ስለተደረበ ምስኪኑ ሊጋባ በየነ የተረፋቸው በአደባባይ መገረፍ ነበር።



## በጅሮንድ ውብሸት ኃይሌ

በ1912 ዓ.ም እነ በጅሮንድ ውብሸት ኃይሌ፣ የፖሊስ አዛዡ አለቃ ገብሩ ሌሎችም መኳንንቶች መንግሥት ለመገልበጥ አድማ ሲመቱ ተያዙና ለፍርድ ቀረቡ። የእነሱም ክስ ራስ ተፈሪ አገሪቱን እየሸጠ ነው የሚል ተቃውሞ ነበር። ለዚህም ምክንያት የሆናቸው ራስ ተፈሪ ለፈረንጆች የሰጧቸው የሞኖፖል ውሎች ናቸው። በዚህ ሳቢያ በአድመኝነት ተይዘው ተፈርዶባቸው ታሰሩ።

## ደጃዝማች አባ ውቃው

የግቢ ዘበኞች አለቃ ደጃች አባ ውቃው ራስ ተፈሪን ለማንገሥ ሰዎች ሲያድሙ ሰሙና ለንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ተቆረቆሩ። ራስ ተፈሪን ለመያዝ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱን ፍቃድ እንዲሰጡዋቸው ቢጠይቁ ንግሥቲቱ ራስ ተፈሪን እያማከሩ ምስጢር በማባከናቸው ነገር አበላሹ። በዚህን ጊዜ አባ ውቃው ቤተ መንግሥት ውስጥ ሸፍተው ከብዙ ድርድር በኋላ ንግሥቲቱ ነገሩን እንዲተው ቢያዙቸው "እኔ አልነግሥ ለእርስዎ ብዬ ነው እንጂ" ብለው መጨረሻ ላይ እጃቸውን ሰጡ። በዚህ ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ በስጦታ የመጣችው ታንክ በግቢው መካከል ተሰልፋ ሚሲዮናዊው የታንኩ ሾፌር አባ ውቃው የሸፈቱበትን የእንቁላል ቤት ልደርምሰው ብሎ ራስ ተፈሪን ጠይቆ ነበር።



ደጃች አባ ውቃው

## ራስ ጉግሣ ወሌና የቋና ጦርነት

ውሸት ነው የተባለው የተፈሪ መንገሥ ጉዳይ ዕውነት መሆኑን የተረዱት የንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ተወዳጅ ባል የነበሩት ራስ ጉግሣ ወሌ በተፈሪ ላይ አኮረፉ። ራስ ጉግሣ ወሌ ወግ አጥባቂ ስለነበሩ በብዙ ምክንያቶች ለማመጽ ይዘጋጁ በነበረበት ወቅት ንጉሥ ተፈሪ ወደ አዲስ አበባ

እንዲመጡ ቢያዟቸው በእንቢታ ቀሩ። በኋላ ራስ ሙሉጌታን አዘምተውባቸው ራስ ጉግሣ በጦርነት ላይ ተገደሉ።

## ወ/ሮ ፀሐይ ወርቅ ዳርጌ

ወ/ሮ ፀሐይ ወርቅ ዳርጌ ለልጅ ኢያሱ፣ ለንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱና ለራስ ተፈሪ እኩል ዘመድ ቢሆኑም በልጅ ኢያሱ መሻርና በአዲሱ ሹመት ስለተከፉ ተፈሪን ለማስገደል ሲዶልቱ ተይዘው በእስራት ተቀጡ።

## ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት

ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት አፄ ምኒልክ ታመው ቀሳውስት ሱባዔ ገብተው በነበረበት ወቅት ከእንጦጦ ራጉኤል ከመጡት ዲያቆኖች አንዱ ናቸው። ጣሊያን ሲመጣ የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ዋና ዲሬክተር ነበሩ። ደጃዝማች ታከለ ደፋርና ሕዝብ ፊት መናገር የሚችሉ ሰው ስለነበሩ በመሃል ሰፋሪዎች (የመንግሥት ሠራዊት) ዘንድ ለደጃች ተፈሪ ድጋፍ በማሰባሰብ በኩል በጣም ረድተዋል። ማይጨው ሲዘመት ፀጥታ ለማስጠበቅ ሲባል አዲስ አበባ ተመድበው ሳይዘምቱ ቀርተዋል።

ደጃዝማች ታከለ የንጉሡን በስደት መሄድ ሲሰሙ እንደሸሸት ስለቆጠሩት በጣም ተናደዱ። በዚህ የተነሳ የሪፑብሊክ መንግሥት እንዲቋቋም ጥረት ማድረግ ጀመሩ። ጎጃም በአርበኝነት በነበሩ ጊዜ ከነሻለቃ መስፍን ስለሺ ጋር በዚሁ በሪፓብሊክ ጉዳይ አለመግባባት ፈጥረው ሽጉጥ ተማዘዙ። ጎንደርም ላይ ይህንን ሃሳብ በአርበኞች መካከል እያነሱ ስላስቸገሩ በእግር ብረት ታስረው ነበር። ኬንያም ሄደው ስደተኞችን በማነሳሳት ላይ በነበሩ ጊዜ እንደበታቸው ይማርክ ስለነበረ እንግሊዞች ስላልተደሰቱበት አስረዋቸውም ነበር። ይሁንና አምስቱን ዓመት በአርበኝነት ካሳለፉ በኋላ ንጉሥ ነገሥቱ ሲመለሱ አብረው ገቡ። ጃንሆይ ዘመዳቸውን ወይዘሮ ምንትዋብን ቢድሩላቸውም ለንጉሠ ነገሥቱ ያላቸውን ጥላቻ መሸሸግ አልቻሉም። በ1962 ዓ.ም በሰበታ መንገድ ላይ ፈንጂ ቀብረው ንጉሠ ነገሥቱ በዚያ ሲያልፉ ሊያስገድሏቸው ተዘጋጅተው እያለ ምስጢሩ ወጥቶ እጃቸውን እንዲሰጡ ቢጠየቁ፣ አሻፈረኝ ቧማለት ሕይወታቸውን በገዛ እጃቸው በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ አጠፉ።



## ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ

ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የልጅ ልጅ ናቸው። ሐምሌ 16 ቀን 1942 ዓ.ም የመንግሥት ግልበጣ ለማድረግ በውጥን ላይ እያሉ ከመካከላቸው ደጃች ገረሱ ዱኪ ምስጢር አውጥተው አስይዘዋቸዋል። ቢትወደድ ነጋሽ እራሳቸው በሁለት በኩል ከመሳፍንት ወገን የሚወለዱ በመሆናቸው ምናልባት ሕዝቡ ይገዛልኛል ብለው ይሆናል። ዓላማቸው ግን ምን እንደነበር የተገለጸ ነገር የለም። የተያዙት ገና በአድማ ላይ እንዳሉ ስለነበረ በእስራት ብቻ እንዲቀጡ ተደረገ። አብረዋቸው ከተደማደሙት ውስጥ አንዱ ዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸው የነበሩትና ደርግ የፈታቸው የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስም ናቸው። የመቶ አለቃ በቀለ ስዊትዘርላንድ የመድፈኛ ትምሕርት ለመማር ሄደው ለማይጨው ጦርነት በእናት አገር ጥሪ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ማይጨው የዘመቱ ሰው ነበሩ። አባታቸውም በአድዋ ዘመቻ ላይ የተሳተፉ እንደነበሩ ይታወቃል። የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ በሪፓብሊክ አገዛዝ የሚያምኑ እንደነበሩ ግልጽ ነበር። ወህኒ ቤት በነበሩ ጊዜ የእስረኛው ሚካኤልን ቤተክርስቲያን በእስር ቤቱ ቅጥር ግቢ ያሠሩ እሳቸው ናቸው።

## በላይ ዘለቀ

በላይ ዘለቀ የልጅ ኢያሱ አንጋች የነበሩት የባሻ ዘለቀ ላቀውና የወይዘሮ ጣይቱ ሐሰኔ ልጅ ናቸው። የልጅ ኢያሱ መንግሥት ሲፈርስ ባሻ ዘለቀ ሚስታቸው አገር ወሎ ክፍለ አገር ጅሩ ወረዳ መኖር ጀመሩ። አንድ ቀን በድንገት ሰው በጃቸው ያልፍና ቤተሰባቸውን ይዘው ወደ ትውልድ አገራቸው ጎጃም ገብተው በግብርና ሲኖሩ ሌላ ችግር ተፈጠረ። ከወንድሞቻቸውና ከወዳጆቻቸው ጋር ሆነው እቤት ውስጥ ሲጫወቱ በፊታውራሪ እምቢ አለ የሚመራ የራስ ኃይሉ ሌባ አዳኝ ጓድ ከበባቸው። "እጅህን ስጥ" ሲባሉ "አሻፈረኝ" በማለት ተታኩሰው በርካታ ሰው ከገደሉ በኋላ ባሻ ዘለቀና ጓደኞቻቸው አቶ መርሻ ሞቱ። ያም የሌባ አዳኝ ጓድ ሁለቱን ሬሳ መኖሪያ ቤታቸው ደጃፍ ላይ ሰቀለ።

በላይ በልጅነት ዕድሜው አባቱ ላይ የተደረገውን ጭካኔ ተመልክቶ ቂም ይዞ አደገ። በዚሁ በቤተሰቡ በደረሰው በደል ከሌሎች ልጆች ተገልሎ ቄስ ትምሕርት ቤት ገብቶ እንኳን ሳይማር እንዲሁ በመሃይምነት እናቱን ከሴሎቹ ወንድሞቹ ጋር እየረዳ ኖረ። በላይ እንደተወለደ ስም ሲያወጡለት አባቱ "ተመስገን" ሲሉ አንዲት ጎረቤት "አስጨናቂ" እናቱ ግን "በላይ" ብለው አወጡለት። ዕድሜው ከፍ ሲል የአባቱን ገዳይ ፊታውራሪ እምቢ አለን ለመግደል ሲሄድ ቢያጣቸው ጓዱን መንገድ እየመራ ይዞ መጥቶ የነበረውን ግራዝማች ደርሰህን ገድሎ ሸፈተ። ጣሊያን ኢትዮጵያን ሲወርር በመላው አገሪቱ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ ሽፍቶች ጃንሆይ ምሕረት አድርገው ነበርና በዚህ ምክንያት ወደ አርበኝነቱ ተሰማራ። ጣሊያን ድል እንደተቀዳጀ በየባላገሩ እየዞረ መሣሪያ አስረክቡ እያለ ሲያውጅ በላይ አሽከሮቹን አስከትሎ ገቢያ እየመጣ ማሣሪያችሁን እንዳታስረክቡ፣ መሣሪያውን ያስረከበ ሰው አኛ ቤቱን ንብረቱን እናቃጥላለን እያለ ሲለፍፍ ሕዝብ እየፈራውና እያከበረው ሄደ።

በላይ ዘለቀ አጠር ያለና ቀይ፣ ጭንቅላቱ ትልቅ፣ ሰውነቱ ቀጭን፣ ሰልካካና መልከ መልካም ሰው ነበር። የተማረም ስላልነበረ ጽሑፍ ይነበብለትና ከተስማማ ጊዮርጊስን ብሎ ከማለ እንደፈረመ ይቆጠርለት ነበር። የአሽከሮቹ ሥነ ሥርዓት የተለየ ነበር። ከድል በኋላ አዲስ አበባ መጥቶ ጉለሌ መንግሥት ለማረፊያ በሰጠው ከንቲባ ማተቤ መኖሪያ ቤት ውስጥ በነበረ ጊዜ አሽከሮቹ ግራና ቀኝ ተሰልፈው እሱ ብቻውን ለረጅም ሰዓት ዝምታ በሰፈነበት ሁኔታ ይቀምጥ ነበር። አለባበሱ ገበርዲን ኮትና ጠባብ ሱሪ ሲሆን ነጠላ ይደረብበታል። ለእግሩም መጫሚያ ነበረው። መጨረሻ ላይ ሲሰቀልም የለበሰው ይኼንኑ ነበር።

በጣሊያን ወረራ ጊዜ በጎጃም ታላቅ ሠራዊት የነበረውና ጀብዱ በመሥራት ስመ ጥር አርበኛ ሆኖ ነበር። ምንም እንኳን መጀመሪያ ላይ የጃንሆይን መመለስ ቢቃወምም ከስደት መልስ ደብረ ማርቆስ ሲደርሱ 15,000 ጦር አሰልፎ ተቀበላቸው። ታዲያ እንግሊዞችን ከጣሊያን ለይቶ ስለማይመለከታቸው አይወዳቸውም ነበር። እነሱም ይኽንኑ ቢያውቁም በጀግንነቱ ያከብሩት ነበር። በአርበኝነቱ ዘመን ለተከታዮቹ የተለያየ ሹመት እስከ ራስ ማዕረግ ድረስ ሲሰጥ የገዛ ወንድሙ "ሹመቱን ሁሉ ጨርሰህ ለአንተ ምን ሊቀርህ ነው?" ሲሰው



"እኔንማ እናቴ በላይ ብላኛለች" አሰው ይባላል። ሆኖም ሕዝቡ ልዑል በላይ እስከማለትም ደርሶ ነበር። ይኽም የሆነበት ምክንያት የንጉሥ ሱስንዮስን ዘውድ፣ አልጋና ሉል ከዲማ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አውጥቶ ታህሣሥ 8 ቀን 1932 ዓ.ም በዋለው ክብረ በዓል ላይ ሚስቱን ምንትዋብ ውቦ ንጉሤን እቴጌ በማለት ራሱን ደግሞ ልዑል ብሎ በመሾሙ ነበር።

ልጅ በላይ ዘለቀ ከጠላት መወገድ በኋላ አዲስ አበባ ሲኖር ከጠላት የማረከውን መኪና ጣራውን ቀዶ የኢትዮጵያን ባንዲራ እያውለበለበ ሲሄድ ሰዎች "ተው አይሆንም!" እያሉ ቢመክሩትም እሱ ግን "እንኳን እኔ ለአገሬ የተዋጋሁት ይቅርና ሸሽቶም የሄደው ባንዲራ ያውለበልባል" እያለ ይመልስ ነበር።

አርበኛው ሁሉ መሣሪያውን ከፈታ በኋላ ሹመት ሲደለደል በላይ ዘለቀ እንደ ሥራዬ ውጤት ሹመት አገኛለሁ ብሎ ሲጠብቅ በደጃዝማችነት ማዕረግ የብቸና ወረዳ አገረ ገዥነት ተሰጠው። ከእሱ በታች ጀብዱ የሠሩ የተሻለ ማዕረግ ከማግኘታቸውም በላይ ጎጃምን በአገረ ገዥናትና በእንደራሴነት የራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት የወንድም ልጅ ራስ ኃይሉ በለው ተሾሙ። ልጅ በላይ የወረዳ ገዥነቱን ሹመት ሲያስጸድቅ ደብረ ማርቆስ ሲደርስ ሕዝቡ በጣም ይወደው ነበርና እሱን ለመቀበል ትልቅ ግብዣ አድርጎ ጠበቀው። የጎጃሙ ገዥ ራስ ኃይሉ በለው የበላይ ዘለቀ በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅ መሆን አስግቷቸው በሥራው ላይ ይፈታተኑት ጀመር።

በላይ ዘለቀ በባለሥልጣኖች ወከባ አኩርፎ በተፈጠረው አለመግባባት አመጸ። የአወረዳውንም ሕዝብ የመንግሥት ግብር እንዳይከፍል ፈቀደለት። ኃይለኛ መሆኑን የሚያውቁት ባለሥልጣኖች አውቀው ደም ለማቃባት ወታደር ሲልኩበት ተታኩሶ ጥቂት ሰው ሞተ። በላይ የግዛቱን ሕዝብ ሰብስቦ "እኔ ወደፊት የምገዛው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ይገዙት የነበረውን አገር ነው። ለሚም በጠላት ጊዜ እጠራበት በነበረው ልዑል በላይ ይሆናል" ብሎ አወጀ። ከዚህም በኋላ ሶማ ሸርሃ ገብቶ ሸፈተ። በዚህም ምክንያት የክብር ዘበኛ ወታደር ተልኮ ከመጠነኛ ፍልሚያ በኋላ ተይዞ ታሠረ።

በ1937 ዓ.ም ከእሥር ቤት ከ500 እስረኞች ጋር ሰብሮ በማምለጥ ከፊታውራሪ አድማሱ ጋር ተገናኝቶ ለሽፍትነት ሲዘጋጁ የአራተኛ

ክፍለ ጦር ወታደሮች ደርሰውባቸው ልጅ በላይና ጥቂት ሰዎች ተያዙ። ፊታውራሪ አድማሱ ግን እጃቸውን ሳይሰጡ የተደበቁበት ዋሻ ውስጥ የማያቋርጥ ነስር ስለፈሰሳቸው ሕይወታቸው አለፈ። በዚሁ ጥፋቱ ችሎት ላይ ቀርቦ የሞት ፍርድ ስለተፈረደበት አዲስ ከተማ የዚያን ጊዜ በግ ተራ አሁን የአዲስ ከተማ ትምሕርት ቤትና አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ ቅዳሜ ጥር 5 ቀን 1937 ዓ.ም በስቅላት ተቀጣ። የተሰቀለበት ገመድ በአንገቱ በስተጀርባ በመሆኑ ምክንያት ብዙ ተሰቃይቶ ሞተ። ቅጣቱን ያስፈጸሙት ኮሎኔል መንግሥቱ ንዋይ ነበሩ።

ከሞት ቅጣቱ በኋላ መንግሥት የአርበኝነቱን ውለታ ለመክፈል ጎሹን፣ ባሕሩንና መልአኩ በላይ የተባሉትን ወንድ ልጆቹን በነጻ አዳሪ ትምሕርት ቤት ከማስገባቱም በላይ የኪስ ገንዘብ በየወሩ 30.00 ለእያንዳንዳቸው እየሰጠና በዓመት ሁለት ሙሉ ሱፍ ልብስ እያለበሰ አስተምሯቸዋል።

የበላይ ዘለቀ ተቆርቋሪዎች ብዙ እንደሆኑና በየጊዜውም በየዘፈኑ ስሙ ይታወስ እንደነበረ ይታወቃል። ስለሆነም እንደተሰቀለ የሚከተለው ተገጥሞለታል።

ተሰቀለ ቢሉኝ ሽጉጡ ነው ብዬ
ተሰቀለ ቢሉኝ ጠመንጃው ነው ብዬ
ለካስ በላይ ኖሯል ትልቁ ሰውዬ

አከታትሎም ዘፈን ቢዘፈንለትም በይበልጥ የጃንሆይ ሥልጣን መውረጃ ገደማ ላይ "በላይዬ! ጀግናው በላይዬ!" እየተባለ በሰፊው ይዘፈን ነበር።

## አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ

አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ የራጉኤል ዲያቆን የነበሩና በኋላም አባታቸው አለቃ በነበሩበት ወጨጫ ማርያም በድቁና ያገለገሉ ሲሆኑ በየጋዜጣው ላይ በሚጽፏቸው ጽሑፎች ጃንሆይ አውቀዋቸው የመንግሥት ሹመት እየሰጧቸው ሲሠሩ የነቀዙ ባለሥልጣኖችን እያሳጡ በንጉሡ ይደነቁ ነበር። መጨረሻ ላይ ግን ንጉሠ ነገሥቱ ከሁሉ ተጣልተው የማይችሉ መሆናቸውን ስላወቁና ከተያያዙት ንቅዘትን የመዋጋት ተግባር ንቅንቅ እንደማይሉ ስለታወቀ በአምባሳደርነት



ተሹመው ወደ ውጭ እንደተወረወሩ ሲረዱ የጃንሆይንም አስተዳደር ጠሉት። በመጨረሻ ስደተኛ ሆነው የጃንሆይን መንግሥት በመቃወም ኖረው ብዙ ጽሑፎችም ሲጽፉ ቆይተው በአሜሪካን አገር አርፈዋል።

አሜሪካን አገር በስደት ሲኖሩ የደርግ መንግሥት ሥልጣን ይዞ ንጉሠ ነገሥቱን መውቀስ ሲያበዛ ተመልክተው ለርዕሰ ብሔሩ ለጀኔራል ተፈሪ በንቴ የጽሑፍ መልዕክት አስተላለፉላቸው። ጽሑፉም:-



አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ ከአሜሪካን ፕሬዚደንት ኬኔዲ ጋር

*"ይድረስ ለወታደራዊ መንግሥት ደብዳቤ አለቃ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ።*

*ጄኔራል አማንን ተክተው አሜሪካን አገር የኢትዮጵያ ሚሊታሪ አታሼ በነበሩ ጊዜ የምንተዋወቅ ይመስለኛል። ኤምባሲውን ለቅቄ ስወጣም እርስዎ ኤምባሲው ውስጥ ነበሩ። እኔ ጃንሆይን በመቃወም ጽሑፍ ስሰጥ ነበር።*

*አሁን ግን ንጉሡ ነገሥቱ ሞተው ምን ይፍጠሩ ተብሎ ነው ስማቸውን በመገናኛ ብዙሐን የምታጠፉት? ወደፊት የናንተስ ምን እንደሚመስል ታውቃላችሁ? በበኩሌ እሳቸውን ከመቃብር ቀስቅሼ ስማቸውን ማንሳት ትቻለሁ። እናንተም ስም ማጥፋቱን እንድትተው አደራ እላለሁ።*


*አክባሪዎ* *ብርሃኑ ድንቄ*

## የታህሣሥ ግርግር


በ1953 ዓ.ም በታህሣሥ ወር መጀመሪያ ላይ ጃንሆይ ብራዚልን በመጐብኘት ላይ እንዳሉ ድንገት የመንግሥት ግልበጣ ሲታወጅ ብዙ ሰው ግራ ተጋብቶ ነበር። ወዲያው ደግሞ የመንግሥት ግልበጣውን የሚቃወሙ መኖራቸውን ሕዝቡ ሲሰማ ነገሩ በጣም አሳሰበው። ግልባጩ ኃይል የክብር ዘበኛ፣ አክሻፊው የጦር ሠራዊት ይሆንና፣ በተፈጠረው አለመግባባት ሁለቱ ኃይሎች ተጋጭተው፣ በአዲስ አበባ ከተማ ጦርነት ተከፈተ። መጨረሻ ላይ የክብር ዘበኛ ጦር ተፈረካከሶ የመንግሥት ግልበጣውም መሪዎች የሞተው ሞቶ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ከወንድሙ ከገርማሜና ከሌላ መኮንን ጋር ሸሹ። ይሁንና በሳምንቱ ተደርሶባቸው ሌሎቹ በተኩስ ልውውጥ ሲገደሉ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ግን ቆስለው ተያዙ። በኋላም ፍርድ ቤት ቀርበው በሞት እንዲቀጡ ተበይኖባቸው አዲስ አበባ ተክለ ሃይማኖት አደባባይ ላይ በስቅላት ተቀጡ።

በዚህ ግርግር መካከል ብዙውን ሰው ቅር ያሰኘው የተለያዩ መኮንኖች በመንግሥት ግልበጣው በመሳተፍ ከሞቱ በኋላ በድናቸው መሰቀሉ ነበር። በመጀመሪያ ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ በኋላ ደግሞ አቶ ገርማሜ ንዋይና ሻለቃ ባዬ ጥላሁን አስከሬናቸው እንዲሰቀል ተደረገ።





መንግሥቱ ፡ ንዋይ ፡



ገርማሜ ፡ ንዋይ ፡

የብዙዎቹን ፡ ደም ፡ በግፍ ፡ ያፈሰሱት ፡ ከሓዲዎች ፡ የመንግሥቱ ፡ ንዋይና ፡ የገርማሜ ፡ ንዋይ ፡ ፎቶግራፎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። በደለኞችን ፡ በነሱ ፡ ፍርድ ፡ እመዛዝነው ፡ ለይተውና ፡ ዐውቀው ፡ የሠሩ ፡ ቢሆኑ ፡ ለሕዝብ ፡ አሰብን ፡ ብለው ፡ ለማበበያ ፡ የተናገሩትን ፡ ቃል ፡ በመዛዘን ፡ ነበር ።

ይልቁንም ፡ ጭፍሮቻቸው ፡ የሆኑትን ፡ የክብር ፡ ዘበኞች ፡ ታማኙን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከዳ ፡ ብሎ ፡ በመናገር ፡ እታለው ፡ ከሞቀ ፡ ቤታቸው ፡ ከልጆቻቸውና ፡ ከመላ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ ለይተው ፡ ደኅና ፡ የተቋቋመውን ፡ ጦር ፡ አበላሹ ።

እውነት ፡ የሠራሉ ፡ ሸሽቶ ፡ ለራሱ ፡ ለማምለጥ ፡ እንዴት ፡ ይጣጣራል ፤ ለራሳቸው ፡ ምኞት ፡ የከዱ ፡ መሆናቸውን ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ ገልጾታል ።

ጢማቸውን ፡ በመላጨት ፡ ወይም ፡ በማሳደግ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዘዴ ፡ ይለወጡ ፡ ይሆናል ። እነሱን ፡ ይዞ ፡ ላመጣ ፡ ታማኝ ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ብርና ፡ ($ 10000) ልዩ ፡ ሽልማት ፡ ይሰጠዋል ።

የጦር ፡ ኃይሎች ፡ ጠቅላይ ፡ ኤታ ፡ ማዦር ፡ ሹም ፡

ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይንና ወንድሙን ገርማሜ ንዋይን ለማደን የተበተነ ወረቀት

መፈንቅለ መንግሥቱን ያከሸፉት የጦር ሠራዊት ጄኔራሎች መርዕድ መንገሻና ከበደ ገብሬ ነበሩ። ጄኔራል መርዕድ በ1959 ዓ.ም ጳጉሜ 5 ቀን ድንገት ሞቱና መስከረም 1 ቀን 1960 ዓ.ም ተቀበሩ። ከረጅም ጊዜ በኋላ ጄኔራል ከበደ ገብሬን ደርግ ገደላቸው። ጄኔራል መርዕድ የሞቱበት ምክንያት በህመም ይሁን በሌላ በእርግጠኝነት ባይታወቅም ሁለት ዓይነት ምክንያቶች ከሕዝብ ዘንድ ይሰማሉ። አንደኛው በተፈጥሯቸው ደፋር ስለነበሩ ቁጭታቸውን መደበቅ ስላልቻሉና ንጉሡንም በቃሎት እስከማለት ደርሰው ነበር የሚል ሲሆን ሁለተኛው ግን አሮጌ መሣሪያዎች ለነጋዴዎች ተሽጠው በእጅ አዙር ለሶማሊ መንግሥት መሸጡን ስለደረሱበት በመቃወማቸው የተነሳ ከባለሥልጣኖች ጋር ሊግባቡ ባለመቻላቸው ነው።

መፈንቅለ መንግሥቱ እንዲከሽፍ ያደረገው ምክንያት የፖሊስ ፈጥኖ ደራሽ አዛዥ የነበረው የሊፍትናንት ኮሎኔል ታደሰ ብሩ ክዳት ነበር። የፖሊስ ፈጥኖ ደራሽ ወታደሮች በሌ. ኮሎኔል ታደሰ ብሩ ታዘው በክብር ዘበኞች ላይ ከጀርባ በመተኮሳቸው ሲሆን የክብር ዘበኞቹም ጃንሆይን መክዳታቸውን ስላወቁና ስለተበታተኑ ነበር። ይህ ኮሎኔል ጄኔራልነት ማዕረግ ከደረሰ በኋላ በፊትም ለግል ሹመት ሲል ግልበጣውን ቢያከሽፍም በሜጫና ቱለማ ንቅናቄ አመራር ውስጥ በመገኘቱ ሸቶ ከተደበቀበት ተይዞ ታሰረ። በመሠረቱ የሜጫና ቱለማ ንቅናቄ የመረዳጃ ማኅበር ሲሆን ከአባሎቹ አብዛኛዎቹ የኦሮሞ ተወላጆች ስለነበሩ የኦሮሞን ልጆች በየመንደሩ እየሰባሰቡ ለማስተማር ጥረት ማድረግ ሲጀምሩ በጊዜው የመንግሥት ሥልጣን ላይ የነበሩት በሌላ ስለተረጎሙባቸው እንደ አድመኛ ተይዘው ተቀጡ። ይሁንና የባለሥልጣኖቹ መደንበር የማኅበሩን ዓላማ መልክ ቀይሮታል። ጄኔራል ታደሰ ብሩ በመጨረሻ በደርግ ዘመነ መንግሥት 'ኢትዮጵያ ትቅደም' የሚል ምልክት የተሸጠበትን ከሰማንያ ሺ. ብር በላይ ከአንድ ሻለቃ ጋር አባክነው ተይዞ ተገደለ።



የኔነህ መንግሥቱ



የጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ መሳይ ልጁ የኔነህ መንግሥቱ ምንም ፖለቲካ ውስጥ ሳይገባ በአዲስ አበባ ውስጥ ይኖር ነበር። የኔነህ መንግሥቱ ቀልጣፋ የከተማ ልጅ ከመሆኑም በላይ አባቱን ስለሚመስል ሰዎች ይለዩት ነበር። ስኩተር ዶቅዶቁ ይነዳ ስለነበረ በተለይ በቀደሞው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጎዳና ላይ ወዲያ ወዲህ ሲጋልብ ይውልና ለእረፍት ብዙውን ጊዜ ቲ ሩም በሚባለው ቡና ቤት ይቀመጥ ነበር። በአደጋ ሞተ ተብሎ ሲወራ ብዙ ሰው አዝኖ አስገድለውት መሆን አለበት እያለ አማ። ይህን ነገር ለማጣራት ባደረኩት ውይይት የሞተው አቃቂ አሮጌው ድልድይ ላይ ስኩተሩን ሲያሽከረክር መኪና ገጭቶት ወድቆና በጣም ቆስሎ አራት ቀን ያህል ታሞ መሞቱን ነው። ለሚያስታምሙት ለእናቱ አጎት ልጅ "እትዬ ገደሉኝ እኮ!" ማለቱን ነግረውኛል። ይሁንና ንጹህ አደጋ መሆኑ በቤተዘመድ በእናቱም ጭምር እንዳታመነበት ታውቋል። በተጨማሪ ሊላ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ብላታ ታከለ የልጁን ፎቶግራፍ አባዝተው ጂማ ላሉ ተማሪዎች በትነው ለፖለቲካ ማነሳሻ አድርገውት እንደነበረ ነው።

## ዋለልኝ መኮንን

ከ1953 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ማግሥት ጀምሮ ተማሪው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ላይ በኅብረት የተቃውሞ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመረ። በተማሪው ተከታታይ እንቅስቃሴ አንድ ክሮኮዳየል (አዞ) የሚባል የኮሚኒስት ቡድን ተፈጥሮ ብዙ ጀብደኞች መሪነቱን ይዘው ዩንቨርስቲው ውስጥ እየወጡና እየገቡ ለ10 ዓመትና ከዛም በላይ እየተድበሰበሱ ኖሩ። መጨረሻ ላይ ተማሪውን መሣሪያ በማድረግ የኮሚኒስት ኃይል ሥልጣን እንዲጨብጥ አደረጉ።

ዋለልኝ ከአዞ ቡድን ወስጥ ከመሪዎቹ አንዱ ነበር። ንግግር አዋቂ፣ ለሚያምነው ዓላማ ጥርት ያለ አቋም ያለውና የመሪነት ጠባይ የሚታይበት የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበር። የመጣውም ደሴ ከሚገኘውና ብዙ ተጋድሎ ያደረጉ ተማሪዎች ከወጡበት ከወይዘሮ ስሂን ትምህርት ቤት ነው።

በየዓመቱ ተማሪዎች ሠላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ አለመግባባት እየተፈጠረ ነገሮች በሚካረሩበት ጊዜ ንጉሡ ነገሥቱ እንደተለመደው ንግግር

እ.ያደረጉ ተማሪውን ትምሕርት ሲያቆም እየተቆጡና ምሕረት እየሰጡ ወደ ትምሕርት ገበታቸው እንዲመለሱ ያዝዙ ነበር። በ1962 ዓ.ም እንደተለመደው ንጉሠ ነገሥቱ ንግግር ካደረጉ በኋላ "የአዋጁ አዋጅ" የሚል ለንግግራቸው መልስ ተጽፎ ተበተነ። ጽሑፉን ያረቀቀው ከተማሪው የኮሙኒስት ቡድን መካከል ታዋቂ የነበረው ዋለለኝ ነው ተብሎ ይታመናል። ጃንሆይ በዚህ በተበተነው ወረቀት ክብራቸው ስለተነካ ሕዝቡ በየድርጅቱና በየአውራጃው እየተሰባሰበና እየተወከለ ጃንሜዳ ድንኳን ተተክሎ ከመላው ኢትዮጵያ እየመጣ ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ እየቀረበ ታማኝነቱን እየገለጸ ይቅርታ ጠየቀ።

ዋለልኝ መጨረሻ ላይ የሞተው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ ላይ ከዘጠኝ ጓደኞቹ ጋር ሆኖ የተሳፈሩበትን አይሮፕላን ለመጥለፍ ሲሞክሩ በጸጥታ አስከባሪዎች ተተኩሶበት ነው። አንድ የፖለቲካ ቡደን ለጸጥታ ኃይሎች ጠቁሞባቸው ነው ለሞት የበቁትም እየተባለ በሰፊው ተወርቷል።






# ምዕራፍ ፴፬

# የጃንሆይ ወዳጆች

ጃንሆይ ጠላት እንዳላቸው ሁሉ ብዙ የልብ ወዳጆች ነበሩዋቸው። ለረጅም ዘመን አገሪቱን በማስተዳደራቸው የተነሣ አብዛኛው ሕዝብ ከልብ የሚወዳቸውና የሚያፈቅራቸው ግርማ ሞገስ የተላበሱ ንጉሠ ነገሥት ነበሩ። ሕዝቡ ከፍቅሩ የተነሣ ጃንሆይ ተነኩ ማለት ኢትዮጵያ እንደተነካች አድርጎም ይመለከት ነበር። በግልም የንጉሠ ነገሥቱ ሃቀኛና የመንግሥታቸው ጠባቂ የሆኑ ብዙ ወዳጆች ነበሩዋቸው። እነዚህ ሰዎች የጃንሆይን ዘመነ መንግሥት ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ሆነዋል። በሌላ በኩል የጃንሆይን ከሥልጣን መውረድ የሚከላከሉት ለራሳቸውም ደህንነት በማሰብም ጭምር ነበር። ከነዚህም ሰዎች መካከል ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

## ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ

ልዑል ራስ ካሣ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሁለት በኩል ይዛመዳሉ። የልዑል ራስ ካሣ እናት ወይዘሮ ትሰሜ ለአባታቸው ለራስ መኮንን የአጎታቸው የራስ ዳርጌ ልጅ ሲሆኑ ለጃንሆይ በእናታቸው በኩል ደግሞ የአያታቸው የወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ልጅ ናቸው ወይም ለእናታቸው ለወይዘሮ የሺ እመቤት እህት ናቸው። በዝምድና ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት ልዑል ራስ ካሣ ጃንሆይን



ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ

በምክርም ኾነ በአገልግሎት በጣም የረዷቸው ከመሆኑም በላይ መጨረሻ ላይ ሙሉ አመኔታ አግኝተዋል። አልፎ ተርፎም ልጃቸው ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ በኤርትራ የጃንሆይ እንደራሴ በመሆን በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ በጣም ታማኝና ተወዳጅ ሰው ነበሩ።

## አባ ገብረ ሃና ጂማ (አባ ሃና)



አባ ገብረ ሃና ጂማ (አባ ሃና)

ልጅ ሺበሺ ጂማ በአባታቸው ጎጃሜ በእናታቸው ሰሜን ሸዋ ሲሆኑ የተወለዱት ሐረርጌ በ1902 ዓ.ም ነው። የደጃች ተፈሪ አሽከር ሆነው ሲኖሩ ዕድሜያቸው ከፍ ሲል መንኩሰው አባ ገብረ ሃና ተብለው በብህትውና ደብረ ሊባኖስ ገቡ። ገዳሙ ውስጥ ያለውን የራስ ተፈሪን የዕርዳታ ድርጅትንም ይቆጣጠሩ ነበር። ከ1922 ዓ.ም ጀምሮ ታማኝ አሽከር በመሆን ዕርዳታ አከፋፋይ ሆነው ቆይተው በጣሊያን ወረራ ምክንያት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በስደት አብረው ሄዱ። ከዚህም ወቅት ጀምሮ እስከ 1953 ዓ.ም ድረስ በልዩ ግምጃ ቤትነት አገልግለዋል። ወንድማቸው ልጅ ፋንታዬ ጂማ አቤቶ ኢያሱ ሐረር በታሰሩበት ወቅት ታማኝ ጠባቂ ሆነው ነበር እየተባለም ይነገራል። በኋላ ቀኛዝማች ፋንታዬ ጂማ የልዑል መኮንን አልባሽ ሆነው ያገለገሉ ሰው ነበሩ።

አባ ሃና በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነት የላቸውም ነበር። አንዱና ዋናው ምክንያት ጃንሆይ እፍስ አድርገው ለድሃ ገንዘብ ሲሰጡ ይቀበሉና ቀንሰው ስለሚሰጡ ነው። እዚህ ላይ ጃንሆይ እፍስ አድርገው የሚሰጡት ገንዘብ ቀጥታ ለተሸላሚው እንዲደርስ ቢፈልጉ ኖሮ አባ ሃናን ማስከተል አልነበረባቸውም። ነገሩ ጥላቻውን አባ ሃና ፍቅሩን ጃንሆይ እንዲወስዱ አባ ሃና ጥላቻ መጣያ (Scape Goat) ተደርገው የኖሩ ሰው ናቸው። በዚህም የተነሣ የአባ ሃናን ተግባር የተመለከተ ሰው ሁሉ አንድ ሰው ለገንዘብ ሲንገበገብ ሲያይ እስካሁን ድረስ "አባ ሃና" ይለዋል።



ሆኖም አባ ሃና በቤተ መንግሥቱ ተከብረውና ተፈርተው ሲኖሩ እነ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ባደረጉት የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት አረንጓዴ ሳሎን ውስጥ ከተገደሉት መኳንንቶች መካከል አንዱ ሆኑ።

## አቡነ ባስልዮስ



አቡነ ባስልዮስ

እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ወልደ ፃድቅ ሐረር ደጃች ተፈሪ ቤት ሄደው "ተፈሪ ሲነግሥ እኔ ሊቀ ጳጳስ ልሆን ታዟል" እያሉ መተንበያቸውን ተፈሪ ሰምተው አስጠሯቸው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የደጃች ተፈሪ ማዕድ ባራኪ በኋላም የንስሃ አባት ሆነው በክብር ኖሩ። በስደትም ዘመን ከጃንሆይ ጋር አብረው ሄደዋል። እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ከኢየሩሣሌም የመድኃኔ ዓለምን ጽላት ከአምስት መነኮሳት ጋር እንግሊዝ አገር ልከው በባዝ ከተማ ፌርፊልድ መንገድ ላይ በሚገኘው የንጉሠ ነገሥቱ የስደት መኖሪያ ቤት ስዕል ቤት ወስጥ ይቀደስበት ነበር።

ሁኔታው ተቀይሮ ጃንሆይ ወደ አገር ቤት ሲመለሱ አንድ ቀን የጃንሆይን ልብስ ይዘው "እባክዎ በድል አገራችን ስንመለስ ቂም በቀል እንዳይኖር ያድርጉ" ብለው ቃል አስገቧቸው። እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ተብለው ተሹመው ሕዝበ ክርስቲያኑን ሲያገለግሉ ኖረው ሲያርፉ ደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ።

## መኮንን ኃብተ ወልድ

መኮንን ኃብተ ወልድ ዳግማዊ ምኒልክ በታመሙ ጊዜ ቀሳውስት ሱባዔ ሲገቡ ከእንጦጦ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ መንግሥት ተልከው የመጡ ዲያቆን ናቸው። በቤተ መንግሥት ውስጥ በመለማመድ ሥራ ጀምረው ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት መኮንን ኃብተ ወልድ

የንግድ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ነበሩ። በኢትዮጵያ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ታሪክ የመጀመሪያው ዋና ዲሬክተር እሳቸው መሆናቸው ነው። በዋና ዲሬክተርነታቸው ጊዜ ጉምሩክንም ያዝሁ ስለነበረና የጣሊያንም መምጣት ስደትን እንደሚያስከትል ቀደም ብለው አውቀው ስለነበረ ገንዘብና ወርቅ ወደ እሥራኤል አገር ይልኩ ነበር ይባላል። ከማይጨው መልስ በአገር ውስጥ ከነበሩት የውጭ አገር ቆንሲሎች ጋር በመመካከር ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ የመሄዳቸውን ሃሳብ ካቀረቡት ሰዎች አንዱ ነበሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ ሲሄዱ አብረው ከተሰደዱትም ባለሥልጣኖች አንዱ ናቸው።


መኮንን ኃብተ ወልድ በ1927 ዓ.ም በልዑል መኮንን ኃይለ ሥላሴ የክብር ፕሬዚዳንትነት የአገር ፍቅር ማኅበር ሲቋቋም ምርጥ ጸሐፊዎችንና ተናጋሪዎችን እየጋበዙ ለሕዝብ ስለወቅቱ ሁኔታ ማብራሪያ ይሰጡ ነበር። ለማይጨው ዘመቻ ማኅበሩ ስንቅ በማሰባሰብና ስለ አገር ጉዳይ ንግግር እያደረገ "የጠቅል አሽከር!" እየተባለ ይፎክርና ይሸለል ነበር። መኮንን ኃብተ ወልድ ከስደት መልስም ይኸንኑ ማኅበር እንደገና አደራጅተው ዘፈን፣ ውዝዋዜና ቲያትር ይታይበት ጀመር።

መኮንን ኃብተ ወልድ አገር ወዳድና ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ ከመሆናቸው በላይ ከስደት መልስም በመንግሥት ሥራ ላይ ከፍተኛ አገልግሎት የሰጡ ሰው ናቸው። ከባድ ሠራተኛ ከመሆናቸው የተነሳ የዕረፍት ጊዜ እንኳን አያውቁም ነበር። ከሠሯቸው ትልልቅ ሥራዎች አንዱ የኢትዮጵያ ብር በ1937 ዓ.ም ከወጣ በኋላ ነጋዴዎችን ሰብስበው እንደማርያቴሬዛ ያሉትንና ሌሎች ገንዘቦችን እንዳይለዋወጡባቸው ቃል አስገብተው ከገበያ ያስወጧቸውና አዲሱን ብር በስፋት ሕዝቡ እንዲቀበለው ማድረጋቸው ነው። ሁለት ወንድሞቻቸውም ሚኒስትር ደረጃ ደርሰው በአንድ ወቅት ሦስት ወንድማማቾች በጃንሆይ ካቢኔ ውስጥ ነበሩ።

የእርሻ የንግድና የእንዱስትሪ ሚኒስትር ከሆኑ በኋላ በ1943 ዓ.ም አራዳ መካከል ዚንጎኒ ፊትለፊት የልዑል ራስ ካሣ ቤት የነበረው ውስጥ የታክሲ ደርሚ (የደረቀ የእንስሳት ገላ) የታየበት የመጀመሪያውን ኤግዚቢሽን ኢትዮጵያ ውስጥ ለአንድ ሳምንት አሳዩ። ቀጥሎም አራዳ መካከል በሚገኘውና በዘመኑ የልማት ባንክ ሕንጻ በሚባለው ላይ "ቀጥ ትክሉ ፍተሉ" የሚል ተንቀሳቃሽ ጽሑፍ እስለጥፈው ሕዝቡን ለሥራ ያነሳሱ ነበር። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለየግላቸው ሁሉንም



ነገር በሚሠሩበት ወቅት ብዙ መዝረክረክ መኖሩን እንደተገነዘቡ ማዕከላዊ የዕቃ ግዢ፣ የሂሳብ አሠራርና ቁጥጥር ከማቋቋማቸው ሌላ የኮንትሮባንድ መከላከያ አደራጁ።



መኮንን ኃብተ ወልድ

የችርቻሮና ቀላል ሥራዎችን ለአገር ተወላጅ ብቻ እንዲሆን ወጥነው እግብ ሳያደርሱት ሞት ቀደማቸው። ክቡር አቶ መኮንን ኃብተ ወልድ ስለ አገር ወዳድነታቸው ምንም ጥርጥር የሌለው ከመሆኑም በላይ ብዙ ጠቃሚ ሥራ ለመሥራት ወደ ኋላ የማይሉ ሰው ነበሩ። አቶ መኮንን ኃብተ ወልድ በከነት ስለሚጠሉ በሁሉም ነገር ላይ ቁጠባ ያደርጋሉ። ስለሆነም ደሞዝ ለሠራተኛ ሲቆርጡ በተቻለ አነስ ያድርጉ ነበር። ገንዘብም ያለምክንያት አትወጣም። በዚህ ምክንያት ሰዎች የሚከተለውን ገጥመውባቸዋል።

መኮንን ኃብተ ወልድ የመከረው ምክር
የበርታ ይብላ የደከመ ይቅር የሚል ነበር።

የኾነው ሆኖ ክቡር አቶ መኮንን ኃብተ ወልድ የስለላ መረብ ዘርግተው ጃንሆይን ከአደጋ ሲጠብቁ የነበሩ ከመሆናቸው በላይ በአገር ፍቅር ማኅበር የሚታየው ቲያትርና የሚዘፈነው ዘፈን ንጉሠ ነገሥቱን እንዲያሞግስ ሆኖ ነበር። በመጨረሻ በታኅሣሥ 1953 ዓ.ም ያልተሳካ የመንግሥት ግልበጣ ላይ ከተረሸኑት ባለሥልጣኖች አንዱ ነበሩ።

# ደጃዝማች ከበደ ተሰማ

ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ወላጅ አባታቸው ቀኛዝማች መንገሻ አየነህ ሲሆኑ እናታቸው ወይዘሮ ደስታ ተሰማ ናቸው። የሚጠሩት ግን ባሳደጓቸው አያታቸው በአዛዥ ተሰማ አንበሴ ነው። አያታቸው አዛዥ ተሰማ አንበሴ የአፄ ምኒልክ መድፈኛ ክፍል ውስጥ ያገለግሉ ነበሩ። ደጃዝማች ከበደ ቁመታቸው ዘለግ ያለና ወፍራም ስለነበሩ የሌላ አፍሪካ አገር ሰው መስለው ያሳስቱ ነበር።



ደጃዝማች ከበደ ተሰማ

በመጀመሪያ የንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ በኋላም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የእልፍኝ አስከልካይ ነበሩ። ምንም እንኳን የታሪክ ማስታወሻ የሚለው መጽሐፋቸው ላይ ቢያስተባብሉም የንግሥት ዘውዲቱ እልፍኝ አስከልካይ በነበሩ ጊዜ ለራሰ ተፈሪ ወሬ ያቀብሉ ነበር እየተባለ ይታማሉ። እንዲያውም የሰው ሃሜት የንግሥት ዘውዲቱ አሟሟት ላይም ያነካኳቸዋል።

አዛዥ ከበደ እሥራኤል አገር የገዳማት ንብረቶችን ባለይዞች ለመውረስ ሲሞክሩ በመከላከል ተግባር ላይ ተሠማርተው በጠላት ከመወሰድ አድነዋል። ጃንሆይ ከስደት በመመለስ ሱዳን ላይ እንዳሉ ተጠርተው ከአርበኞች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ወደ አገር ቤት ቀድመው ተላኩ።



ከነፃነት በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባነት፣ በዘውድ አማካሪነት፣ በብሔራዊ ጦር አዛዥነት በታላቅ ሞገስ እያገለገሉ የኖሩ ሰው ናቸው። በመጨረሻውም ሰዓት የግቢ ሚኒስትር ነበሩ።

የቤተ መንግሥቱ ዋና ሚስጢር ጠባቂ ከመሆናቸው በላይ የማያውቁት ነገር ስላልነበረ በጣም ይፈሩ ነበር። ብዙ ሰዎች ሌ. ኮ. መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን በሥልጣን ያደላደሏቸው እሳቸው ናቸው ይላሉ። እንደሚወራውም የኮ. መንግሥቱ አባት ሃምሳ አለቃ ኃይለ ማርያም መጀመሪያ የነበርሃኑ ባዬ አጎት የአቡነ አብርሐም አገልጋይ የነበሩና ጦርሠራዊት መግሪያ ጠጋኝ ከመሆናቸው በፊት የደጃዝማች ከበደ አሽከርም እንደነበሩ ነው። የሃምሳ አለቃ ኃይለ ማርያም ሚስትም ደጃች ከበደ ከንግሥተ ነገሥት ደንገጡር ከጠጪት በድብቅ የወለዷትና በወንድማቸው በይልማ ተሰማ አባትነት የምትታወቅ ልጅ ስለነበረች ይፋ ባልኾነ መንገድ ለኮሎኔል መንግሥቱ ቅድመ አያታቸው ስለነበሩ "የኛው ልጅ ነው" እያሉ ጃንሆይንም አዘናግተዋል ይባላል። ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ጃንሆይን ለረጅም ጊዜ በታማኝነት አገልግለው ራስ ተብለው ባለመሾማቸው ቅር ስለተሰኙ ጃንሆይን አዘናግተው ካስፈቀዱ በኋላ 'የታሪክ ማስታወሻ' የሚል መጽሐፍ ጽፈዋል። ጃንሆይ ያላሰቡት ዓይነት መጻሐፍ በመጻፉ ተቆጭተው 'እኔና የሕይወቴ እርምጃ' የሚል መጽሐፍ በተራቸው አሳተሙ።

በሌላ መልኩ ኮሎኔል መንግሥቱ በቅርቡ ከደጃዝማች ከበደ ተሰማ ጋር ምንም ዝምድና እንደሌላቸው በሰጡት ቃለ መጠይቅ ተናገረዋል። ሃምሳ አለቃ ኃይለ ማርያምም ይህ ታሪክ ተረት ነው ብለዋል። ራሳቸው ደጃዝማች ከበደም ኮሎኔል መንግሥቱን በአካል ያዩኋቸው ሦስት ጊዜ ብቻ ነው በማለት ተናግረዋል። ሕዝቡን በይበልጥ ጥርጣሬ ውስጥ ያስገባው ልጃቸው አቶ ካሣ ከበደም የኮሎኔል መንግሥቱ ታማኝ ባለሥልጣን መሆናቸው አንዱ ምክንያት ሲሆን ሌላው ኮሎኔል መንግሥቱ ደጃዝማች ከበደን ከሌሎች መኳንንቶች በተለይ አክብረው መያዛቸውና ሲሞቱም በክብር እንዲቀበሩ ማድረጋቸው ነው። ስለዚሁ ጉዳይ ኮሎኔል መንግሥቱ ተጠይቀው ሲመልሱ "ደጃዝማች ከበደን ያከበርኳቸው የታሪክ ማስታወሻ በሚለው መጽሐፋቸው ሲሆን አቶ ካሣ ከበደንም በታጠቅ ጦር ሠፈር በሚሠሩበት ወቅት ንቁና ቀልጣፋ ሆነው ስለ አገኘኋቸው ነው" ብለዋል።

# ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ

ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ዋና ፀሐፊ፣ በኋላም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ነበሩ። ከጃንሆይ ጋር በስደት ከሄዱት ሰዎች አንዱ ሲሆኑ የጃንሆይ ፀሐፊ ሆነው አገልግለዋል። ከስደት መልስ ቀስ በቀስ በሥልጣን በማደግ በፅሕፈት ሚኒስትርነት ማዕረግ እያሉ በጣም የሚፈሩና የሚከበሩ ነበሩ። በዘመኑ ከነበሩት ባለሥልጣኖች የሚስተካከላቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው ብቻ ነበሩ። ራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው ረጅም፣ መልከ መልካምና ሽቅርቅር ቢሆኑም ሰው የሚንቁ፣ ሰነፍና ብልህነት የሚያንሳቸው ነበሩና ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስን በተስሚነት ሊወዳደሩዋቸው አልቻሉም። ምንም እንኳን ፀሐፊ ትዕዛዝ የፈረንሳይኛ ቋንቋ የሚናገሩ ቢሆንም የውጭ አገር ትምሕርታቸው አያወላዳቸውም ነበር። በአገር ውስጥ ትምሕርት የገፉ፣ በተፈጥሮም ብልህና ዘዴኛ ስለነበሩ• በተጨማሪም በንጉሠ ነገሥቱ የተወሰኑ ወሳኔዎቸ ሁሉ በሳቸው ፊርማ ስለሚተላለፉ በጣም ተደማጭ ነበሩ። በዚህም ምክንያት በዘመኑ የነበሩ የውጭ አገር ሰዎች 'የወልደ ጊዮርጊስ መንግሥት' (Uncrowned Emperor or Wolde-Giorgis' Government) እያሉ እስከ መጥራት ደርሰዋል።

ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ሥልጣናቸው ከጃቸው እንዳይወጣ ይሰጉ ስለነበረ ልዕልት ተናኘ ወርቅን ለማግባት ጥረት አድርገዋል። ትውልዳቸው ሲጠየቅ ውልደታቸው የባላባት ወይም የሹም ልጅ ሆነው ስላልተገኙ ሊጋብቻ አለመመጠናቸው ታውቆ ሳይሳካ ቀረ ተብሎ ተወራ። በተጨማሪም የንጉሠ ነገሥቱ ተወዳጅ አማካሪ የነበሩት ጄኔራል ዓቢይ አበበ ስለፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ቅን አመለካከት ስላልነበራቸው ሌሎች ባለሥልጣኖችም ገሸሽ ሲደረጉ እሳችውም የአርሲ አገረ ገዥ ሆነው ተሾሙና በደረጃ ዝቅ አሉ። ሆኖም መጨረሻ ላይ መኖሪያቸውን እንግሊዝ አገር አድርገው እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ንጉሡ ዘንድ እየቀረቡ ስለታላላቅ ጉዳዮች ያማክሩ ነበር። አሁን ግን በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።



# ዕንቆ ሥላሴዎች

ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቆ ሥላሴና ወንድሞቻቸው፣ ደጃች ከፍሌ፣ ደጃች ወርቁና ፊታውራሪ ታደሰ እንዲሁም ሌሎችም የቅርብ ዘመዶቻቸው በጣሊያን ወረራ ጊዜ በጀግንነት የተዋጉ የአርበኛ ልጆችና ራሳቸውም ጀግና አርበኞች ነበሩ። እንደሚታወቀው ምንም የመርሐ ቤቴ ተወላጆች ቢሆኑም ፍልስታቸው ከጎንደር የመጡ የአስኳል ዘሮች ናቸው። ከንጉሡ ስደት መልስ በኋላ ደጃች ፀሐዩና ደጃች ወርቁ በመንግሥት ባለሥልጣንነት ለጃንሆይ ታማኝ ከመሆን አልፈው ንጉሡ ነገሥቱን ከተቃዋሚዎች በመከላከል ረገድ የታወቁ ነበሩ።

ደጃዝማች ወርቁ ዕንቆ ሥላሴ የከብረ መንግሥት አውራጃ አገረ ገዥ በነበሩበትም ወቅት የአዶላ ወርቅ ማዕድንም በሳቸው ቁጥጥር ሥር ስለነበረ ሠራተኛው ማቤያውን (ካምፑን) ለቆ ሲሄድ ወርቅ ደብቆ እንዳይሄድ ኮሶ ያጠጡት ነበር። የሰበሰቡትን ወርቅ በቀጥታ ቤተ መንግሥት ያስገባሉ። ደጃዝማች ወርቁ ዕንቆ ሥላሴ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴን "አንተ አዝማሪ ና ዝፈን" ብለው ስላስጨነቋቸው እሳቸውም እሺ ብለው እንደሚከተለው ወርፈዋቸዋል።

በጣሙን አዝናለሁ ባለመሠልጠኔ
በጄ አበላዋለሁ ሽጉ አልልም እኔ"



ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቆ ሥላሴ

ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቆ ሥላሴ የወንድማቸውን ብድር ለመመለስ መኳንንቶች የሚመዘኑባት አራዳ ውስጥ ሸዋ ፋርማሲ የምትባል ቦታ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴን አግኝተዋቸው "እስቲ ተመዘን" ብለው ገና የከብደት ሚዛኑ ላይ ሲወጡ ወፈር ያሉ ስለነበሩ ሕዝብ ፊት "ለካ ውስጠ ቀላል ነዎት" አሉዋቸው ይባላል።

በተረፈ ወንድማማቾቹና ዘመዶቻቸው በተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶችና አውራጃዎች በአገረ ገዥነት ሹመት ለጃንሆይ ቅን አገልጋይ ሆነው ቆይተዋል። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ባለሥልጣኖችን እየጠራ በሚያስርበት ወቅት በተለይ ፀሐዩ ዕንቁ ሥላሴ እጄን አልሰጥም ብለው ተታኩሰው መሞታቸውን የሰማ ሁሉ ድሮም ጀግና እንደነበሩ አስመስክሩ እያለ አሞገሳቸው። እናታቸው ወይዘሮ ፍቅርተ እንኳን በሠፈራቸው የእኔ ልጅ ጀግና ነው እጁን አይሰጥም እያሉ ይፎክሩ ነበር።

በማሊያን ጊዜ ጅሩ ላይ ተሰብስበው የመጀመሪያውን የጀግኖች ማኅበር ከመሠረቱት መካከል ፀሐዩና ተስፋዬ ዕንቁ ሥላሴ፣ ጀኔራል ተድላ፣ ራስ አበበ አረጋይ፣ ደጃዝማች አሉላ በቀለና ሌሎችም መሆናቸው ይታወቃል።

## ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ



ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ

ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአባታቸው የአክስት የልጅ ልጅ ከመሆናቸውም በላይ ከተፈሪ ጋር አብረው አፈር እየፈጩ ያደጉ ታማኝ ዘመዳቸውና ወዳጃቸው ናቸው። በማይጨው ጦርነት ጊዜ ጥሩ አድርገው በስሜን በኩል የዘመተውን የጐጃምንና የጎንደርን ጦር የመሩ አዝማች ነበሩ።

በሰላሙም ዘመን በአገረ ገዥነት፣ በተለያዩ አገሮችም የኢትዮጵያ አምባሳደር በመሆን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል። በተጨማሪም ለጃንሆይ የልብ ወዳጅ ከመሆናቸው የተነሳ "በቃዎት ሥልጣንዎን ለልጅዎ ያስተላልፉ" ብለውም በወቅቱ መክረዋቸዋል።



ራስ እምሩ ከሌሎቹ መኳንንቶች የሚለዩት ኃብት ማጋበስን የማይወዱና የነበራቸውን መሬት ለሕዝብ ያከፋፈሉ፣ ቁጥብና ሕዝብ በጣም የሚወዳቸው ነበሩ። ደርግ ለሥልጣኑ የማያሰጉት ስለነበሩና በሕዝብም ዘንድ በጣም ተወዳጅ መሆናቸውን እግንዛቤ በማስገባት ምንም ዓይነት ጉዳት አላደረሰባቸውም።

## ራስ መስፍን ስለሺ



ራስ መስፍን ስለሺ

ጠላት ከመግባቱ አስቀድሞ ከሆለታ ገነት ጦር ትምሕርት ቤት ተመርቀው ለሻለቃነት ማዕረግ የበቁና ከዚያም በወረራው ጊዜ በጣም ስመጥር አርበኛ ነበሩ። በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ ሽሮ ሜዳ የሚባለው ሠፈር የነበረውን የጣሊያን ካምፕ ቀን ቀን እንቁላል እየሸጡና እየሰለሉ ሌሊት ሌሊት ሲያተራምሱት ያድሩ ነበር። በኋላም በአምቦ መንገድ መናገሻ ከተማ አጠገብ 'ሴኮንዶ ማይጨው' በተባለው ቦታ የጣሊያንን ጦር ፈጅተው ወደ ጎጃም ተሻግረው ከአርበኞች ጋር ብዙ ጀብዱ ሠርተዋል። ጃንሆይ በስደት በነበሩ ጊዜ አስፈላጊ የሆኑና የሚታመኑ መረጃዎች በማቀበል አገሪቸውን ጠቅመዋል። ጃንሆይ ሲመለሱም አርበኞችን በማስተባበር ብዙ የሚያኮራ ሥራ ሠርተዋል።

ከድል በኋላ በአራዳ ዘበኛ ኃላፊነት፣ በአ.አ. ከተማ ከንቲባነትና በአገረ ገዥነት ያገለገሉ ሰው ናቸው። አባታቸው ስለሺ የራስ መኮንን ባለሟል የነበሩና ልጅየውም ምስፍን ስለሺ በጃንሆይ ዘንድ ፍጹም ታማኝ ነበሩ።

ራስ መስፍን ስለሺ ዩኒፎርም በጣም ስለሚወዱ አንድ ጊዜ የሌፍትናንት ጀኔራል ልብስ ለብሰው ጃንሆይን "ይመርቁልኝ" ብለው ስለጠየቁና ጃንሆይም ስለተስማሙ ሌፍትናንት ጀኔራል ሆነዋል። ሆኖም በባህል

የሀማች ሹመት የመጨረሻውን እርከን በመቀዳጀት በ1948 ዓ.ም ራስ ተብለዋል።

በየአካባቢው መሬት መያዝ ይወዱ ስለነበረ የመሬት ከበርቴ ምሳሌ ከመሆናቸውም በላይ ሁኔታው ከብዙ ሰው ጋር አጋጭቷቸዋል። ደርግ ሥልጣን ላይ እንደወጣ የቀድሞ ባለሥልጣኖችን እጃቸውን የሚሰጡበትን ሰዓት ወስኖ በነበረበት ጊዜ ራስ መስፍን ከከተማ ውጭ ስለነበሩ ሰዓቱ ያለፈ እንደሆን ርስታቸው እንዳይወረስ ሰግተው ስልክ ደውለው መጣሁ በማለታቸውና ሁኔታው በወቅቱ በሬዲዮ ይተላለፍ ስለነበረ ብዙ ሰው በሁኔታው ተገርሟል። በመጨረሻ ርስታቸውም ተወረሰ፤ እሳቸውም ከተረሸኑት ከስልሳ አንዱ ውስጥ ነበሩ።





# ምዕራፍ ፴፰

# የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባህርይና ትክለ ሰውነት

## ትክለ ሰውነት

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተፈጥሮአቸው አጭር ሲሆኑ ቁመታቸው አንድ ሜትር ከስልሳ ሴንቲ ሜትር (1.60 ሳሜ)፣ ክብደታቸውም ሃምሳ ኪሎ ግራም (50 ኪግ)፣ የእግራቸው መጫሚያ ትልቅና የቀኙ ወደጎን የሚረግጥ ነበር። ጃንሆይ መልከ ቀና፣ ቀይ፣ ጥርሰ ፍንጭት፣ ትላልቅ ጆሮና አፍንጫ ያላቸው፣ ጠጉራቸው ከግንባራቸው ገባ ያለ፣ ጎፈሬያማ፣ ባለ ሙሉ ጢምና ትልቅ የቅንድብ ጠጉር ያሏቸው ነበሩ። ምንም አጭር ቢሆኑም በ20ኛው ክፍለ ዘመን ካሉት ንጉሦች ሁሉ ንጉሥ ሲኖረው የሚገባው ግርማ ሞገስ ነበራቸው።

አማርኛ ተናጋሪ ቢሆኑም በተጨማሪ አደርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ በመጠኑ ደግሞ ጀርመንኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎችን ያውቁ ነበር። ሲናገሩ አንዳንድ የሚጫኑዋቸው ቃላቶች የነበሩና የምታስቸግራቸውም ድምጽ "ረ" ስትሆን ድምጻቸው ጎርናና ነበር።

ከማጠራቸው የተነሣና ለክብራቸውም ሲባል ወንበር ላይ ሲቀመጡ ብዙ ጊዜ እግራቸው ሥር ትራስ ይደረግ ነበር።

## ባህርይ

በጠባይ በኩል የሁለት ተፈሪዎችን ስብዕና የተላበሱ ነበሩ ለማለት ይቻላል። አንደኛው ተፈሪ ትሁት፣ ሩህሩህ፣ ሊጋስ፣ ሲሆን ሁለተኛው ተፈሪ ደግሞ ቁጡ፣ ጨቋኝ፣ ቂመኛና አናካሽ ነበሩ። በጠቅላላው ግን ተፈሪ በጎብረት ኩሩ፣ ጨዋ፣ ደፋር፣ ራስ ወዳድ፣ የማስታወስ ችሎታ